በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የፈረንሳይ፤የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ

አበባው ዘውዴ

በሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ የኢትዮጵያ ሥነ - ጽሁፍና ፎክሎር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ሰኔ 2003 ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የፈረንሳይ፤የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ

አበባው ዘውዴ

በሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ የኢትዮጵያ ሥነ - ጽሁፍና ፎክሎር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ሰኔ 2003 ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የፈረንሳይ፤የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ

አበባው ዘውዱ

ሰኔ 2003 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

---------------------------- ----------------------------

ፈታኝ ፊርማ

---------------------------- ----------------------------

ፈታኝ ፊርማ

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

# ምስጋና

- በዚህ ጥናት ላይ አማካሪዬ የነበሩት ዶ/ር ዮናስ አድማሱ ያልተጠቀሱት በአማካሪነት የትምህርት ክፍሉ እንዲያማክሩኝ የመደበልኝ ቢሆንም ከመጀመሪያዎቹ ቀናት ውጪ ከአማካሪዬ ጋር ያልተገናኘንና ያላማከሩኝ በመሆኑ አማካሪ ብዬ ለመግለጽ አልቻልኩም ። በመሆኑም በግሌ ካለአማካሪ ጥናቴን ሰርቼ ለትምህርት ክፍሉ ለተቋቋሞ እንድቀርብ በጠየኩት መሰረት ለግል ተቋቋሞ ለመቅረብ የቻልኩ ሲሆን ፤የትምህርት ክፍሉም ዶ/ር ፈቃደ አዘዘን እና አቶ ዘሪሁን አስፋውን እንዲፈትኑኝ በመደበልኝ መሰረት ከሁለቱም ፈታኞቼ በተሰጠኝ ምክር መሰረት ማስተካካያዎችን በማድረግ የጥናት ወረቀቴን ለማጠናቀቅ ችያለሁ። ለዚህም የትርፍ ጊዜያቸውን ሰውተው አካዳሚያዊ፤ጥልቅ ሙያዊና መምህራዊ ምክራቸው ስለሰጡኝ ልባዊ ምስጋናዬን ለማቅረብ እፈልጋለሁ። እግዚአብሄር ይስጥልኝ ።
- በአጠቃላይ የጥናት ስራዬ ከዳር እንዲደርስ የኄኑ ያህል በማበረታትና መረጃዎችን በማሰባሰብ ላገዙኝ ተወዳጅ ጓደኞቼ ንጉስ ወዳጅነው፤ታምራት ሃይሉ፤ሰለሞን ተሾመ ፤ዘላለም ጥላሁን እና የኔጌታ ግዛው እነሆ አጋርነታችሁ እዚህ ድረስ አድርሶኛል ። አመሰግናችኋለሁ ። ታላቁን ውለታችሁን መቼም ቢሆን ሳስታውሰው እኖራለሁ ። አቶ ግዛቸው አማረ ላደረክልኝ ሁሉ ድጋፍ ሳላመሰግን ላልፍ እንዴት ይቻለኛል ።
- ለብርታቴ የሞራል ስንቅ የሆኑት ባለቤቴ ወ/ሮ ሃይማኖት ታደሰ ፤ብርቅዬ ልጆቼ እምራኬብ/ቼልሲ/አበባውና ሶሊያና አበባው እንዲሁም እህቴ ማስተዋል ዘውዴ ሊመሰገኑ ይገባል ።

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

አጠቃሎ ... 1
1. መግቢያ ... 2
1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ... 3
1. 2. የጥናቱ ዓላማዎች ... 3
1.2.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ ... 3
1.2.2.የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች ... 4
1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት ... 4
1.4 የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴ ... 5
1.4.1. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ... 7
1.5 የጥናቱ ገደብ ... 8
1.6 የጥናቱ አደረጃጀት ... 9
1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ... 11
1.8.የጥናቱ ተጠቃሚዎች ... 12
2. የንድፈ ሃሳብ ዳሰሳ ... 12
2.1. የባህል ማዕከል ምንድን ነው? ... 13
2.1.1. የባህል ማዕከላት ታሪካዊ ዳራ ... 14
2.1.2. የባህል ማዕከላት ይዞታ ... 16
3. የፈረንሳይ ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ ... 16
3.1 የፈረንሳይ ባህል ማዕከል ታሪክ ... 19
3.2 ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ ... 21
3.2.1 ስነ ስዕል ... 25
3.2.2 ስነ ፅሑፍ ... 28
3.2.3 ሙዚቃ ... 39
4. የጀርመን ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ ... 40
4.1 የጀርመን ባህል ማዕከል ታሪክ ... 44
4.2. የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ... 45
4.2.1. ስነ ስዕል ... 51
4.2.2. ስነ ጽሑፍ ... 60
4.2.3. ሙዚቃ ... 66
5. የጣሊያን ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ ... 66
5.1. የጣሊያን ባህል ማዕከል ታሪክ ... 67
5.2. የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ በጣሊያን ባህል ማዕከል ... 68
5.2.1. ስነ ስዕል ... 71
5.2.2. ሥነ ጽሑፍ ... 73
5.2.3 ሙዚቃ ... 77
6. የሶስቱ ባህል ማዕከላት ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ ተመሳሳይነትና ልዩነት ... 82
7. ማጠቃለያና ይሑንታዎች ... 88
ዋቢ መፅሐፍት ... 91
አባሪዎች ...
አባሪ 1 መግለጫዊ መዘርዝር
አባሪ 2 በመገናኛ ብዙሃን ከተላለፉት ናሙና የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች

አባሪ 3 ዋና ዋና ቃለ መጠይቆች
አባሪ 4 ጥያቄዎች

# አጠቃሎ

የፈረንሳይ፤ የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ ላይ የሚያተኩረውን ይህንን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱኝ ምክንያቶች አሉ፡፡የመጀመሪያው ምክንያት በአገራችን ከሚገኙት ኢምባሲዎች አብዛኛዎቹ የሁለትዮሽ ግንኙነቱን መሰርተው ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ስራቸውን ወደ ተሻለ ደረጃ እያሳደጉ መሆናቸውን በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን፤ፌስቲቫሎችና የዲፕሎማሲ መድረኮች ቢገልጹም፤ የላቀ ስራ በመስራትና የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር የእነዚህ ሶስት አውሮፓዊ አገሮች ግንኙነት ይበልጥ የቀረቡ መሆን የጥናት ትኩረቴን ስቦታል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኢምባሲዎቹ የባህል ማዕከላት የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን አለማየቴ የበለጠ አዲስ ነገር ፍለጋዬን እንድቀጥልበት አድርጎኛል ፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማ በፈረንሳይ ፥በጀርመንና በጣሊያን ኢምባሲዎች የባህል ማዕከላት የሚያካሄዱት ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴዎች ምን ገጽታ እንዳላቸው፥ በማዕከላቱ የሚቀርቡ እንቅስቃሴዎች ለአገራችን የኪነ ጥበብ እድገት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ማመልከትና የማዕከላቱን ታሪክ መፈተሽ ነው ፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የሶስቱንም አገሮች ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አጀማመር ምን ይመስል እንደነበረ ለመዳሰስ ሞክሯል ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የባህል ማዕከላት አመሰራረትና ሂደቱ ምን ገጽታ እንደነበረው ለመመልከት ተችሏል ፡፡ የባህል ማዕከላቱን ሃላፊዎች፥የኪነ ጥበብ ስራቸውን ያቀረቡና በማቅረብ ላይ የሚገኙ የጥበቡን ሰዎች ለማነጋገር ተሞክሯል ፡፡ በኪነ ጥበቡ ዙሪያ ታዳሚዎችንና ጋዜጠኞችን ሳይቀር የጥናቱ አካል ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡
በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተሰበሰበውን መረጃ በገለጻ ዘዴ በመተንተን የቀረበው ይህ ጥናት የባህል ማዕከላቱ ለኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ከፍ ያለ ትኩረት መስጠታቸውን አረጋግጧል፡፡ ለበርካታ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች መድረኩን በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ሙያቸውን ለማሳደግ ረድተዋል፡፡ ከፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ባሻገር በፈጠሩት የባህልና የኪነ ጥበብ ግንኙነት ምክንያት የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ፤የባህልና ኪነጥበብ ልውውጥ እንዲፈጠር ያስችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት አጠቃላይ የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ጥናት በባህል ማዕከል ሲሆን ከደረሰበት ግኝት ተነስቶ የመፍትሄ አቅጣጫዎችንም ሰንዝሯል፡፡
ከመፍትሄዎች አንዱ በባህል ማዕከላቱ የሚቀርቡ የኪነ ጥበብ ስራዎች በአግባቡ እንዲቀረጹና ለትውልድ እንዲተላለፉ የየራሳቸው ባህል ማዕከላቱም ሆኑ የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም የፌዴራል ባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ትኩረት እንዲሰጡ ጥቆማ መስጠት ነው፡፡ በባህል ማዕከላቱ የሚሰጡ የኪነ ጥበብ ድጋፎች ዘላቂነት ባላቸውና በስልጠናና በምርምር እንዲደገፉም ጠቁሟል፡፡ እንዲሁም በኪነ ጥበብ ዙሪያ ስራቸውን የሚሰሩ የትምህርትና የምርምር ተቋማትም በሌላ በኩል ጠለቅ ያለ ጥናትና ሙያዊ ድጋፍ ሊሰጡ እንደሚገባ ጥናቱ ይመክራል ፡፡

# 1. መግቢያ

ኪነ ጥበብ ከባህል እና ከታሪክ ዘርፍ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው::ኪነ ጥበብ ስንል የሰዎች የፈጠራ ውጤት የሆኑ ደስታንና ሃዘንን÷ እርካታና ቁጭትን÷ ፈንጠዝያና ምሬትን÷ ስኬትንና ውድቀትን÷ህልምና ምኞትን እንዲሁም ትንቢቱንና በሆነልኙን የሚገልጽባቸው ኪነ ጥበባዊ መንገዶቹ ስነ ጽሑፉ ÷ስነ ስዕሉ÷ ስነ ህንጻው÷-ቀረጻው÷ ሙዚቃው÷ዳንስ÷ዲዛይኑ ÷ ፊልሙና ሌሎችም የአስተውሎት አይኑን የሚከፍትባቸው የፈጠራ ጥበባትን ያጠቃልላል::

የፈጠራ ስራዎቹ ወይም የኪነ ጥበብ ፈጠራዎቹ የራሳቸው የሚቀርቡበት የአቀራረብ÷ መድረክና ጊዜ ይኖራቸዋል :: ስለዚህም ኪነ ጥበቡ ከባህል ጋር ያለውን ተዛምዶ÷ ቅርበቱና የትስስሩን ያህል÷ ታሪካዊ ቁርኝቱም የኪነ ጥበቡን ይዘትና ጊዜ ለመመርመር ፤መርምሮም ለማወቅ ይረዳል ::

ለዚህም ነው በዚህ ጥናት በሃገራችን ከሚገኙ ከ93 በላይ ኢምባሲዎች መካከል ቀደምት የአውሮፓ ሃገሮች ውስጥ የሶስት ሃገሮች ኢምባሲዎች የባህል ማዕከላት አጠቃላይ ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ ታሪክን ለመመርመር የተሞከረው::

ምዕራፍ አንድ ሰባት ንዑስ ክፍሎች አሉት:: እነሱም: የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ÷የጥናቱ ዓላማዎች ÷ የጥናቱ አስፈላጊነት÷ የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴ÷ የጥናቱ ገደብ÷ የጥናቱ አደረጃጀትና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎች እንዲሁም በጥናቱ ተጠቃሚዎች የሚሉትን አካቷል::

በምዕራፍ ሁለት የንድፈ ሃሳብ ዳሰሳ ጥናት ተደርጓል:: የባህል ማዕከል ምንድን ነው ? የባህል ማዕከላት ታሪካዊ ዳራ ÷ የባህል ማዕከላት ይዞታ የሚሉ ንዑስ ርዕሶች ተዳሰውበታል :: በምዕራፍ ሶስት ደግሞ የፈረንሳይ ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴን ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል:: በዚሁ ምዕራፍ የፈረንሳይ ባህል ማዕከል ታሪክ÷ ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ ÷ ስነ ስዕል ÷ስነ ጽሁፍ ና ሙዚቃን ተመልክቷል ::

በምዕራፍ አራት የጀርመን ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ ÷ የጀርመን ባህል ማዕከል ታሪክ ÷ ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ ÷ ስነ ስዕል ÷ ስነ ጽሁፍ ና ሙዚቃ ላይ ቅኝት አድርጓል :: የጣሊያን ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ በሚል ስር የጣሊያንን ባህል ማዕከል ታሪክ ÷ ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ÷ስነ ስዕል÷ ስነ ጽሁፍና ሙዚቃው በምዕራፍ አምስትም ተዳስሷል ::

በምዕራፍ ስድስት የሶስቱ ባህል ማዕከላት ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ አንድነት ና ልዩነት÷ በምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያና ይሑንታ በምዕራፍ ስምንት ስር በጥናቱ ለመመልከት ተችሏል፡፡

## 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የፈረንሳይ ፥ የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ በየኢምባሲዎች በተቋቋሙት ባህል ማዕከላት ላይ ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱኝ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከ93 በላይ ኢምባሲዎች ጽህፈት ቤታቸውን በመዲናችን ከፍተው የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ወደ ተሻለ ደረጃ እያሳደጉ መሆኑን በተለያዩ መገናኛ ብዙሃንና በዲፕሎማሲ መድረኮች እንዲሁም በተለያዩ የምረቃና የስብሰባ መድረኮች የሚናገሩ ቢሆንም፥ የነዚህ ሶስት አገሮች ግንኙነት ግን የጠበቀ መሆኑ የጥናት ትኩረቴን ሊስበው ችሏል ፡፡ በዚህ መነሻነት ሌሎች ምክንያቶቼን ልዘርዝር ፡፡ በአንድ በኩል ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ የትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፌን ያዘጋጀሁት በሬዲዮ ፕሮግራም በቀረቡ የመዝናኛ ፕሮግራም ዝግጅቶች የኪነ ጥበብ ስራዎች ላይ ስለነበር የኪነ ጥበብ ስራዎች ላይ የነበረኝ የመስራት ፍላጎት እንድገፋበትና ሰፋ ባለ መልኩ ይህንኑ ዘርፍ እንድመረምረው አነሳስቶኛል፡፡

ሁለተኛው ምክንያቴ በስራ ዓለም በጋዜጠኝነት ÷ በህዝብ ግንኙነትና በፕሮሞሽን ሞያዬ በቆየሁባቸው 12 ዓመት በባህል ማዕከላቱ የሚቀርቡ የኪነ ጥበብ ስራዎችን የመከታተል እድል ስለገጠመኝ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በሚዘጋጁ የባህልና የኪነ ጥበባት መድረኮች ኢምባሲዎቹ ሰፋ ያለ ትኩረት የሚሰጡት በሃገሮች መካከል የባህል ልውውጥ ለማድረግና ኪነ ጥበብን ለማሳደግ ነው ፡፡ የኪነ ጥበብ ውጤቶች ከፖለቲካና ከዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በላቀ ደረጃ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱን የሚያሳድጉና ጠንካራ የስነልቦና ቅርበት የሚፈጥር በመሆኑ ነው ፡፡ እነዚህን አቀራረቦች መመርመር ደግሞ ኪነ ጥበብና ባህል ካላቸው ትስስር አንጻር አንዳች ቁም ነገር ሊያመለክተኝ እንደሚችል በመገመት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቻለሁ፡፡

ሦስተኛው መነሻ ምክንያቴ ደግሞ ሃገሮቹ በአውሮፓ አህጉር የሚገኙ በመሆናቸው በሚያቀርቡት የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለማወቅ ካለኝ ፍላጎት ነው ፡፡ በእርግጥ የሃገሮቹ ሁሉም ባህሎችና የኪነ ጥበብ ዘርፎች ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ባህል ማዕከላት ሊቀርቡ አይችሉም ፡፡ በናሙናነት

ተወስደው ግን ማዕከላቱ የተቋቋሙበትን አላማም ማንጸባረቅ እንደሚችሉ ከወዲሁ ጥናታዊ መላምት/Hypothesis/ መሰንዘር አያዳግትም፡፡

ከዚህም በላይ አጥኚው በፈረንሳይ ኢምባሲ የባህል ማዕከል ታሪክ ላይ ለመስራት ምክረ ሃሳብ /Proposal/ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ፤ በአንዱ ላይ ብቻ ከመስራት ይልቅ በሶስቱ ታዋቂ የባህል ማዕከላት ላይ አተኩሮ ቢያጠና ምርምሩን ይበልጥ ከፍ እንደሚያደርገው በድህረ ምረቃ ትምህርት መምህሩ በዶ/ር ፈቃደ አዘዘ የተሰጠው ምክር ጥናቱን ለመስራት ይበልጥ አነሳስቶታል ፡፡

## 1. 2. የጥናቱ ዓላማዎች

የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች ቀጥሎ ተጠቅሰዋል፡፡

### 1.2.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ በፈረንሳይ፤ በጀርመንና በጣሊያን ኢምባሲዎች የባህል ማዕከላት ታሪክን መፈተሽ፤ በባህል ማዕከላቱ የሚያካሄዱት ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴዎች ያላቸውን ገጽታ ፥ በማዕከላቱ የሚቀርቡ እንቅስቃሴዎች ለአገራችን የኪነ ጥበብ እድገት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ማመልከትነው ፡፡

### 1.2.2.የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች

ይህ ጥናት ከላይ የቀረበውን አበይት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በሂደት ይመልሳል ፤

- በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ኢምባሲ የባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ ምን ይመስላል
- በኢትዮጵያ የጀርመን ኢምባሲ የባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ ምን ይመስላል
- በኢትዮጵያ የጣሊያን ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ ምን ይመስላል
- የሶስቱ ባህል ማዕከላት ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ አንድነትና ልዩነት ምን ምን ናቸው

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የተለያዩ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- በቀዳሚነት ከኪነ ጥበብ ጥናት አንጻር የሚኖረው ጠቀሜታ ይጠቀሳል፡፡ ከዋና ዋና የኪነ ጥበብ ዘውጎች መካከል ስነ ጽሁፍ፥ስነ ስዕልና ሙዚቃ ላይ በማተኮሩ በሃገራችን የባህል ማዕከላቱ የሚያቀርቧቸውን የኪነ ጥበብ ስራዎችን አይነት ሁኔታ ያሳውቃል ፡፡
- በባህል ማዕከላቱ በኪነ ጥበብ ዙሪያ ለሚያጠኑ ሙያተኞችና ፍላጎቱ ላላቸው ሁሉ መነሻ ጥናት እንደሚሆን ይታመናል ፡፡
- በሃገሮቹ መካከል ከሚካሄደው ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ባሻገር ኪነ ጥበብ ያላትን የባህል ልውውጥና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ማሳደጊያ መሳሪያነት ለመመልከት ይረዳል፡፡
- የሃገሮቹ የባህል ማዕከላት ለአገራችን የኪነ ጥበብ ስራዎችና ባለሙያዎች የፈጠራ ስራ ዕድገት ያደረጉትን አስተዋጽኦ ያሳያል ፡፡

ማዕከላቱ የአገራችን የኪነ ጥበብ ውጤት በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ለመረዳትም ያስችላል፡፡

## 1.4 የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴ

ጥናቱን ለማካሄድ በዋነኛነት የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለ መጠይቅ /Interview/ ና አሳታፊ ምልከታ /Participatory observation / ፤በተወሰነ ደረጃ ያለፉ አነስተኛ ዘጋቢ ዝግጅቶችን በፊልም የማዬትና መረጃ የማግኛ ዘዴ ሳይዘነጋ / ናቸው ፡፡ አንዳንድ ስሞችን የጊዜና የመቼት እንዲሁም የሰዎችን አድራሻዎች ለማግኘትና መረጃዎችን ለመሰብሰብ በስልክ ለማረጋገጥና ክፍተቱን ለመሙላትም ተሞክሯል ፡፡ከዚህ ቀደም በፈረንሳይ ኢምባሲ የ100ኛ ዓመት በዓል ላይ የታተሙ ጽሁፎችንና የዝግጅት ማብራሪያ ጽሁፎችን ለስራው አጋዥ ለማድረግም ተችሏል፡፡በተመሳሳይም የጀርመን የ100ኛ ዓመት፤ የ40ኛ ዓመት የባህል ማዕከሉ እንቅስቃሴዎች፤የመጥሪያ ወረቀቶች፤የተተረጎሙ መጻህፍትን ሳይቀር ለመመልከት ተችሏል፡፡

### 1.4.1. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

ጥናቱን ለማካሄድ ለሶስቱ ኢምባሲዎች የባህል ማዕከላት መረጃ የመሰብሰቢያ ጥያቄዎችን በመስጠት መልስ እንዲሰጡ ለማድረግ ያደረኩት ጥረት በፈረንሳይ ኢምባሲ የአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ባህል ማዕከል የሁለቱን ሃገሮች የ100ኛ ዓመት በዓል ላይ የተዘጋጀ መጽሄት ከመስጠት ባለፈ ለጊዜው መረጃ ለመስጠትም ሆነ ለማግኘት አልተቻለም ::በኋላ ላይ ግን የባህል ማዕከሉ የህዝብ ግንኙነትና የባህል ዝግጅት አስተባባሪ የነበሩትን ወ/ሮ መርሴማ ታሪኩ በኢሜል ጥያቄዎችን ልኬ መልስ ሰጥተውኛል ። በጣሊያን ኢምባሲ በኩል የኢምባሲው የባህል አታሼና የባህል ማዕከሉ ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ቡሩኖ ቢሊቶ አጥጋቢም ባይሆን መጠነኛ መረጃ ሰጥተውኛል፡፡[1] ከሁሉም በላይ ግን በጀርመን ኢምባሲ የጀርመን የባህል ማዕከል ጥናት ፕሮግራም ዳይሬክተር ወይዘሮ ተናኜ ታደሰ ለሙሉ ቃለ መጠይቁ መልስ የተሟላ መረጃ በመስጠት ተባብረውኛል፡፡ከእርሳቸው ጋር አቶ ዮናስ ታረቀኝ የባህል ማዕከሉ የቤተመጻህፍትና ዶክመንቴሽን ሃላፊም በቃለ ምልልስና የጽሑፍ መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ ሁለተኛው የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዬ በሶስቱ ባህል ማዕከላት መድረኮች የተለያዩ የኪነ ጥበብ ስራዎቻቸውን ያቀረቡ ከወጣት እስከ አንጋፋ ሰዓሊያን ፣ የሙዚቃ እና የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎችን በአድራሻቸው በማፈላለግ በቃለ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በአንድ የዝግጅት አጋጣሚ የምፈልጋቸውን ሰዎች በማግባባት ያለፈ ዝግጅታቸውንና ስለማዕከላቱ የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ያላቸውን አስተያየት በመጠየቅ መረጃዬን አጠናቅሬአለሁ፡፡

እንደገናም በሚያቀርቡት ኪነ ጥበባዊ ዝግጅት ፕሮግራሞችን በመምራት የሚታወሱና ሙያዊ ትንታኔ ሊሰጡኝ ይችላሉ ያልኳቸውን ባለሙያዎች በአድራሻቸው በመፈላለግ በቃለ መጠይቅ ስለ ባህል ማዕከላቱና ስለአጠቃላይ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መረጃ እንዲያቀብሉኝ አድርጌያለሁ፡፡

---

[1] ዳይሬክተሩ እ.ኤ.አ ከ2009 ጀምሮ ከሃላፊነታቸው የተነሱ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

### የመረጃ ሰጪዎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ባሲዎች ዎችና ኞች | የስነ ጽሑፍ ሙያተኞች | የስዕል ሙያተኞች | የሙዚቃ ባለሙያዎች | ጋዜጠኞች | ታዳሚ ዎች | ከመጽሔትና መጥሪያ ወረቀቶች ላይ የተገኙ | ዝግጅታቸ ውን ካቀረቡት መካከል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ት ች | ሶስት ወንዶች | ሁለት ወንዶች | ሁለት ወንዶች | አንድ ወንድ | አንድ ወንድ | አምስት ወንድ | ሁለት ወንድ |
| ት ፡ | | | | | አንድ ሴት | ሁለት ሴት | ሶስት ሴት |
| | | | ድምር | | | | 26 |

ከላይ በሰንጠረገዡ እንደተመለከተው በአጠቃላይ በቃለመጠይቁ 26 መረጃ አቀባዮቼን አነጋግሬአለሁ ::ከነዚህ ውስጥ አስሩ ዋነኛ አቀባዮቼ ሲሆኑ፤ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ማብራሪያ ሰጥተውኛል::
ቀሪዎቹ አስራ ስድስቱ አቀባዮቼ ደግሞ በተመረጡ ጥያቄዎች ላይ መልስ ሰጥተዋል:: ጥያቄዎቹ በተቻለ መጠን ድግግሞሽ ያልበዛባቸውና አንዱ የአንዱን ሃሳብ የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ተደርጓል::

በሶስተኛ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የባህል ማዕከላቱ የተለያዩ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን በሚያቀርቡበት መድረክ በቦታው በመገኘት የራሴን ምልከታና ከታዳሚው መካከል የተወሰኑ ሰዎችን ስሜት በቃለመጠይቅ በመጋራት ነው ::

ይህ ጥናት ከተጀመረበት ከመጋቢት 2001 ዓ. ም ጀምሮ ከአንድ አመት በላይ በየባህል ማዕከላቱ ባደረኩት ክትትል ያገኘሁት መረጃንም ተጠቅሜአለሁ::
ሌላው የመረጃ መቀበያ ዘዴዬ በቤተመጻሕፍት የሚገኙ የጽሑፍ መረጃዎችንና የኢንተርኔት መረጃዎችን መመርመር ነው:: በዚሁ መሰረት አስፈላጊው መረጃን ለማካተት ተሞክሯል ::

ሌላው የተሟላ እንኳን ባይሆንም ይቀርቡ በነበሩ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ለታዳሚዎች ይላኩ ከነበሩ መጥሪያዎች መካከል ከአዘጋጆችና ከታዳሚዎች ጥቂቶችን በማፈላለግ( ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ፤አቶ ዘሪሁን አስፋው፤ አቶ እዝራ አባተ፤ አቶ ታምራት ሃይሉ፤ አቶ ፋንታሁን ኬሬቦ ይጠቀሳሉ) መረጃ እንዲሰጡ ለማድረግ ተችሏል ::

በመጨረሻ የተጠቀምኩት ከባህል ማዕከላቱ የተቀረጹና በአግባቡ የተቀመጡ የቪዲዮ ፊልሞች መረጃ ባለማግኘቴ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ የቴሌቪዥን ጣቢያ (ኢቲቪ-2) የኪነ ጥበባት ፕሮግራም አርካይቭ መፈተሽ ነው::[2] በመሆኑም በድርጅቱ የተቀመጡ የሶስት ዓመት /ከ1998-2001ዓ.ም / ናሙና የተላለፉ ዝግጅቶችን ለማግኘት 23 ባለ 20 ደቂቃ ፕሮግራሞችን ለመመልከት ተችሏል :: የቀረቡትን ዝግጅቶች ይዘትና የተላለፉትን መልዕክቶችም ለማግኘት ጥረት ተደርጓል:: እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተገኘውን መረጃ በማቀናጀት ለማቅረብ ተሞክሯል::

## 1.5 የጥናቱ ገደብ

ጥናቱ የፈረንሳይ፤ የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ ላይ ያተኮረ እንደሆነ ተገልጿል :: ሃገሮቹ ከአገራችን ጋር ያላቸውን ታሪካዊ ግንኙነት የባህል ማዕከላቱ አመሰራረትንና የተጓዙት ሂደት ላይ ቅኝት አድርጓል :: የባህልና ኪነ ጥበብ ትስስሩን ለማብራራትም ተሞክሯል ::

ጥናቱ የሶስቱን ሃገሮች የባህል ማዕከላት ታሪክ እና የሚያቀርቡት ዝግጅቶች ላይ የተወሰነ ነው :: ይህም የሆነበት ምክንያት ርዕሱ «የፈረንሳይ የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ » በመሆኑ . የማዕከላቱን ታሪክና እንቅስቃሴ ከማጥናት ባሻገር ሌላ ትንታኔ ውስጥ ስለማያስገባ ላድርገውም ቢባል የተለያዩ ወሰኖች ስለሚኖሩ፤ በሌላም በኩል ሁሉም ሙያዎች ላይ ምዘና እና ትንታኔ ለማቅረብ የእውቀት አድማሴ የማይፈቅድ በመሆኑ/ ለምሳሌ የስነ ስዕል . የሙዚቃና ዳንስ ወዘተ/ ነው ::

በተወሰነ ደረጃ ሙያው የሚፈቅደውን ያህል ናሙናዊ ትንታኔ እንኳን ለመስጠት በማዕከላቱ በቀረቡት ስነ ጽሑፎች ላይ ለማቅረብ ቢፈለግ (የርዕስ ገደቡ እንዳለ ሆኖ) በሶስቱም የባህል ማዕከላት ከቀረቡት ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች መካከል አንድም የተቀመጠ /Document የተደረገ/ ስራ ያላገኘሁ በመሆኑ፤በሌላ በኩል በባህል ማዕከላቱ የሚቀርቡ ስነ ጽሁፎች የተለዩ መስፈርት ተሰጥቷቸውና ተመዝነው የማይቀርቡ በመሆናቸው( ዶ/ር ፈቃደ ግን በጀርመን ባህል ማዕከል ምዘና በማድረጉ በውስጥ መረጃው የሚገኝ ሆኖ) . መረጃ አቀባዮችን በቃለመጠይቅ ፤ በመጠየቅ፤

---

[2] አርካይቡ የተዘጋጀው" ጥበብ " በሚል ርዕስ ሲሆን፡የፕሮግራሙ አዘጋጅ ከሆነው ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኤሪቦ ጋርም ረዘም ላለ ጊዜ ውይይት አድርገናል::

በምልከታና በውስን ፊልሞች ላይ በመመርኮዝ ዳሰሳዊ ምልከታ በማድረግ ታሪካቸውንና ያቀረቡትን ዝግጅቶች ብቻ ለማየት ተገድጃለሁ፡፡

እንዲሁም በዚሁ ጥናት ውስጥ ተሰብስበው የሚገኙት መግለጫዊ መዘርዝሮች ባህል ማዕከላቱ ካከናወኗቸው ዝግጅቶች አንጻር መረጃውን ለማግኘት ባለመቻሉ ለናሙና ያህልየቀረቡ እንጂ እጅግ ዝቅተኛ መሆናቸውን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ይሄም ከመረጃ ውስንነት አንጻር የተፈጠረ ችግር መሆኑ እንዳለ ሆኖ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ሰፊ እና በስሩ ሊታቀፉ የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች የመኖራቸውን ያህል/ፊልም ፤ዲዛይን ፤ዳንስ ወዘተ / ሁሉንም በጥናቱ ለመመልከት አልተፈለገም፡፡ ስነ ስዕል ስነ ጽሑፍ እና ሙዚቃ ላይ ብቻ ለመወሰን ተገዷል፡፡

## 1.6 የጥናቱ አደረጃጀት

የፈረንሳይ ፤ የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ ላይ ያነጣጠረው ይህ ጥናት በሰባት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው ፡፡ በምዕራፍ አንድ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት÷ ዓላማ÷ አስፈላጊነት÷ የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴ ÷ የጥናቱ ገደብና አደረጃጀት ÷በጥናቱ ወቅት ያገጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎች እንዲሁም የጥናቱ ተጠቃሚዎች መካተታቸው ተገልፆአል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ደግሞ የንድፈ ሃሳብ ዳሰሳ ሲሆን የባህል ማዕከል ምንድን ነው÷ የባህል ማዕከላት ታሪካዊ ዳራ ÷ የባህል ማዕከላት ይዞታ÷ስለጥበቡ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡ በምዕራፍ ሶስት የፈረንሳይ የባህል ማዕከል ታሪክ ÷ የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ በፈረንሳይ ባህል ማዕከል÷ በስነ ስዕል÷ በስነ ጽሑፍና በሙዚቃ የቀረቡትን እያንዳንዳቸውን ለመመልከት ተሞክሯል፡፡ ምዕራፍ አራት የጀርመን የባህል ማዕከል ታሪክ ÷የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ በጀርመን ባህል ማዕከል÷ በስነ ስዕል÷ በስነ ጽሑፍና በሙዚቃ የቀረቡትን ዝግጅቶች ተመልክቷል ፡፡ በምዕራፍ አምስት የጣሊያን የባህል ማዕከል ታሪክ ÷ የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ በጣሊያን ባህል ማዕከል ÷ በስነ ስዕል÷ በስነ ጽሑፍና በሙዚቃ የቀረቡ ዝግጅቶችን ለመቃኘት ተችሏል፡፡ ምዕራፍ ስድስት የሶስቱ ባህል ማዕከላት የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ አንድነትና ልዩነት ተፈትሸዋል፡፡

ምዕራፍ ሰባት የጥናቱን ማጠቃለያና ይሁንታ የያዘ ሲሆን በመጨረሻም ከጥናቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው የተለያዩ ማስረጃ አባሪዎች ተካተዋል፡፡

## 1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

አንድ ጥናት ሲታሰብ አነስተኛና ጎላ ያሉ ችግሮች ሊገጥሙት እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ የፈረንሳይ፤ የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ ላይ ያተኮረውን ይሄን ጥናት ለማካሄድ ያጋጠመው መሰረታዊ ችግር ከአምሳ ዓመት በላይ ዕድሜን ባስቆጠሩት ባህል ማዕከላቱ የተጻፈና በአግባቡ የተያዘ መረጃ /document/አለማግኘቱ ነው፡፡ሶስቱ ሃያላን የአውሮፓ ሃገሮች መረጃን ያክል ነገር ሰንዶና መረጃን በአግባቡ ይዞ አለመገኘቱ ጥናቱን እጅግ አድካሚና በወቅቱ እንዳይደርስ በማድረጉ ቃለ መጠይቅን በስፋት እንዲጠቀም አጥኚውን አስገድዶታል፡፡ለአብነት ያህል በ1968 ዓ.ም.ሉዊጅ ፒራንዴሉ በሚል ርዕስ ስለጣሊያን ባህል ማዕከል የተጻፈ መረጃ እንዳለ ተገልጾልኝ፤ከጣሊያን ባህል ማዕከል ቤተ መጻህፍት መጽሀፉን ለማግኘት ይቅርና ስለሁለቱ አገሮች ግንኙነት የሚገልጽ በአማርኛም ሆነ በእንግሊዘኛ የተጻፈ መረጃ ለማግኘት አልተቻለም፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሚገኙ አብያተ መጻህፍት፤በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፤ በኬነዲ፤በጣሊያን ዩኒቲ፤በኢትዮጵያን ጥናት ተቋም ሊገኝ አልቻለም፡፡ ስለዚህም የተጻፈ መረጃ በጣሊያን ባህል ማዕከልና ኢምባሲ ዙሪያ ለማግኘት አልተቻለም፡፡ ባለሙያውም በቦታቸው ካለመገኘታቸው ጋር ተያይዞ መረጃ ለማግኘት ያልተቻለበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው፡፡

በሌላ በኩል የመጀመሪያ መረጃ ሰጪ ይሆኑኛል በማለት ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ለሶስቱም የባህል ማዕከላት ዳይሬክተሮች ቢሠጣቸውም የሰጡት ምላሽ አጥጋቢ አልነበረም ፡፡ ከጀርመን ባህል ማዕከል በስተቀር የጣሊያን ባህል ማዕከል የተጻፈ መረጃ ወይም መጽሄት የመሳሰሉትን አልሰጡኝም፡፡ የፈረንሳይም ቢሆን በኋላ ላይ በኢሜል ካደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ በስተቀር የተወሰኑ የተጻፉ መረጃዎችን በማግኘቴ ብቻ ነው ስራውን ለመስራት የቻልኩት፡፡ በመንግስታዊ ድርጅቶች በኩልም ተመሳሳይ ችግሮች ነበር ያጋጠሙኝ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ÷

የፌዴራል ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንዲሁም የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ስለባህል ማዕከላቱ እንቅስቃሴ ተጠይቀው መረጃ እንደሌላቸው በስልክ መልስ መስጠታቸውና አንዳንዶቹም በአካል « በዚህ ጉዳይ ላይ ክትትል አድርገንም አናውቅም» ማለታቸው የመረጃ አቀባዮችን ስፋትና አይነት እንዲሁም የመረጃ ስብጥሩን ውስን እንዲሆን አድርጎታል::

ከዚህም ሌላ አንዳንድ የጥበቡ ታዳሚዎች ና የጥበቡ ባለሙያዎችን አድራሻ ከመፈለግ አንስቶ መረጃ ለማግኘት በተደረገው ጥረት ለበርካታ ቀናትና እጅግም ለበርካታ ጊዜ ስልክ በመደወል÷ለከፍተኛ የትራንስፖርት ወጪና አታካች መለማመጥም በአጥኚው ላይ እንደደረሰበት ያነጋገራቸውን መረጃ አቀባዮች በመመልከት መረዳት ይቻላል::

በመጨረሻም ከባህል ማዕከላቱ ያልተገኙ መረጃዎችን በአዲስ አበባ መገናኛ ብዙሃን ቴሌቪዥን ጣቢያ በኪነ ጥበባት ፕሮግራም የተላለፉትን የሶስት አመታት መረጃ ለማግኘት፤ በራሳቸው ስቱድዮ መስማትና ትራንስክራይብ ማድረጉ አስቸጋሪ ስራ ነው:: ብዙውን ጊዜ ስቱድዮች እንዳይያዙ ፕሮግራም አቅራቢዎች በሚቀንሱበት ሰዓት እየተጠበቀ የማታ ሰዓት ና እሁድ ከ 10 ሰዓት እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት እያመሹ ፊልሞችን ለማጥናት መሞከሩ ሥራውን አድካሚ አድርጎታል ::በተጨማሪም ለሁለተኛ ጊዜ በተደረገ ፊልሞችን የመፈለግ ሂደት አንዳንዶቹ ክሮች የመጥፋታና ሌላ ፕሮግራም ተቀድቶባቸው በመገኘቱ የመደምሰስ አደጋ እንደተጋረጠባቸው ይታመናል::

አጥኚው እነዚህን ችግሮች ለማቃለል አስፈላጊውን ጥረት አድርጓል:: የመጀመሪያዎቹ ችግሮች ጥናቱን እስከማቆም ደረጃ አድርሰውት የነበረ ሲሆን /ካለዶክመንት መረጃ መስራቱ/ ሌሎቹ የመረጃ አቀባዮችን ችግር ሰው በሰው በማስቸገርና በመለመን መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል:: በአዲስ አበባ ከተማ መገናኛ ብዙሃን ቴሌቪዥን በኩል የቢሮ ሃላፊዎችን ÷ የኪነ ጥበባት ፕሮግራም አዘጋጆች እንዲሁም የኦዲዮቪዝዋል ባለሙያዎች ያደረጉት ትብብር አበረታቶት ጅምሩን ለመቋጨት በቅቷል ::

## 1.8.የጥናቱ ተጠቃሚዎች

የዚህ ጥናት ዋና ተጠቃሚዎች መንግስት፤ ኢምባሲዎች፤ባህል ማዕከላት፤ በባህል ዙሪያ የሚሰሩና የሚመለከታቸው አካላት ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት በዚህ ጥናት የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴና በሃገሮች መካከል የባህል ልውውጥ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመረዳትና ለጥበቡ እድገት መንግስታዊ ድርጅቶችም ሆኑ የኪነ ጥበቡ አፍቃሪያንና ባለቤቶቹ ጥበቃና እንክብካቤ ለማድረግ እንደ ማነሳሻ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ የባህል ማዕከላቱ እስካሁን ያካሄዱትን የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ምን አይነት ውጤት እንዳገኙበት ጠቋሚ መረጃ ሰጪ በመሆን ሊያገለግላቸው የሚችል በመሆኑ ፤ያለውን ክፍተት ተመልክተው ማስተካከያዎችን ለማድረግ ሊጠቀሙበት ይችላሉ ፡፡ ከእነዚህ ተጠቃሚዎች በተጨማሪ በዋናነት የፎክሎር፣ የስነ ጽሑፍ ፤የታሪክ፣ የባህል፣ የስነ ሰብ፣ የሙዚቃ፤ የስነ ስዕል እና የዳንስ ጥበብ ተመራማሪዎች በጥናቱ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

## 2. የንድፈ ሃሳብ ዳሰሳ

በዚህ ክፍል ውስጥ የንድፈ ሃሳብ ዳሰሳን እናገኛለን ። ከጥናቱ ጋር ዝምድና ያላቸው ተዛማጅ ስራዎች ግን ፤በተለይም ኪነ ጥበብን እንደዋና ርዕስነት ያነሱ የምርምር ስራዎች ባለማግኘቴ በትሁት ገለጻ ፤ይህ ጥናት ቀዳሚ ስራ ሊሆን ይችል ይሆናል የሚል ግምት አለኝ። በንድፈ ሐሳብ ዳሰሳ ግን የተለያዩ ምሁራን በባህል ማዕከላት ምንነትና በኪነ ጥበብ ዙሪያ ያነሷቸውን ሃሳቦችን እንመለከታለን ።

በዚህ ክፍል ስር ሶስት ንዑሳን ርዕሶች አሉ። እነዚህም የባህል ማዕከል ምንድን ነው? ኪነ ጥበብ ምንድን ነው? ጥበብና ባህል ያላቸው ተዛምዶ ምን ይመስላል? የሚሉ ናቸው። ሶስቱንም እንደቀደም ተከተላቸው አንድ በአንድ ተዳሰዋል።

## 2.1. የባህል ማዕከል ምንድን ነው?

የባህል ማዕከል ባህልና ሥነ-ጥበብን ለማስተዋወቅና ለመጪው ትውልድ ለማሳየት የሚያስችል ተቋም ነው። የባህል ማዕከላት መንፈሳዊና ቁሳዊ ባህሎችን በየፈርጁ አደራጅተው ለእይታ የሚያበቁ ሲሆን ህብረተሰቡ የሚሳተፍበትና ማንነቱን የሚገልጽበት የጥበብ መድረክ ነው ። ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ (2009፤136)" cultural center is an organization building or complex that promotes Culture and Arts"( ባህል ማዕከል ባህልና ኪነ ጥበብ የሚተዋወቁበት ህንጻ ወይም ከፍ ያለ ማዕከል ነው)

በማለት ይበይነዋልና።

የባህል ማዕከላት የቁሳዊና መንፈሳዊ ባህሎች መገኛ እንደሆነ ጠቅሰናል። በባህል ማዕከላት ውስጥ የሰው ልጅ የእጅ ስራ ውጤቶችና የተፈጥሮ ቅርሶች ለእይታ የመቅረባቸውን ያህል መንፈሳዊ ሃብቶችም(የፈጠራ) ጥበባዊ በሆነ መልኩ ለመድረክ ይበቃሉ። ይህንን በተመለከተ Levari,Norma.(1968፤105) የባህል ማዕከላት የሚከተሉትን ሶስት መሰረታዊ ተግባራትን ያከናውናሉ።

- Excellence teats in fine Arts and humanities, also Known as high culture.

- An integrated Pattern oh human knowledge that depends upon the capacity fur symbolic thought and special learning.

- The set of shared attitudes, values, goals and practices that characterize institution,organization or group.

Levari,እንደሚለው የባህል ማዕከላት የሰው ልጅ የማንነት መግለጫ የሆኑ የሥነ-ጥበብ ውጤቶች የሚቀርቡት ዕውቀቱን፤እምነቱንና ባህሪውን ባለው ችሎታ የሚገልጽበትና ለሌሎች ለማስተላለፍ የሚያስችለውን መድረክ መሰረት በማድረግ የሚንቀሳቀስበት ተቋም ነው።

የባህል ማዕከላት የማህበረሰብን ባህሎችን ለማሳየት ከሚቋቋሙ የሥነ-ጥበብ ተቋማት(Community Art Centers)ጋር ጥብቅ ቅርኝት አላቸው። እነዚህ ማዕከላት በርካታ ሰዎች የሚሰባሰቡበትና ሥነ-ጥበባዊ ትርኢቶችን በማቅረብና በማዝናናት ብቻ ሳይወሰኑ ታሪካዊ ቅርሶችን መዝግበው ለመጪው ትውልድ በማተላለፍም ይታወቃሉ።

## 2.1.1. የባህል ማዕከላት ታሪካዊ ዳራ

የባህል ማዕከላትን የማቋቋምና ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ለህብረተሰቡ የማቅረብ ሀሳቡ የተጠነሰሰው በ18ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያና በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በምዕራብ አውሮፓ ነው።Marshall(1994፤161) እንደሚለው የባህል ማዕከል ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ጀምሮ የሰው ልጅን አዕምሮ በእውቀት ለማበልጸግ የሚያግዙ የፈጠራ ውጤቶችን የሚያቀርቡበት ተቋም ለማድረግ መመስረታቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜም እተስፋፉ መምጣታቸውን ይገልጻል።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የምዕራብ አውሮፓ ሃገራት የራሳቸውን ባህልና ቋንቋ በሌሎች ሀገራት ህዝቦች ውስጥ እንዲሰርጽ ለማድረግ እንደ አይነተኛ መሳሪያ ተጠቅመውበታል።Pierre Bourdieu(1973፤205)ሀገራቱ በተለይም ቅኝ በገዟቸው የአውሮፓ ሀገራት ማእከላቱን በማቋቋም ህብረተሰቡ እየተዝናና የምዕራባዊያንን ባህልና ቋንቋ የሚለምድበትና የሚቀስምበት መድረክ እንዲሆን ሠርተዋል።

የባህል ማዕከላት መሰረታዊ ዓላማዎች በህዝቦች መሃል ማህበራዊ መስተጋብር እንዲፈጠርና በዚያም ሳቢያ የባህል ልውውጥ እንዲኖር ማስቻል ቢሆንም የባህል ማዕከላት የተለያዩ ግቦችን ለማሳካት በሚል የተለየ ፍላጎት ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አማካይነት ሊቋቋሙ ይችላሉ Bourdieu(1973፤206) ከነዚህም መሀል የክርስቲያኖች የባህል ማዕከል(Christian Cultural Center) የሙስሊሞች የባህል ማዕከል(Islamic Cultural Center)የአይሁዶች ባህል ማዕከል(Jewish Cultural Center)ወዘተ የየማህበረሰቦችን ሃይማኖታዊ እሴቶችና ባህል ለማስተዋወቅ የሚቋቋሙ ናቸው።

የባህል ማዕከላት የተጠነሰሱት በምዕራብ አውሮፓ ሀገራት ቢሆንም የባህል ማዕከላትን ከትምህርት ቤት ጀምሮ በማቋቋም ሃሳቡ መሰረት እንዲይዝ በማድረግ በኩል ቀዳሚዋ አሜሪካን ነች(Edward J ward 1997:266)።በአሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሰረተው የተማሪዎች የባህል ማዕከል እ.ኤ.አ.በ1907 ሲሆን የተከፈተው በኒዮርክ ነው።

እ.ኤ.አ. በ1916 በአሜሪካ National Community Center Association ከተቋቋመ በኋላ በየት/ቤቶች የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ማሳያ ማዕከላት በብዛት ተከፍተዋል። እ.ኤ.አ.በ1930 በአሜሪካ ት/ቤቶች ከ500 በላይ የተማሪዎች የባህል ማእከላት ሲቋቋም ከ4 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች በቋሚነት ትርኢቶችን በማቅረብና በመመልከት ተሳታፊዎች ነበሩ። በእንግሊዝ የመጀመሪያው የባህል ማእከል የተቋቋመው በ1926 በ Leicestershire ከተማ ነው። በጡረተኛው የሥነ ጥበብ ሰው Charles Booth(1867-1926) የተቋቋመው የባህል ማዕከል ከሥራ በኋላ በልዩ ልዩ ተሰጥኦዎች ሰዎችን ማዝናናት ለሚፈልጉ ግለሰቦች የተከፈተ ነበር።

## 2.1.2. የባህል ማዕከላት ይዞታ

የባህል ማዕከላት በየሃገራቱ የተለያዩ አካላት ይዞታ ስር ነው የሚገኙት። በአንዳንድ ሀገራት የባህል ማዕከላት የማቋቋምና የማስተዳደር ሃላፊነቱ የመንግስታቱ ሲሆኑ፤ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው፤በባህል ሚኒስቴራቸውና በኢምባሲዎቻቸው አማካኝነት ተግባራዊ ያደርጋሉ ። በአገራችን የሚገኙ የኢምባሲዎች ባህል ማዕከላት ለዚህ ገለጻ ዋቢዎች ናቸው ። በሌሎች ሀገራት ደግሞ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰቦች፤ሙያተኞችና ሲቪል ማህበራት በትብብር ሲመሰርቱት ይታያል።

የባህል ማዕከላት በመንግስታት በሚቋቋሙበት ወቅት የተለየ ግልጽ ዓላማ ተቀምጦላቸው ህብረተሰቡን ከማዝናናት በተጨማሪ የቋንቋና የባህል ማስፋፊያ መድረኮች ሆነው ያገለግላሉ። መንግስታቱ በባህል ማዕከላት አማካይነት ሊተላለፉ የሚችሉ የፈጠራ ውጤቶቻችን ላይ ገደብ ባያደርጉም በተለይ የሥነ-ጥበብ ዘርፎች ላይ ብቻ በማተኮር (ቴአትር፣ ሙዚቃ፣ ስዕል፣ ስነጽሑፍ፣ ቅርጻ ቅርፆች፣ ዲዛይን፣ ዳንስ፣ የፎቶግራፍ፣ ልዩ ልዩ ጌጣጌጦች፣ የፋሽን፣ ልዩ ልዩ ህዝባዊ ውይይቶችንና አሳታፊ ኪነ ጥበባዊ ጉዳዮች፣ ፊልም...ወዘተ) የበጀትና የሙያተኛ ድጋፍ ያደርጋሉ።

በሙያ ማህበራት፣በግለሰቦችና በሲቪል ማህበራት የሚቋቋሙ የባህል ማዕከላት ባህሎቻቸውንና የሥነ-ጥበብ ውጤታቸውን የማስተዋወቂያ ማእከል አድርገው ከመጠቀማቸውም በላይ የመዝናኛ መድረክ አድርገው ይገለገሉበታል።እንደ ቱሪዝም መስህብም የሚጠቀሙበት አካላትም አሉ።

## 3. የፈረንሳይ ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ

ከአውሮፖ ሃያላን ሃገሮች ፈረንሳይ አንዷ ነች:: የአውሮፖ ሃገሮች የአፍሪካና እስያ ሃገሮችን በቅኝ ግዛት በሚቀራመቱበት የ19ኛው ክፍለ ዘመን ፈረንሳይ ከእንግሊዝ ቀጥሎ በርካታ ሃገሮችን በመያዝ ትታወቃለች:: በዚህ አይነቱ ታሪካዊ ክስተትም ሆነ በሁለትዮሽ ግንኙነት መርሆ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት ከጀመረች ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ 104 ዓመታት እድሜ አስቆጥሯል:: በ1899 ዓ. ም ጀምሮ ሁለቱ አገሮች ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንደመሰረቱ የታሪክ መዛግብት ያመለክታሉ::[3] የሁለቱ አገሮች ግንኙነትም የምድር ባቡር ትራንስፖርትን ከጅቡቲ አዲስ አበባ በመዘርጋትና በዚህ የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ግንባታም የድሬድዋ ከተማን ለመቆርቆር፤ የአሊያንስ ፍራንሲስ አዲስ አበባ እና የአሊያንስ ፍራንሲስ ድሬድዋ ለማቋቋም ተችሏል (አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሔት 1990 ዓ.ም.):: ሁለቱ ባህል ማዕከላት አሊያንስ ኢትዮ-ፍራንሲስ የሚለውን የወል ስም የሚጠሩበት ነው :: በዚህ የመቶ ዓመት ታሪክ ውስጥ ከ50 ዓመት በፊት እ.ኤ.አ.በ1960 የባህል ማዕከል መመስረቱን ይነገራል :: ይህንኑ ታሪካዊ ሁነት የባህል ማዕከል ግንባታውን ና የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴውን ቀጥሎ እንቃኛለን ( ዝክ ቢሮ፤1989) ::

### 3.1 የፈረንሳይ ባህል ማዕከል ታሪክ

የፈረንሳይና የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የተጀመረው ህዳር 3 ቀን 1899 ዓ.ም የፈረንሳይ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት (ፍሊክስ ፎር ) ለአፄ ምኒልክ በፃፉት ደብዳቤ ነበር:: በደብዳቤውም በፈረንሳይና በኢትዮጵያ መካከል ለሚደረገው የሁለቱን ሃገሮች ሉዓላዊነት የጠበቀ ወዳጅነት አመቺ ሁኔታዎችን ለማረጋገጥና ለማጥናት ሙሴ ሊዮንስ ሌርድ ኃላፊነት እንደተሰጠው ተገልጾአል:: ኤምባሲውም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ መቀመጫውን በማድረግ ስራውን ጀምሯል::

አልያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ (የፈረንሳይ ባህል ማዕከል) ከመመሥረቱ በፊት ስራውን የጀመረው በ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር:: ይህንን ታሪክ ዲኒ ዜሪር ሰኔ 1989 ዓ.ም በወጣው የአሊያንስ መፅሔት ቁጥር 7 ላይ እናገኛዋለን ::

> የአዲስ አበባን ፍራንኮ ኢትዮጵያን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመስረት ወንድም ፌሊክስ ዳኖል (ቅዱስ ገብርኤል አዲስ አበባ የገቡት በ1900 ዓ.ም በጥቅምት ወር ነበር:: ከተመሰረተ በኋላም ምንም እንኳን

---

[3] -በኢቲቪ.2 /አዲስ ቴሌቪዥን " ጥበብ " ፕሮግራም ላይ በ28/7/2000/ የተላለፈው ዝግጅት መግቢያ ላይም ተመሳሳይ ገለጻ አግኝቻለሁ::

ትምህርት ቤቱ በቅዱስ ገብርኤል ወንድሞች ይተዳደር የነበረ ቢሆንም በአልያንስ ፍራንሲስ ኮሚቴ ስር ሆኖ ነበር ስራውን የጀመረው (አሊያንስ መፅሔት 1989÷ቁ7)

የተቋሙ አመሠራረትም ብዙዎቹ የአውሮፖ ሃገሮች (እንግሊዝ፣ጀርመን እና ፈረንሳይ) ይከተሉት ከነበረው የቋንቋና የባሕል ሽግግር ጋር የተያያዘ ነበር:: አልያንስም የፈረንሳይኛን ቋንቋ በቅኝ ግዛት ሃገሮች ብሎም በሌሎች ልዑአላዊ ሀገሮች ከማስፋፋት አንጻር ኢትዮጵያውያንና የውጭ ሀገር ዜጎች የሆኑ ወንድ ተማሪዎችን ለማስተማር ሥራውን «ሀ» ብሎ ጀምሯል::

ትምህርት ቤቱ ስራ ሲጀምር ሃይማኖታዊ በሆኑት መምህር አባቶችና ሃይማኖታዊ ባልነበሩት የሥራ ኮሚቴው አባላት መካከል አልፎ አልፎ አለመግባባቶች ይከሰቱ ነበር:: በዚህም ምክንያት የቅዱስ ገብርኤል ወንድሞች የቄስ ልብሣቸውን እንዲያወልቁ ፣መንፈሳዊ ትምህርት እንዳይሰጡና የስቅለት ምስል በመማሪያ ክፍሎቻቸው እንዳያሳዩ በጥብቅ ተከለከሉ:: ህዳር 1900 ዓ.ም ወንድም ፍሊክስ ዶኖል ለትምህርት ቤቱ እንደ መምህርም እንደ ርዕሰ መምህርም በመሆን ማስተማር ጀምረዋል (የአሊያንስ ኢትዮ- ፍራንሲዝ 2000 ዓ.ም የመቶኛ ዓመት ክብረ በዓል የወጣ መፅሔት ገፅ 12)::

በዚህ ሁኔታ የተጀመረው ትምህርት የሚሰጠው የዳይሬክተሩ መኖሪያና መማሪያ ክፍል በሆነች አንድ ጠባብ ጎጆ ውስጥ ነበር:: ወንበር፣ ጠረጴዛና ደብተር የሚባል ነገር ባይኖርም 12 ተማሪዎች መሬት ላይ በተነጠፈ ድብዳብ ላይ ተቀምጠው ይማሩ ነበር:: የመማር ማስተማሩን ስራ የሚያግዙት፤ መፅሐፍትና እንደጥቁር ሰሌዳ የሚያገለግለው ሰራተኛ ብቻ ነበሩ:: ዲኒ ዘሪር ይህን ጊዜ የገለፁት እንዲህ በማለት ነበር::

> .....ከትንሽ ጊዜ በኋላ ትምህርት ቤቱ ስልሳ ስምንት ተማሪዎች ተመዘገቡ:: በኋላም አንድ ሄክታር ያህል የሚሆነውና አሁንም ድረስ በዋብል ስትሪት (Wable street) የሚገኘው የአልያንስ መሬት ነሐሴ 1904 ዓ.ም በአልያንስ ኮሚቴ ተገዛ:: በሚያዚያ 1905 ዓ.ም ከአምስት ተከታታይ የቦታ ለውጦች በኋላ የዛሬዎቹ ሁለት መምህራኖች ፊሊክስ ዶኖልና በርናርዲን ዲሲየን 100 የሚደርሱ ተማሪዎችን ይዘው ባላለቀው ህንፃ ስር ጀመሩ:: የአልያንስ የፈረንሳይ ት/ቤት በዚያው ጊዜ ተመርቆ ተከፈተ (1990÷16)::

ተቋሙ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ውጣ ውረዶችን እያለፈ እንደመጣ ሌሎች መረጃዎችም ያመለክታሉ፡፡ በ1934 ዓ.ም አልያንስ ከመንፈሳዊ ትምህርት ቤትነት ወደ ዓለማዊ ትምህርት ቤትነት በመሸጋገር ለሁለት ዓመታት ለተወሰኑ የግሪክና የአርመን ተወላጆች ላጋርድ የተሰኘ ትምህርት መስጠት ጀምሯል፡፡ በ1941 ዓ.ም ሊሴ ገ/ማርያም ከሐይማኖት ትምህርት ውጭ በሆነ የፈረንሳይ ተልዕኮ ሲመሠረትም በተወሳሰቡ ችግሮች ላይ ወድቆ ነበር፡፡

በጊዜ ሂደት በ1953 ዓ.ም ተቋሙ ለተወሰነ ጊዜ እንደ ቴክኒክ ትምህርት ቤት ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በሊሴ ገ/ማርያም ሞግዚትነት ይተዳደር እንደነበረም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በጊዜ ሂደት እንዴት የባህልና የኪነ ጥበብ ማዕከል ወደመሆን ተቀየረ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጠው የፈረንሳዊው ሻርሊ ጆሊሽ ፅሑፍ ነው፡፡

> በ1949ዓ.ም ከተካሔደው አጠቃላይ ጉባዔ በኋላ ኮሚቴው በየዓመቱ በአጠቃላይ ጉባዔ አባላት የሚመረጥበት ሁኔታ አልያንስ ትክክለኛ ማህበር ሆነ፡፡ በ1960 ዓ.ም አልያንስ ቀስ በቀስ ወደ ባሕል ልውውጥ ተግባሩ እያደላ መጣ፡፡ ለዚህም ተግባር ይውል ዘንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፈረንሳይ የተላከው የገንዘብ ድጎማ የዋለው አንድ የሲኒማ ክበብና የህፃናት መፃሕፍት ቤት ለማቋቋም ነበር (ሻርሊ ጆሊሺ አሊያንስ መጽሄት፤1990፤7 /

አሊያንስ በቀንና በማታ ትምህርት ከሚያስተምራቸው የቋንቋ ትምህርቶች በተጨማሪ የፈረንሳይን ባህል በሰፊው ማሰራጨት ጀመረ፡፡ በመሆኑም በ1968 ዓ.ም የፈረንሳይ ሲኒማ ሳምንት፤ በ1970 ዓ.ም ደግሞ የአውሮፓ ፊልም የተሰኙ ፕሮግራሞችን ነድፎ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡በ1973 ዓ.ም ደግሞ የስዕል ኤግዚቢሽኖችን ማሳየት ጀመረ (ታዬ ታደሰ፤91) ፡፡

ወ/ሮ መርሴማ ታሪኩ እ.ኤ.አ. ከ1999 እስከ 2009 ድረስ የባህል ማዕከሉ የህዝብ ግንኙነት ኦፊሰርና የኪነ ጥበባት ዝግጅቶች አስተባባሪ በመሆን አገልግለዋል፡፡ ስለ አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የባህል ማዕከል የተቋቋመበትን ዓላማ አስመልክቶ ሲያብራሩ፤

---

> የኢሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የተመሰረተበት ዋና ዓለማው የሁለትዮሽ ግንኙነቱን በፈረንሳይና በኢትዮጵያ መካከል

> ማጠናከር ሲሆን፤ይህንኑ ጉዳይ ለማስፈጸምም በዋናነት የፈረንሳይኛ ቋንቋ ኮርስን መስጠት እና በሁለተኛ ደረጃ ባህላዊ የኪነ ጥበብ ልውውጥ በማድረግ ባህልን መጠበቅና ማስፋፋት ነው (ወ/ሮ መርሴማ ታሪኩ 5/10/03 ዓ.ም.) ፡፡

በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር የነበሩት አምባሳደር ስቲፋን ጎምፔርትዝ በአሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሄት ላይ የወ/ሮ መርሴማን አስተያየት የሚያጠናክር አመለካከታቸውን አስፍረዋል፡፡

> በኢትዮጵያና በፈረንሳይ ሀገራት መካከል ቋሚ የሆነ የአስተሳሰብ ልውውጥ እንዲኖር፤በሁለቱም ሀገራት ህዝቦች መካከል የባህል ውይይት መድረክ እንዲከፈትና የሁለቱንም ሀገራት ህዝቦች በልብና በመንፈስ እንዲቀራረቡ የማድረግ ራዕዮች ያቀፈ ማዕከል ነው(አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሔት፤1990 ዓ.ም )፡፡

የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ለማጠናከርና የባህል ልውውጥ ለማድረግ ዋነኛ ዓላማው አድርጎ የተቋቋመው ባህል ማዕከል ዓላማውን በአግባቡ አሳክቶት ይሆን ? በቀጣዩ ጽሑፍ እንመለከተዋለን፡፡

## 3.2 ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ

የፈረንሳይ ባህል ማዕከላት በመላው ዓለም በ136 አገሮች ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በአፍሪካ በ38 አገሮች ማዕከላቱ ይገኛሉ( መርሴማ ታሪኩ፤5/10/03 ዓ.ም ) ፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኘው ባህል ማዕከል ምን አይነት ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴዎችን አካሂዷል ፡፡ ባህል ማዕከሉ በባህልና ኪነ ጥበብ እንቅስቃሴው ላይ ያሳለፈውን ታሪካዊ ሂደት በተመለከተ ሲያብራሩ፤

> አሊያንስ የሚያቀርበው ዝግጅት ከፊልም ዝግጅቶች አንስቶ፤ቲያትሮችን ለምሳሌ ንግስተ ሳባን፤ የስዕል፤ የሙዚቃ፤ የዲዛይን፤ የፋሽን፤ የዳንስ፤ የስነ ጽሑፍ፤ የሽክላ ስራ፤የቅርጻ ቅርጽ የመሳሰሉት ላይ በስፋት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በሳምንትና በሁለት ሳምንት

ውስጥ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማካሄድ በአማካይ በዓመት እስከ 200 የሚደርስ የተለያዩ ኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ይካሄዳሉ (መርሴማ ታሪኩ፤5/10/03)፡፡

የአሁኑ የፈረንሣይ ኢምባሲ ጉዳይ አስፈፃሚ አቶ አስፋው ሳለሁ በባህል ማዕከሉ የረጅም ጊዜ ትውውቅ ያላቸው በመሆኑ በባህል ማዕከሉ የሚቀርቡት የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን በተመለከተ የሚከተለውን ይገልጻሉ፡፡

> በ1978 ዓ.ም አልያንስ ያዘጋጅ የነበረው የፊልም ሣምንት በደረጃው ከፍ ብሎ 3 የፈረንሳይ ፊልሞችን በፕሮግራሙ ያካተተ የአውሮፖ ፊልም ፌስቲቫል ነበር፡፡ በተጨማሪም በሌሎች የኪነ ጥበብ ዘርፍ በሰፊው በመንቀሳቀስ አልያንስ በሙዚቃውም ሆነ በቲያትሩ ዓለም ከፍተኛ እንቅስቃሴዎችን ጀመረ (አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሔት፤1990 ዓ.ም.)፡፡

የተለያዩ ዝግጅቶችን ለተመልካች በማቅረብ በአገራችን ከሚገኙ የባህል ማዕከላት በቀዳሚነት የሚገኘው ይህ የባህል ማዕከል ፤ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን በማሰናዳት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኪነ ጥበብ ታዳሚን ለማዝናናት፤ለማስተማርና የባህል ልውውጥ ለማድረግ ችሏል ፡፡ የባህል ማዕከሉ እንደ ዓላማ ያነገበው አሊያንስ በባሌ ዳንስ፣ በዘመናዊ ዳንስ፣ በሰርከስ÷ በውይይት መድረኮች÷ በአዝማሪ ምሽቶች÷ በፋሽን ዝግጅት÷ በቲዓትር ÷ በሙዚቃ እና በስዕል በስፋት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ ከሁሉም እንደዋና ስራ አድርጎ የያዘውና ከፍተኛ የማስተዋወቅ ስራን የሚሰራው የሙዚቃና የስዕል ኢግዚቪሽኖችን በማዘጋጀት ነው፡፡ ወ/ሮ መርሴማ እንደምትገልጸው ‹‹ የአሊያንስ የስዕል ጋለሪ ዝነኛ እና ከወጣት እስከ አንጋፋ የስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ባለሙያዎች የሚያቀርቡበት በከተማዋ ተመራጭ ጋለሪ ነው ፡፡ ››

አቶ አስፋውም የወ/ሮ መርሴማ ሃሳብን ያጠናክራሉ፤ ‹‹የአሊያንስ ጋለሪ በአዲስ አበባ ቀደምት ከሚባሉት አንዱና እጅግ ታታሪ በመሆኑ በብዛትና በጥራት የማይተናነስ ሁሉን አይነት ስነ ጥበብ ለእይታ በማብቃት ላይ ይገኛል» ይላሉ፡፡

የባህል ማዕከሉ የስዕል ማሳያ ጋለሪ በከተማዋ ከሚገኙ ጋለሪዎች በላቀ ደረጃ ተመራጭ ነው፡፡ይህም በመሆኑ በርካታ የስዕል ስራዎች የሚቀርቡበት ቦታ ለመሆን ችሏል ፡፡ የባህል ማዕከሉ በዋናነት የፈረንሳይን ኪነ ጥበብና ባህል የማስተዋወቅ አላማ

ቢኖረውም ፤ ወደ ኢትዮጵያ ኪነ ጥበብና ባህል የማስተዋወቅና የማሳደግ ስራዎች እንደሚያመዝን ይገልጻሉ። ታዳጊና ባለተሰጥዖ ወጣቶችን ለዕውቅናና ከፍተኛ ዝና ማድረሱን የባህል ማዕከሉ በኩራት የሚናገረው ተግባሩ ነው ።

የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴው በስነ ስዕልና ቅርፃ ቅርፅ ጋለሪ፣ በሙዚቃና ትያትር መድረኮች፣በፊልም ስክሪኖችና በስነ ፅሑፍ የውይይት መድረኩ ጥበባዊ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ የሚገኘው የያኔው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፡ የአሁኑ የቋንቋ ትምህርት ቤት እና የባህል ማዕከልን አጠቃላይ ገፅታ በየፈርጁ እንመለከታለን።ስለቋንቋ ትምህርቱ ከርዕስ ጉዳያችን ስለሚያስወጣን እንጂ በዓመት ከ3ሺህ 500 በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ የሚያስተምር ትምህርት ቤትነቱን ጠቅሰን ማለፋችን አይቀርም[4] ። እነዚሁ ተማሪዎች የኪነ ጥበቡ ዝግጅት ቀዳሚ ታዳሚዎች ናቸውና።

## 3.2.1 ስነ ስዕል

በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ከሚቀርቡት የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች በቀዳሚነት የምናገኘው የስዕል ጥበብን ነው። ከስዕሉ በመቀጠልም ሙዚቃውን። እዚህ ላይ መነሳት ካለበት ምክንያቱ ምን ይሆን የሚለው ይሆናል። በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ በሚቀርቡ የኪነ ጥበባት ዝግጅቶች ከሚታደሙት መካካል ቀዳሚውን የሚይዙት በአዲስ አበባ ተቀማጭ የሆኑ የውጪ አገር ዲፕሎማቶች ሲሆን ከእነርሱ በመቀጠልም በመደበኛ የህዝብ መዝናኛዎች ወይም አዳራሾች ሄደው መዝናናት የማይችሉ፤ለመኪናቸው ማቆሚያ ከማግኘት አንስቶ ለመዝናኛነት አመቺ በመሆኑ ይመርጡታል።

እነዚህ የኪነጥበብ ታዳሚዎች የዕይታ ጥበባት ላይ (ስዕል፤ሙዚቃ፤ፋሽን፤ፊልም ወዘተ)ያተኩራሉ። የስነ ጽሑፍ ጥበብ ግን ከቋንቋው ጋር እና ከመድረክ አጠቃቀሙ አንጻር ተመራጭ አይሆንም(ፋንታሁን ኬሪቦ፤እዝራ አባተ፤ዘሪሁን አስፋው)። በዚህ አስተያየት ላይ ተመሳሳይ አቋም አላቸው።

---

[4] ብዙዎቹ የአውሮፓ ሃገራት ባህላቸውን፣ቋንቋቸውንና ማንነታቸውን በሌላው ዓለም ለማስረጽ፣ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ከሚጠቀሙበት መንገድ አንዱ የቋንቋ ትምህርት ቤት ነው።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሃገሮች ሰዓልያን በዘመናዊው ዓለም ሊያገኙት የሚገባውን ክብርና ጥቅም እያገኙ ባይሆንም የጥበቡ ትልቅነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እውቅናን እያገኘ መጥቷል፡፡ ቀደም ሲል ግን የስዕል ስራዎች  አሉ ለማለት አያስደፍርም ነበር፡፡  ሰዓሊያን የስነ ጥበብ ማሳያ ስፍራዎች ካላገኙ ደግሞ «የጋን ውስጥ መብራት» መሆናቸው አይቀሬ ነው፡፡

> ቀደም ሲል የስዕል ማሳያ መድረኮች እጥረት በከተማዋ ነበር፡፡በርካታ የስዕል ባለሙያዎችም ያላቸውን የጥበቡ እውቀት ለአድናቂዎቻቸው ለማሳዬት ሲቸገሩ ቆይተዋል፡፡ ከ197ዎቹ አካባቢ የባህል ማዕከላት የስዕል ማሳያ ጋለሪዎችን ማዘጋጀታቸው፤እንደገናም በቅርቡ ደግሞ የግል ጋለሪዎች መስፋፋታቸው ለጥበቡ ማደግ አስተዋጽኦ ማድረግ ችለዋል፡፡(በቀለ መኮንን 8/10/03)

አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ የስዕል ኤግዚቢሽኖች የሚታይበት ስፍራ ሆነ፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አሊያንስ በስነ ስዕል የኪነ ጥበብ ዘርፍ ረገድ የባህል ማዕከሉ ያለውን አስተዋፅኦ የዘርፉ ባለሙያ ሰዓሊ ጌታቸው ዮሴፍ ይገልፃሉ፡፡

> አሊያንስ ኢትዮ-ፍራንሲስ እንደ ባህል ማዕከል ለዚህ ሃገር ሰዓልያን ብዙ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ለእኔም ሆነ ለተማሪዎቼ ያደረገልን ድጋፍ ከፍተኛ ነው፡፡ በአሊያንስ ጋለሪ ስራዎቼን ማሳየት የጀመርኩት ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን በመጀመሪያ ያቀረብኩት ሥራ «ከፀሐይ በታች» የተሰኘ ነበር፡፡ እስካአሁን በሙያ ህይወቴ ካቀረብኳቸው 15 የስዕል ኤግዚቢሽኖች  አስሩን ያቀረብኩት በዚሁ ማዕከል ነው (አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሔት፤1990ዓ.ም. ) ፡፡

ሰዓሊው የእርሳቸውን ጨምሮ የበርካታ የጥበብ ሰዎችን (ሰዓልያንን ) የፈጠራ ውጤቶች በማስተዋወቅ ረገድ አሊያንስ ትልቅ ሚና እንደነበረው ደጋግመው ያወሳሉ፡፡ በተለይም ባህል ማዕከሉ በኢትዮጵያውያን ፕሬዚዳንቶች መመራት ከጀመረ ወዲህ ለውጡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እድገት እያሣየ መጥቷል፡፡ ወ/ሮ መርሴማ ታሪኩ እና  አቶ በቀለ መኮንን  የአቶ ጌታቸው ዮሴፍ አስተያየትን ይጋራሉ፡፡

አርቲስት ዘሪሁን የትምጌታ የተባሉ መረጃ አቀባይ የስዕል ባለሙያ ላለፉት 40 ዓመታት አብዛኛዎቹን የስዕል ስራዎቻቸውን በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ጋለሪዎች ማሣየት እንደቻሉ ያስረዳሉ፡

> ከምንም በላይ ለጥበቡ ፤ተቋሙ ያደረገው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው ። አሊያንስ የወጣትና የአንጋፋ አርቲስቶች ሥራዎችን ለእይታ በማብቃቱ ኢትዮጵያውያን የስዕል ጥበብን በማድነቅ ለባለሙያዎቹ ዕውቅና መስጠትን እንዲያዳብሩ ከማድረጉም በላይ የእውቀት ሽግግርን እየፈጠረ ነው (አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሔት፤1990 ዓ.ም.) ።

በአሊያንስ የስዕል ጋለሪ (ኤግዚቢሽን) ለእይታ ክፍት የሚሆነው፣በተለያዩ ወቅቶች ነው፡፡ በአንድ በኩል ዓመታዊ በዓላት ሲዘጋጁ ሙያተኞች ተጋብዘው የፈጠራ ስራዎቻቸውን የሚያቀርቡ ሲሆን፤ በሌላ መልኩ በባለሙያዎቹ ጥያቄ በተለያዩ ጊዜያት የስዕል ስራዎችን ለህዝብ ያቀርባሉ፡፡ በአብዛኛው ግን አንድ የስዕል ዝግጅት ሲቀርብ ከአምስት እስከ አስራ አምስት ቀናት ለእይታ ክፍት ሆኖ ስለሚቆይና ወዲያዉኑ ሌላኛው የስዕል ኤግዚቢሽን ስለሚከተል በወር ውስጥ ሁለቱ ዝግጅቶች ስለሚይዙት አመቱን ሙሉ የስዕል ኤግዚቢሽን የሚታይ ያስመስለዋል (ሙሉ ዝርዝሩን ከመግለጫዊ መዘርዝሩ አባሪ አንድ ይመልከቱ) ።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ዝናን እያገኙ የመጡ ወጣት ሰዓሊያን አሁን ለደረሱበት የዕውቅና ደረጃ እንዲደርሱ የባህል ማዕከላቱ ሚና ላቅ ያለ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ወጣት ሰዓሊ ማርታ መንግስቱ ለእውቅና የበቃችው ሥራዎቿዋን ለመጀመሪያ ጊዜ በአሊያንስ ኢትዮ-ፍራንሲስ የሥዕል አዳራሽ ባቀረበችበት ማግስት ነበር፡፡

በቡድንም ሆነ በግል አሊያንስ ኢትዮ- ፍራንሲስ ባደረገቻቸው ኤግዚቢሽኖች ላይ ሁሌም ቀልብን መሳብ የምትችለው ይህች ሰዓሊ መድረኩን ያገኘችው ብሎም ከብዙ አድናቂዎቿ ጋር የተገናኘችው በዚሁ ሥፍራ መሆኑን ደጋግማ ትናገራለች፡፡ ከሶስት ዓመት በፊት በአሊያንስ የስዕል ስራዎቿን ካቀረበች ወዲህ በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ አገሮች አዘጋጅነት በዛምቢያ ዋና ከተማ በሉሳካ በተካሄደው የአፍሪካውያን የሥዕል ኤግዚቢሽን ላይ በአሊያንስ አማካኝነት ተሳትፎ ከነበራቸው ሰዓሊያን ውስጥ ምርጥ የሴት ሰዓሊ ተብላ ለመሸለም የበቃችው ማርታ፤ በአሁኑ

ወቅት በዓለም አቀፍ መድረክ አግኝታ አሜሪካን ሃገር በሜሪላንድ የስዕል ስራዎችዋን ለማቅረብ ችላለች( አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሔት፤1990 ዓ.ም) ፡፡

ወጣት አርቲስት ሰአሊ ዓብይ ጌድዮንም የባህል ማዕከሉ መድረኩን አመቻችቶለት ያለውን የጥበብ ፍቅርና ተሰጥኦ በማሳየት ከህዝብ ጋር የተገናኘበት መሆኑን ይናገራል፡፡

ሰአሊ ዓብይ ጌድዮን ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጽ፤

> በመጀመሪያ የተሳተፍኩት በዚሁ ስፍራ በተካሄዱ ሁለት የቡድን ኤግዚቢሽኖች ሲሆን፤ አንደኛው በሙዚቃ ርዕስ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የኪነ ጥበብ መንደር የተሰኘ ነበር፡፡በዚህም አጋጣሚ ከስነ ጥበብ ትምህርት ቤት ወዳጆቼ ጋር በጋራ ዝግጅት ማቅረብ በመቻሌና ስራዎቼም አደባባይ ስለወጡልኝ ደስታዬ ወደር እንዳልነበረው አስታውሳለሁ ይላል( አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሔት፤1990 ዓ.ም) ፡፡

አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ለወጣት ሰዓሊያንም ሆነ ለአንጋፋ ሰዓሊያን የማሳያ መድረኮችን በመመቻቸቱ እኔን ጨምሮ በመድረኩ ተጠቃሚ ለመሆን ችያለሁ፡፡ ከህዝብ ጋርም ለመገናኘት መድረኩን አመቻችተውልናል ››ሲል ሰዓሊና ቀራጺ በቀለ መኮንን አስረድቷል፡፡

በሌላ በኩል ግን የባለሙያዎችን ስራ ለማሳዬት በሚመረጥበት ወቅት ፍትሃዊ አሰራር እንደሌለ የሚገልጹ ባለሙያዎች መኖራቸውን ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኬሪቦ ይናገራል፡፡

> እኔ በዚሁ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ላይ በምከታተልበት ወቅትና በምዘግብበት ወቅት ከባለሙያዎች የሚሰማው እሮሮ የባለሙያዎችን ስራ ሲመርጡ ፍትሃዊ አለመሆኑን ነው፡፡ እንዲያውም እከሌ ጋር እግሩ ስር ካልወደኩ አልመረጥም የሚሉ ባለሙያዎች እንዳጋጠሙት አስረድቷል፡፡

የጋዜጠኛ ፋንታሁንን ሃሳብ ደራሲ ዳንኤል ወርቁና ሰዓሊ በቀለ መኮንን ቀደም ሲል ይህን መሰል ችግር እንደነበር ገልጸውታል(9/10/03)፡፡ ወ/ሮ መርሴማ

ታሪኩ ግን አሰራሩ ግልጽነት ያለውና ጥንቃቄ በታከለበት ምርጫው እንደሚካሄድ ሲገልጹ፤

> ምርጫው የሚካሄደው የፈጠራ ብቃት ያላቸውን ወጣቶች ስራ በማየትና በቀጣይ ተስፋ የሚጣልበት ወጣት ሰዓሊ መሆኑን ስንመለከት የስዕል ስራዎቹን በሲዲ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ እናደርጋለን፡፡ ወደ ስቱድዮው በመሄድ እንጎበኛለን፡፡ ወደ አዝማሪ ምሽት ዝግጅትም ስትመጣ በማታ ድንገተኛ ጉብኝት በማድረግ የሚያቀርቡትን ዝግጅት በመጎብኘትና በመገምገም ብቃት ያለው ስራና ተመራጭ ሆኖ ስናገኘው ብቻ ነው ወደ መድረክ የምንጋብዘው፡፡ በአዝማሪ ምሽት ላይ በሰራነው ውጤታማ ስራ እነፈንድቃን አዝማሪዎችን ተመልከት፡፡ ዛሬ ዝነኛ ሊሆኑ የቻሉት ጥንቃቄ ባለው መልኩ ስለመረጥን ነው፡፡ በአዝማሪ ላይ የነበረውን የተሳሳተ አመለካከት እንዴት እንደቀየርነው መመልከት ትችላለህ፡፡ እነርሱም በኩራት ሞያቸውን ወደውታል፡፡ ህዝቡም በፍቅር ከእነርሱ ዘንድ እየሄደ ይዝናናል(5/10/03)፡፡

አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የስዕል ኤግዚቢሽን ማሳየት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ላለፉት 30 ዓመታት በርካታ የስዕል ባለሙያዎች ሙያቸውን እንዲያሳድጉና ለከፍተኛ ዝና እንዲበቁ ከፍ ያለ እገዛ አድርጓል ፡፡ ከውጭ አገር ሳይቀር በርካታ ሰዓሊያን ስራዎቻቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ የስዕል ኪነ ጥበባዊ ዋጋ ከፍ ያለ መሆኑንና ማህበረሰቡም የዚህ ጥበብ ታዳሚ እንዲሆን በማድረግ በጥበቡ ዙሪያ የተሻለ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ እገዛ አድርጓል ፡፡

### 3.2.2 ስነ ፅሑፍ

በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የባሕል ማዕከል ለስነ ጽሑፍ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ምን አይነት ትኩረት ሰጥቶ ተንቀሳቅሷል ? ወይም ለስነ ጽሑፍ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ምን ያህል መድረክ አዘጋጅቶ የጥበብ ታዳሚዎችን አስተምሯል አልያም አዝናንቷል ? ወይም በሌላ ገለጻ በኢትዮጵያ ስነ ፅሑፍ ታሪክ ውስጥ ምን አይነት አስተዋፅኦ እያደረገ ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡

የስነጽሑፍ ዝግጅቶች እንደ እይታ ጥበባት ቋንቋውን ካልቻሉትና አይንን ያዝ አድርጎ የማቆየት አቅሙ ደካማ በመሆኑ በአሊያንስ በተካሔዱ ዝግጅቶች አነስተኛ ቁጥር ያለው መድረክ ያገኘ መሆንን ለመመልከት እንችላለን(ሙሉ ዝርዝሩን ከመግለጫው መዘርዝሩ አባሪ አንድ ላይ ይመልከቱ)::

ከዕይታ ጥበባት (ስዕል፤ፊልም፤ሙዚቃ፤ዳንስ፤ፋሽን ወዘተ) አንጻር በተለይም ለውጪ አገር ዜጎች የስነ ጽሑፍ ጥበብ ሊስባቸው እንደማይችል አቶ ዘሪሁን አስፋውና ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኬሪቦ ይስማሙበታል::ከላይ ደግሞ እንደተገለጸው የአሊያንስ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን በመከታተል ረገድ ቀዳሚውን ድርሻ የሚይዙት የውጪ ዜጎች በመሆናቸውና እምብዛም የማይከታተሉት ዝግጅት ነው ለማለት እንችላለን::

ያም ሆኖ ታዲያ አሊያንስ ስነ ጽሁፍን ከጃዝ ጋር በመቀላቀልና በማጀብ የተለዩ አቀራረብን የተከተለባቸው መድረኮችንም ለመፍጠር የቻለባቸውን መድረኮች ማንሳት እንችላለን:: በ2/4/01 ዓ.ም. ዶ/ር ፈቃደ አዘዘን ጨምሮ፤አበባው መላኩ፤ፍሬዘር ዘለቀ፤ምስራቅ ተረፈ ያቀረቡትን መድረክ ማንሳት ይቻላል::

ከዚህ ሌላ አሊያንስ በአንድ በኩል በፈረንሳይኛ ቋንቋ የሚቀርቡ የአውሮፖ ስነ ጽሑፎችንና የዕሕፈት ውጤቶችን ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በማስረፅ በኩል የተጫወተው ሚና ይጠቀሳል:: በሌላ በኩል የሀገር ውስጥ ወጣትና አንጋፋ ደራስያን ስራዎቻቸውን በባሕል ማዕከሉ በማቀረብ ለውይይትና ለሂስ የሚከፍተው በር ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው መሆኑን በስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ይነገራል::

የአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የባሕል ማዕከልን የስነ ፅሑፍ አስተያየት ከመጀመሪያው ጠቀሜታ አንፃር ከሚያስረዱት መካከል ፕሮፌሰር ብርሃኑ አበበ አንዱ ናቸው::በተቋሙ 100ኛ ዓመት የህትመት ውጤት ላይ በሰጡት አስተያየት፤

> ፈረንሳዮች ከሚገምቱት በላይ ፈረንሳይኛ ቋንቋ ለኢትዮጵያ ባህል ቋንቋና ስነ ፅሑፍ ብልጽግና የራሱን ሚና ተጫወቷል:: ቋንቋውን የተገነዘቡ ሰዎች አዳዲስ ሃሳቦችንና ጭብጦችን በስነ ፅሑፎች ታሪክና ቴክኒክን በመገንዘብ የስነጽሁፍ ባህል ሽግግር ስለመኖሩ መካድ አይቻልም:: ለዚህም ደግሞ ከግማሽ ምዕተ አመት ወዲህ በተፈጠረው ትውልድ ላይ የተንፀባረቀውን የፈረንሳይ ተፅዕኖ መገንዘብ ይቻላል(አልያንስ መጽሄት 100ኛ

ዓመት፣1990 ዓ.ም.)::

አሊያንስ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት ቤት ነው:: እስከ አሁንም ይህንኑ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል:: በእርግጥ ዛሬ በተለያዩ የግልና የመንግስት የትምህርትና የስራ ተቋማት የፈረንሳይኛ ቋንቋ በመስጠትና በመነጋገሪያነት እያገለገለ ነው:: በዚህም ምክንያት ፈረንሳይኛ ከእንግሊዘኛ ቀጥሎ በሃገሪቱ እየተለመደ የመጣ የአውሮፓ ቋንቋ በመሆን ላይ ነው:: በዚህ የቋንቋ ተሳትፎ ውስጥ የተተረጎሙ መጽሐፍት፣ ግጥሞችና ዘገባዎችም አሉ ፣ አስተያየት ሰጪው ፕሮፌሰር አበበ እንዳስረዱት::

ወጣት ደራሲያን በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የሥነ ጽሑፍ ምሽቶች ለአድማጮቻቸው የተለያዩ የግጥም ንባቦችን በማቅረብ መድረኩን ለመጠቀም ችለዋል:: መፃህፍቶቻቸውን አሳትመው ለማስመረቅና ለመወያየት የተሻለ መድረክ ተፈጥሮላቸዋል:: በእነዚህ ሞቅ ያሉ የሥነ ጽሑፍ ምሽት መድረኮች ከአድማጭ-ተመልካቾቻቸው ፊት ለፊት ቆመው የአድማጮቻቸውን የማድመጥ ስሜት እየለኩ ግጥሞቻቸውን አቅርበዋል:: ከእነዚህ ደራስያን መካከል ወጣት ደራሲ አበባው መላኩ እንደገለጸው፣

> የአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የባህል ማዕከል በሚያዘጋጃቸው የሥነ ጽሑፍ ምሽት የግጥም ዝግጅቶችን በማቅረብ ዓይናችንን የገለጥንበት መድረክ ነው:: የባህል ማዕከሉ ፊት ለፊት በቅርበት እየተያየህ የምታቀርብበት መድረክ ስለሆነ የግጥሞቻችን ይዘት ከፍ ባለ ጭብጨባና ሞቅ ያለውን ድጋፍ ለመመልከት ያስችላል:: የታዳሚውንም አቀባበል ለመመልከት ያስችላል:: በአሊያንስ መድረክ ጽሑፎችን ባናቀርብ ኖሮ ተደፋፍረን መጽሃፍቶችን ለማሳተምና ታዋቂነትን ለማግኘት አንደርስም ነበር (አበባው መላኩ፣ 18/8/2001ዓ.ም.)::

የወጣቱ ደራሲ የትምጌታ ከበደ ሃሳብም ከላይኛው ሃሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው (18/8/2001ዓ.ም)::በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የባህል ማዕከል ወጣቶች ብቻ ሳይሆን አንጋፋ ደራሲያንም እውቀታቸውን ለጀማሪና ወጣት ደራሲያን በማስተላለፍ

መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ነው:: የሥነ ጽሑፍ ዝግጅቶች ላይ ሞቅ ያለ ውይይትና ሂሶችን በድፍረት በመስጠት የሚማማሩበት መድረክም ነው ፡፡ በተለይም እነ ሀመር የስነ ጽሑፍ እና ጳውሎስ ኞኞ የጋዜጠኞች ክበብ የተለያዩ የስነ ጽሁፍ ዝግጅቶችን ያቀርቡ እንደነበረ ጋዜጠኛ ፋንታሁን ያስረዳል፡፡

የባህል ማዕከሉ ከኢትዮጵያውያን የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች በተጨማሪ ከፈረንሳይ አገርና ፈረንሳይኛ ቋንቋ ከሚናገሩ አገሮች የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎችን በማስመጣት የእውቀትና የባህል ሽግግር ያደርጋል:: ከቀረቡት ስራዎች ውስጥ ሴኔጋላዊ ረመዳን ሱሌማን «ዘለላ የፍቅር ደብዳቤ» በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ 2006 ያቀረበውን መጥቀስ ተገቢ ነው (ሙሉ ዝርዝሩን መግለጫዊ መዘርዝሩ ላይ ይገኛል)::

በአጠቃላይ የአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ በሚያቀርባቸው የስነ ጽሑፍ ዝግጅቶች ለኪነ ጥበቡ ማደግና ተሰሚነት እንዲኖረው ከፍተኛ እገዛ እያደረገ መሆኑን ከማዕከሉ÷ከጥበቡ ታዳሚዎች ና የስነ ጽሑፍ ስራቸውን የሚያቀርቡት ባለሙያዎች በአንድ ቃል የሚናገሩት እውነት ነው ፡፡

የስነ ጽሑፍ ሙያ እንዲጎለብትና ወደ ህብረተሰቡ የሚቀርብበትን መድረክ በመፍጠር ህብረተሰቡ የእለት ከእለት ኑሮው ላይ መሻሻል እንዲመጣና እድገት እንዲያሳይ የመሪነት ሚናን በመጫወት ላይም ይገኛል፡፡

## 3.2.3 ሙዚቃ

አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ለሙዚቃ ጥበብ እድገት ያለውን አስተዋፅኦ በርካታ መረጃ ሰጪዎቼ በአድናቆት ያስታውሱታል፡፡ የፈንታሁን ሸዋንቆጨውና የወረስ ገብረ እግዚአብሄር እንዲሁም የእጅግአየሁ ሽባባው/ ጂጂ/ለረጅም ጊዜ በአልያንስ ያቀርቡት የነበረው የሙዚቃ ዝግጅት እና ለንግስት ሳባ ቲያትር አጃቢነት የተለያዩ ማጀቢያ ዘፈኖቻቸው ከአድናቂዎቻቸው ዘንድ ለብዙ አመታት ታትሞ የቆዬ ስራ ነበር ፡፡ አርቲስት ግርማ ይፍራሸዋ በክላሲካልና በአፍሪካ ሙዚቃ ዘርፍ ፒያኖ ተጫዋችና የሙዚቃ ደራሲ ነው:: «አሊያንስ ለኢትዮጵያውያን አርቲስቶች ጥሩ መድረክ እየፈጠረ ሙያቸውን ያስተዋውቃል፡፡ እኔም እንደ ብዙዎቹ ባለሙያዎች ከአሊያንስ ጋር በመስራቴ ተጠቃሚ ሆኜያለሁ፡፡በአገር ውስጥና በውጪ አገር ሳይቀር የሙዚቃ ስራዬን እንዳቀርብ እገዛ አድርገውልኛል» በማለት ይናገራል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ዳይሬክተር አቶ እዝራ አባተ ስለአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የሚከተለውን አስተያታቸውን ያብራራሉ፡፡

> ያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ከሶስቱም የባህል ማዕከላት ጋር በሙዚቃው ዘርፍ በጋራ እንሰራለን፡፡ ሶስቱም የተለያዩ አቀራረብ ስላላቸው ለእኛ ጥሩ አጋጣሚ ነው፡፡ ወደ ፈረንሳይ ስንመጣ በርካታ የሙዚቃ ዝግጅቶችን ያቀርባሉ፡፡ የኢትዮጵያ(የሃበሻ)ሙዚቃ ፌስቲቫልን ማዘጋጀታቸው ጥሩ ተግባር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መድረኩን በማዘጋጀታቸው እንድንጠቀምበት አድርገውናል፡፡ በተጨማሪም ከውጪ አገር የሚያስመጧቸው የሙዚቃ ባለሙያዎች አውደጥናት ሲያዘጋጁ ት/ቤታችን ድረስ መጥተው ለተማሪዎቻችን ልምዳቸውን ያካፍሉናል፡፡ (እዝራ አባተ 16/10/03 ዓ.ም.) ፡፡

የአሊያንስ አቀራረብ የኢትዮጵያንና የፈረንሳይን ሙዚቃ በማቀላቀል የተለዩ ዜማዎችን የመፍጠርና የተለዩ አቀራረብ ስላላቸው ለባለሙያው እገዛ እንደሚያደርግ፤ያሬድ ሙዚቃ ት/ቤትም የበለጠ ከአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ጋር እንደሚሰራ አቶ እዝራ ያብራራሉ፡፡

አሊያንስ በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ አገርም መድረኮችን በማመቻቸት የኢትዮጵያ ሙዚቃ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት እንዲያገኝና የኢትዮጵያን ባህል/ዜማው፥ እስክስታው፥ ባህላዊ አለባበሱ፥ሙዚቃዊ ተውኔቱ፥ የሙዚቃ መሳሪያው/ እንዲተዋወቅ ከፍ ያለ ሚና ተጫውቷል፡፡ አርቲስት ግርማን ብቻ እንኳን ብንወስድ በአሊያንስ አማካኝነት ለብቻው ወደ11 የአፍሪካ ሃገሮች ተጉዞ የክላሲካል ሙዚቃ ያቀረበ ሲሆን፤ ወደ 12 ከሚሆኑ የአፍሪካ አገሮች ከድምፃዊት ጴጺያ ገ/ማርቆስ እና ሚካኤል በላይነህ ጋር ሙዚቃቸውንና ሥራቸውን ለማስተዋወቅ አስችሏቸዋል፡፡[5]

የአልያንስ የሙዚቃ ዝግጅት በተመለከተ አርቲስት ጌታቸው ደባልቄ ሲገልጽ፤

> አሊያንስ ስለባህልና ኪነ ጥበብ እድገት በሚያደርገው ጥረት እደነቃለሁ፡፡ አሊያንስ በባህሉ ዘርፍ ብዙ ሚና እንደተጫወተና ታላቅ አስተዋጽኦም በማድረግ ላይ

[5] ቃለ ምልልስ ያደረኳቸው ባለሙያዎች እንደገለጹት አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ በሙዚቃው ዘርፍ ካከናወናቸው ተግባራት አንዱና ዋነኛው ከግርማ ይፍራሸዋ ጋር የተገበረው ነው፡፡

እንዳለ እገነዘባለሁ:: የኢትዮጵያን ሙዚቃ በግሉም እንዲታወቅ እያደረገ ይገኛል ( አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሄት፣1990 ዓ.ም. )::

አሊያንስ ለኢትዮጵያ ሙዚቃ እድገት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንዳደረገ የዘርፉ ባለሙያዎች ይስማሙበታል:: በተለይም የኢትዮጵያን አርቲስቶች ለማስተዋዋቅ፣ የተረሱትን ታላላቅ አርቲስቶች በመዘከርና መድረክ በመስጠት የሚተጋበት ጉዳይ ይጠቀሳል:: በተለይም ደግሞ የተለያዩ የሙዚቃ ፌስቲቫሎችን ባህል ማዕከሉ በማዘጋጀት ክብሩን ለተለያዩ የዘርፉ ባለሙያዎች ያደርጋል::

እ.ኤ.አ.ከ2001 ጀምሮ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ፌስቲቫልን በማዘጋጀት የኢትዮጵያን ሙዚቃ በማስተዋወቅ እና ክብርና ምስጋና እንዲያገኙ በማድረግ፣ዓለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኙ በማድረግ እንዲሁም ወጣት ባለተሰጥኦ ሙዚቀኞች ትኩረት እንዲያገኙ ባህል ማዕከሉ ሰርቷል:: ከ2004 ጀምሮ ደግሞ የውጪ አገር ባንድ የሆኑትንና የኢትዮጵያን ሙዚቃ የሚጫወቱትን ጨምሮ በመጋበዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ሙዚቃ እንዲያድግ እየተደረገ ነው:: ይህንን ስራ በመስራት አሊያንስ እንደድልድይ ሆኖ በማገልገል ሙዚቀኛውንና ተመላካቹን፣ሙዚቀኛውንና ሚዲያውን፣የአገር ውስጡንና የውጪውን ሙዚቀኛ ለማገናኘት ችሏል(መርሴማ ታሪኩ 5/10/03 ) ::

ወ/ሮ መርሴማ እንደምታብራራው ከዚህ በፊት ተደርጎየማያውቅና አዲስ አይነት የሙዚቃ ስልቶችንም በመከተል የጃዝ ሙዚቃንንና አዝማሪን በመቀላቀል የተሰራበት ሂደት ልዩ የሙዚቃ ፈጠራውንና ጣዕሙን ለአድማጨ ለማሰማት ተችሏል:: እነ ሄኖክ ተመስገን፣ግሩም መዝሙርንና አበጋዙ ሺዎታን የመሳሰሉ የዘመናዊ ሙዚቃ አቀናባሪና ተጨዋቾችን ከአዝማሪ ዘፋኞች መካከል ሚሚ ዘነበ፣መላኩ በላይ፣ ሰላምነሽ ዘመነእና የመሳሰሉትን በማቀናጀት የቀረቡት ዝግጅቶች ሙዚቃችንን በተለያዩ አቀራረቦች ማቅረብ እንደሚቻል የታየበት ክስተት እንደነበረ በማስረዳት::

እንዳለ እገነዘባለሁ። የኢትዮጵያን ሙዚቃ በግሉም እንዲታወቅ እያደረገ ይገኛል ( አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሄት፤1990 ዓ.ም. )።

አሊያንስ ለኢትዮጵያ ሙዚቃ እድገት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንዳደረገ የዘርፉ ባለሙያዎች ይስማሙበታል። በተለይም የኢትዮጵያን አርቲስቶች ለማስተዋወቅ፣ የተረሱትን ታላላቅ አርቲስቶች በመዘከርና መድረክ በመስጠት የሚተጋበት ጉዳይ ይጠቀሳል። በተለይም ደግሞ የተለያዩ የሙዚቃ ፌስቲቫሎችን ባህል ማዕከሉ በማዘጋጀት ክብሩን ለተለያዩ የዘርፉ ባለሙያዎች ያደርጋል።

እ.ኤ.አ.ከ2001 ጀምሮ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ፌስቲቫልን በማዘጋጀት የኢትዮጵያን ሙዚቃ በማስተዋወቅ እና ክብርና ምስጋና እንዲያገኙ በማድረግ፤ዓለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኙ በማድረግ እንዲሁም ወጣት ባለተሰጥኦ ሙዚቀኞች ትኩረት እንዲያገኙ ባህል ማዕከሉ ሰርቷል። ከ2004 ጀምሮ ደግሞ የውጪ አገር ባንድ የሆኑትንና የኢትዮጵያን ሙዚቃ የሚጫወቱትን ጨምሮ በመጋበዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ሙዚቃ እንዲያድግ እየተደረገ ነው። ይህንን ስራ በመስራት አሊያንስ እንደድልድይ ሆኖ በማገልገል ሙዚቀኛውንና ተመላካቹን፤ሙዚቀኛውንና ሚዲያውን፤የአገር ውስጡንና የውጪውን ሙዚቀኛ ለማገናኘት ችሏል(መርሴማ ታሪኩ 5/10/03 ) ።

ወ/ሮ መርሴማ እንደምታብራራው ከዚህ በፊት ተደርጎየማያውቅና አዲስ አይነት የሙዚቃ ስልቶችንም በመከተል የጃዝ ሙዚቃንንና አዝማሪን በመቀላቀል የተሰራበት ሂደት ልዩ የሙዚቃ ፈጠራውንና ጣዕሙን ለአድማጩ ለማሰማት ተችሏል። እነ ሄኖክ ተመስገን፤ግሩም መዝሙርንና አበጋዙ ሺዎታን የመሳሰሉ የዘመናዊ ሙዚቃ አቀናባሪና ተጨዋቾችን ከአዝማሪ ዘፋኞች መካከል ሚሚ ዘነበ፤መላኩ በላይ፤ ሰላምነሽ ዘመነእና የመሳሰሉትን በማቀናጀት የቀረቡት ዝግጅቶች ሙዚቃችንን በተለያዩ አቀራረቦች ማቅረብ እንደሚቻል የታየበት ክስተት እንደነበረ በማስረዳት።

ፍራንሲስ ፋልሲቶ የፈረንሳይ ታሪክ፤ የኢትዮጵያን ሙዚቃ አጥኚና የሙዚቃ ፕሮዲዩሰር ሲሆን ላለፉት 25 ዓመታት በኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ ጥናት በማካሄድ የኢትዮጵያን ሙዚቃ «ኢትዮፒክ» በሚል በሲዲ በማሳተም በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲተዋወቅ ያደረገና የኢትዮጵያን የሙዚቃ ፌስቲቫል ከአልያንስ ጋር በመተባበር የሚያዘጋጅ የሙዚቃ ሰው ነው ። ከአሊያንስ ጋር የሚያዘጋጁትን የሙዚቃ ፌስቲቫል ጥቅም ሲገልጽ፤

> ዋናው ጥቅሙ በመላው ዓለም ሊወደድ የሚችለውን ግን ደግሞ እዚሁ ሃገር ውስጥ ብቻ ተወስኖ የቆየውን ሙዚቃ ለተቀረው ዓለም በስፋት ማስተዋወቅ ነው ። በነገራችን ላይ ካደረኩት ሰፊ ጥናት እንደተረዳሁት የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ከዜማ ይልቅ በሰምና ወርቅ ለተሞላው ግጥም ከፍተኛ ትኩረትን የሚሰጡ በመሆናቸው አማርኛ የማያውቀው የሌላው ዓለም ሰው የእነርሱን ሙዚቃ የሚያደንቅና የሚወድ አይመስላቸውም ። ይሄ ፍጹም ስህተት ነው። አማርኛ፥ትግርኛ፥ ኦሮምኛ፥ጉራጊኛና ሌሎችም የትኛውንም የሃገራችሁን ቋንቋ የማይችል የውጭ አገር ዜጋ የኢትዮጵያን ሙዚቃ በሚገባ ማጣጣም ይችላል/13/12/2001/።

የሙዚቃ ፌስቲቫል መርሃ ግብሩ ከ13 ዓመት በፊት በ1990 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን፤ የመጀመሪያው መታሰቢያ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ በግል የሳክስ ሙዚቃ አሳታሚና ባለመደብር አምሃ እሸቴ እንዲሰየም ተደርጓል። ከመጀመሪያው መታሰቢያ ቀጥሎ ለአስናቀች ወርቁ፥ ለጥላሁን ገሰሰ ፥ለመሃሙድ አህመድ፥ ለሳክስፎኒስቱ ጌታቸው መኩሪያና ለሌሎችም ክብር እየተሰጠ የሙዚቃ ፌስቲቫሉ ለአስር ጊዜያት ተካሂዷል።

ስለሙዚቃ ፌስቲቫል ዝግጅት አስፈላጊነት የአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ቦርድ ሊቀመንበር አቶ አምዴ አካለወርቅ እንደገለፁት፤

> የባሕል ማዕከሉ ለኪነ ጥበብ እድገት አስተዋጽኦ በማድረግ የተለያዩ ዝግጅቶችን ያቀርባል። ከእነዚህም ውስጥ የሙዚቃ ፌስቲቫል በማዘጋጀት በአንድ ጊዜ ሁለት ሶስት አስተዋፅኦ ለማድረግ አስችሏል። የመጀመሪያው መድረኩን ያላገኙና ችሎታ ያላቸው

መዚቀኞች መድረኩን ፈጥረንላቸዋል። ሁለተኛው የሙዚቃ አድማጩ ኢትዮጵያዊ ሙዚቃን በተለያዩ አቀራረቦች/በዘመን፣በጾታ፣ በተመሳሳይ ቅኝት ወዘተ/ እንዲያይ ና እንዲመለከት ተደርጓል። ሶስተኛም አንጋፋና ለሙዚቃ እድገት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ የነበራቸውን ሙዚቀኞች በመዘከር ለአዲሱ ትውልድ የሙዚቃ ሥራዎቻቸውን እንዲያደምጥ ያደርጋል (አሊያንስ100ኛ ዓመት መጽሄት፣1990ዓ.ም)።

በሙዚቃ ፌስቲቫል ዝግጅቶች የተለያዩ የአገር ውስጥ ባንዶች በግልና የኢትዮጵያና የአውሮፖ ሙዚቀኞች በጋራና በተናጠል የሁለቱን አገሮች ሙዚቃዎች የሚያቀርቡበት ዝግጅትም አለ። ዘመናዊ የኢትዮጵያ ባንድ ከፈረንሳይ ዘመናዊ ባንድ ወይም የአዝማሪ ማሲንቆና ዘፋኙን ከፈረንሳይ ዘመናዊ ባንድ ጋር አቀናጅቶ የሚቀርብበት ዝግጅት አይነት ማለት ነው ።

ባለፉት ሶስት ዓመታት የተዘጋጁ የሙዚቃ ፌስቲቫል ሙሉ ዝግጅቱን በመቅረጽና በሲዲ በማዘጋጀት በመላው ዓለም እንዲሰራጭ በማድረግ የኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ ውጤቶች በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ዕውቅና እንዲያገኙ ባህል ማዕከሉ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ።

የ2010ን እንኳን ብንወስድ የኢትዮጵያ ሙዚቃን ለማድመቅ፣በብዙ ባህላዊ ሙዚቃዎች ከሚታወቀው ደቡብ ኢትዮጵያ አንዱ የሆነው‹‹ጋሞ››፣በተለየ የሙዚቃ ፈጠራቸው ከሚገኙት መካከል አዲሶቹ እና ‹‹ኑቢያን አርክ››፣‹‹ኢትዮ ከለር›› እየተባሉ የሚጠሩት ምርጥ የአዝማሪ ቡድን፣በብራዚል ብዙ ቆይታ ያደረገው አሜሪካዊው ዲጄ ‹‹ማጋቦ›› እንዲሁም ተጋባገሮቹ ፈረንጆቹ‹‹ኡካናዳንስ እና ኢትዮ›› የበፊቱን የኢትዮጵያ ወርቃማውን የሙዚቃ ስልት ተጫውተውታል። እነዚህን ዝግጅቶች ደረጃቸውን በጠበቁ ስቱድዮዎች እንዲታተሙ በማድረግ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እንዲሰራጩ ተደርገዋል። ባለፉት አስር ዓመታት ዓመታዊ ትርኢቱ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ፌስቲቫል የሃገሪቱን የሙዚቃ እድገት ያበሰረ

እና ለውጥ ያስገኘ ነው (ፍራንሲስ ፋልሲቶ፤ /13/12/2001)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሙሉ ባንዱ ከአውሮፓ አልያም ከራሷ ከፈረንሳይ ወይም ፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑ አገሮች የሙዚቃ ቡድን በማስመጣት የባህል ልውውጥ የሚያደርጉበት ዝግጅቶች በርካቶች ናቸው፡፡ «ግንደ ቆርቁር» በመባል የሚጠራው ታላቁ የፈረንሳይ የጃዝ ሙዚቃ አራትዮሽ የሚታወቀው ዘመን የማይሽራቸውን የፌላ ኩቲ÷የሮላንድ ከርክ÷ የዳክ ኤ ልንግተንና በሰባዎቹ ዓመተ-ምህረት በኢትዮጵያ ይቀነቀን የነበረውን የጥንቱን የፋንክ ሙዚቃ ቅለጻዎች በራሳቸው መንገድ በመጫወት ታዋቂነት ያተረፉ ሙዚቀኞች በአምስተኛው የኢትዮጵያ የሙዚቃ ፌስቲቫል ዝግጅታቸውን በድሬዳዋ አሊያንስና ÷ በአዲስ አበባው አሊያንስ አቅርበዋል ፡፡ አራትዮሽ የፈረንሳይ የሙዚቃ አባላት የተባሉ የሙዚቃ ባለሙያዎችን አሊያንስ ወደ አገራችን አስመጥቶአቸው ነበር ፡፡ እነዚህ የሙዚቃ አባላት ለረጅም ጊዜ የሚተዋወቁና አብረው ብዙ የሰሩ ሲሆኑ ፤ በድምጽ ÷በሳክስፎን÷ በትራምፔት ÷በቱባ÷ በሱባሶፎንና በጃዝ ከበሮ ታጅበው ድንቅ ለዳንስ የሚወሰውስ የሙዚቃ ዝግጅቶችን አቅርበዋል፡፡ በአምስተኛው የኢትዮጵያ ሙዚቃ ፌስቲቫል እ.ኤ.አ.ጥር 11 ቀን2006 ኢደን ሬቸል የተባለ የሮክ ሙዚቃ አቀንቃኝ ሰባት አባላት ያሉት የሙዚቃ ቡድን በማምጣት በእብራይስጥና በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ የሙዚቃ ዝግጅቶቻቸውን አቅርበዋል ፡፡ዝነኛው የማሊ ዘፋኝ ሐቢብ ኮቲና በማዳ የተባለው ባንድ በ1989 ዓ. ም አዲስ አበባ አሊያንስና ብሄራዊ ቲያትር የሙዚቃ ዝግጅታቸውን በማቅረብ የባህልና የሙዚቃ ልውውጥ አድርገዋል ፡፡ የጅቡቲ «ፋይፍ ስታር ባንድ»ና «የዲሲ» የተባለ ሁለት የሙዚቃ ቡድኖች ከጅቡቲ ኢምባሲ ጋር በመተባበር «የጅቡቲ ምሽት» በሚል የጅቡቲን የሙዚቃና ባህላዊ ዳንስ ያቀረበበት ዝግጅት የሚጠቀስ ይሆናል፡፡ ከፈረንሳይ ዘሾፒንግ ከተባለ ባንድ በተጨማሪ ከማሊ ÷ከሴኔጋልና ከሌሎችም አገሮች ባለሙያዎች እየመጡ÷ የባህልና የኪነ ጥበብ ልውውጥ የሚደረግባቸው ዝግጅቶች ይጠቀሳሉ (ሙሉ ዝርዝሩን በመዘርዝራዊ መግለጫ አባሪ አንድ ላይ ቀርቧል) ፡፡

በሙዚቃ ዝግጅቱ ከልምድ ልውውጡ በተጨማሪም÷ ጊዜና ቦታ የማይሰጣቸውና ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተለይ በከተሞች ተፈላጊነታቸው በመጠኑም ቢሆን እየቀነሰ የመጣውን የአዝማሪነት ሙያ ለማሳደግ አልያንስ ተንቀሳቅሷል፡፡

የአዝማሪነት ሙያ ቀደም ሲል ጀምሮ የመጣ አንጋፋ ባህላዊ የዘፈን ጥበብ ነው፡፡ስለ አዝማሪነት ሙያ የተለያዩ የዘርፉ ባለሙያዎች የራሳቸውን ብያኔ ይሰጣሉ ፡፡ አሸናፊ (እ.ኤ.አ.1971) አዝማሪ የሚለውን ቃል ከሙያው ባህሪ ተነስተው ግጥምና

ዜማውን በህገረሠብ የሙዚቃ መሣሪያ (ማሲንቆ) በማጀብ በታዳሚው ፊት ብቻውን ወይም ጥንድ ሆኖ የሚከወን እና ታዳሚውን የሚያዝናና ዘፋኝ ማለት እንደሆነ ገልፀዋል። ከዚህም በተጨማሪ አሸናፊ (እ.ኤ.አ.1971፡168) “አዝማሪ የሚለው ቃል “ዘመረ” ከተባለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም አመስጋኝ ማለት ነው” ብለዋል። ደስታ ተክለወልድ (1962፣496) አዝማሪ የሚለውን ቃል ከሙያው ባህሪና ማህበረሰቡ ለሙያው ከሚሠጠው ግምት በመነሳት “ያዘመረ፣ የሚያዘምር፣ ዘፋኝ፣ ባለማሲንቆ፣ አርኾ፣ ጪኸ.” በማለት በይነውታል ። አዝማሪነትን በካዛኒቺስ፤ በዳትሰን ሰፈር ወይም በቺቺኒያ በባለሙያነት የሚሰራውን የራሱን ሙያና ማን እንደሚባል ብንጠይቀው ‹‹አርቲስት፤ ሙዚቀኛ›› የሚል መልስ ይሰጠናል ። ጎንደር ወይም ወሎ የሚገኝ አዝማሪን ብንጠይቀው ደግሞ ራሱን ሰውን አመስግኖ ኗሪ አድርጎ ዝቅ ባለ ስም ከበታችነት የሙያና የስራ መስክ ጋር አያይዞ ሊያቀርብልን ይችላል ። ያም ሆነ ይህ አዝማሪነት የሙዚቃ ጥበብ መሆኑ ሁላችንንም የሚያስማማን-ሙያ ነው ።

የአዝማሪ ዘፈን በድምፅ፣ በማሲንቆ፣ በግጥምና በሰውነት እንቅስቃሴ ተዋህዶ ይከወናል። በዚህም ህብረተሰቡን በማስደሰት፣ በማዝናናትና በማስተማር ሲያገለግል ቆይቷል። አሁንም እያገለገለ ይገኛል።

አዝማሪዎች በሚያቀርቡበት መድረክ ሃገረሰባዊ አልባሳቱን ለብሰው ፤ አሽንክታቡንና ጠልሰሙን አጥልቀው በገጠር አካባቢ ለሙገሳም ሆነ ለወቀሳ የሚጠቀሙበትን ግጥምና ዜማ እንዲያንቆረቁሩ ነው የአሊያንስ መድረክ የሚዘጋጀው። ስለሆነም ጥንድ ባልና ሚስት አልያም እህትና ወንድም ከዚያም ካለፈ በስራ የሚግባቡና የሚመቻቹ አዝማሪዎች በቡድን ማሲንቆአቸውን ከርክረው፤ ከበሮቸውን/አታሞአቸውን/ መትተው ወይም ደብድበው፤ ከፍ ባለ ዜማ እየተቀባበሉ ግጥምና ቅኔያቸውን ከዜማቸው ጋር ያወርዱታል[6] ። እስክስታውን እያስነኩ ታዳሚውን ከመቀመጫው ያስነሱታል። የዝግጅታቸው አድማጭና አድናቂ ብቻ ሳይሆን ተሳታፊ ያደርጉታል። አገረ መንገዱንም እንዲሸልማቸው ያሞካሹታል።

በአሊያንስ ያለው የአዝማሪ ምሽት ሙያውን ከፍ ከፍ በማድረግ ታዳሚው በሃገረሰብ ሙዚቃ እንዲዝናና እና ክብር እንዲሰጥ የማድረግ እንድምታ አለው ።

---

6 .ከኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ ውስጥ በአዝማሪዎችና በመሲንቆ የሚደረገው ጨዋታ/ሰምና ወርቅ/የሚበዛበት መሆኑን ዘነበ በቀለ /በ1987/በጥናቱ መመልከቱን ልብ ይሏል ።

ለበርካታ ጀማሪ አዝማሪዎችም «የአዝማሪ ምሽት» በሚል መድረኩን በማዘጋጀት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ድረስ መድረኮችን በማመቻቸት ለሙዚቃው እድገት የበኩሉን ሚና በመወጣት ላይ ነው፡፡ ከአዝማሪዎቹ መካከል የአበባው አንዳርጌና ቡድኑ፣ የመሰለ አስማማው፤የማለፊያ ልብ ተካና ቡድኗ፤ የገነት ማስረሻና ቡድኗ፤ከበርካቶቹ በጥቂቱ ተጠቃሽ ናቸው (ሙሉ ዝርዝሩን ከመዘርዝራዊ መግለጫ አባሪ አንድ ላይ ይገኛል)፡፡

በአዝማሪ ምሽት ዝግጅቶች ላይ የአቶ እዝራ አባተ አስተያየት ከላይ ከቀረበው ይለያል፡፡ አቶ እዝራ እንደሚሉት፤

> የሊያንስ የአዝማሪ ምሽት ማለት በአዝማሪ ቤቶች የሚካሄዱ የሙዚቃ ዝግጅቶችን እነርሱ ወደ አዝማሪ ቤት እንዳይሄዱ በራሳቸው መድረክ እንዲጫወቱ በማድረግ የመዝናኛ ቦታውን ቀየሩት እንጂ ሙዚቃውን ለማሳደግ (የአዝማሪውን) ጥረት አድርገዋል በሚለው ላይ አልስማማም፡፡ከመዝናኛነት ባለፈ አካዳሚያዊ በሆነ ለፎክ አርቱ(ለባህላዊው ሙዚቃ) ምን ያደረጉት ድጋፍ አለ? ሲሉ ይሞግታሉ (እዝራ አባተ፤16/3/03) ፡፡

ከአቶ እዝራ ሃሳብ ጋር የአቶ በቀለ መኮንን፤ ደራሲ ዳንኤል ወርቁና ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኬሬቦ አስተያየትም ተመሳሳይነት አለው ፡፡

ወ/ሮ መርሴማ ታሪኩ ግን ከዚህ የተለዩ አመለካከትና አስተያየቷን ታብራራለች፡፡ የአዝማሪነት ሙያ በህብረተሰቡ ዘንድ እየተረሳና የተሳሳተ አመለካከት እየያዘ በመምጣት ላይ ነበር፡፡ በተወሰነ የምሽት ቤቶች ብቻ ይደመጥ የነበረውን ባህላዊ ሙዚቃ መድረክ ሰጥተን የውጭ አገር ዜጋውም ሆነ ኢትዮጵያዊው የሙዚቃ ተሰጥኦዋቸውን እንዲያዳምጥ ከማድረጋችንም ባሻገር ለአንዳንዶችም የውጪ አገር ተሞክሮና የሙዚቃ ሙያቸውን እንዲተዋወቅ አድርገናል ትላለች፡፡

ከዚህ በተጨማሪ «የኢትዮጵያ ሴቶች ድምጽ» በሚል የሴቶች የሙዚቃ ዝግጅት ብቻ የሚቀርብበትና እውቅና የሚሰጥባቸው÷ ከአድናቂዎቻቸው ጋር የሚገናኙበትና ስለ ሙዚቃ ህይወታቸው እየተተረከ የሚቀርብበት መድረኮችም አሉ፡፡ በዚህ የዝግጅት መርሃ ግብር ዝግጅታቸውን በ1998 ዓ. ም. ካቀረቡት መካከል ዙሪያሽ አብዩ ÷ እንደልቤ ማንደፍሮ ÷ ትዕግስት አፈወርቅ ና ዝናሽ ጸጋዬ ይገኙበታል ፡፡ በዝግጅቱ ዙሪያ እንደልቤ ማንደፍሮን አነጋግሬአት ነበር፤

በአሊያንስ ሴቶች ብቻ ሙዚቃ እንድናቀርብ በተደረገበት ወቅት ከአድናቂዎቻችን ጋር ለመገናኘት የተመቻቸ ዝግጅት በመሆኑ እኛም ለሙያችን የተሰጠው ክብር ስላስደሰተን ከልባችን ነበር የምንጫወተው ። አድናቂያችንንም በዝግጅታችን ተደስቶና ተዝናንቶ እኛንም በትክክል ማንነታችንን በቅርበት ለማወቅ ችሏል። ከዚያ መድረክ ወዲህ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ሙዚቃ ለማቅረብ ዕድሉ ተመቻችቶልኛል ብላለች(ዝናሽ ጸጋዬ፤ 16/2/2002 ዓ.ም)።

በተመሳሳይም ባለሙያዎችን በዘመን፤ በጾታ፤ በሙዚቃ ተመሳሳይነት፤ በባህል፤ ዘመናዊ ባንድ በሚሉና የሙዚቃውን ቃና ለማጣጣም በሚያስችል መልኩ በማቅረብ፤ ለውይይት መድረኮችን በማዘጋጀትና በመዝናኛነት ሰፋ ያሉ ስራዎች እንደተሰሩ ወ/ሮ መርሴማ ያብራራሉ።

‹‹ አምስቱ ታላላቅ ዘመናዊ የሙዚቃ ሰዎች» በሚል ርዕስ የሙዚቃ ዝግጅታቸውን እንዲያቀርቡ አሊያንስ መድረክ ያዘጋጀላቸው አርቲስት መሐሙድ አህመድ ፥ ባህታ ገብረ ህይወት፥ ግርማ ነጋሽ ፥ ጌታቸው መኩሪያ እና መኮንን በቀለ ተጠቃሽ ናቸው። በእነዚህ አንጋፋ አርቲስቶች ዝግጅት በርካታ አድናቂያቸው ያለፈውን ጊዜ በማስታወስ አዲሱ ትውልድ የሙዚቃውን ደረጃ ምን ይመስል እንደነበረ ካሁኑ ጋር እያወዳደረና እያጣጣመ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን በአምስተኛው የሙዚቃ ፌስቲቫል ላይ እ.ኤ.አ.ጥር 13 ቀን 2006 ባቀረቡት ዝግጅት ታድሞባቸዋል(ሙሉ ዝርዝሩን በመግለጫዊ መዘርዝሩ ይገኛል) ።

‹‹አምስቱ ዝነኛ የባህል ሙዚቀኞች» በሚል ርዕስ በስማቸው መድረክ የተዘጋጀላቸውና በባህል የሙዚቃ ጨዋታቸው ለረጅም ዓመታት በሙያው ላይ የቆዩትን አርቲስት ራሄል ዮሃንስ፥ ዳምጠው አየለ፥ ሃብተ ሚካኤል ደምሴ ፥ ይርጋ ዱባለ ና አለማየሁ ፋንታ በግንድ አልብስ ባህላዊ ባንድ ታጅበው ቱባውን የአገራቸውን ባህል በተለይም የአማርኛ ባህላዊ ዘፈን እ.ኤ.አ.ጥር 13 ቀን 2006 በኢትዮጵያ

5ኛው የሙዚቃ ፌስቲቫል በማቅረብ ከአድናቂዎቻቸው ጋር ለመገናኘት ችለዋል ፡፡ በክራር ና ማሲንቆ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚጫወቱት አንጋፋዎቹ ዘፋኞች የባህል አምባሳደር በመሆን የአገራቸውን ሙዚቃ በማስተዋወቅ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ማበርከታቸው ተገልጿል(ሙሉ ዝርዝሩን ከመግለጫዊ መዘርዝሩ ይገኛል)፡፡

ወ/ሮ መርሴማ እንደምታብራራው የአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የሙዚቃ መድረኩን ለፈረንሳዮች ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እንዲሁም የአፍሪካ ለአፍሪካ ግንኙነት እንዲፈጠርና እንዲጠናከር በሙዚቃውና በባህል ዝግጅቶች ዙሪያ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርጓል ፡፡ በአዲስ አበባ ካሉት የባህል ማዕከላትም አሊያንስ የበለጠ ውጤታማ የባህል ማዕከል መሆን እንደቻለ ታስረዳለች ፡፡

አምባሳደር ስቲፋን ጎምፔርትዝም የአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ሲያከናውናቸው የቆዩት ስራዎች ውጤታማ መሆናቸውን ሲያብራሩ፤

> የአፍሪካ መዲናዋ አዲስ አበባም ለዚህ የባህል ልውውጥ አመቺ እንደመሆንዋ በአልያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የመቶ ዓመታት ቆይታ ውስጥ ያለማሰለስ እጅግ ብዙና አዳዲስ የባህል ለውውጦች ተካሂደዋል ፡፡ . . . አልያንስ የእውቀት ማስፋፊያና የባህል ልውውጥ ቦታ ብቻም ሳይሆን አርቲስቶች እንደ ጥበብ ቤታቸው የሚያስቡት መስሪያ ቤታቸውም ጭምር ነው፡፡ ለዚህም በእድሜ ወጣት የሆኑት ጀማሪ አርቲስቶችም ሊቀላቀሉት የሚያልሙት ጎራ ነው፡፡ በአሊያንስ ብዙ ሰዓሊያን፤ ቀራጺያን፤ ታላላቅ ጣዕመ- ዜማዎች፤ ስነ ውዝዋዜዎች ተፈጥረዋል፡፡ አሁንም እየተፈጠሩ ነው (አሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሔት ፤1990 ዓ.ም.)፡፡

በሌላ በኩል ወ/ሮ መርሴማ የባህል ማዕከሉ በዝግጅቶች ላይ በስፋት ለመንቀሳቀስና የኪነ ጥበብ ዝግጅታቸውን ለሚያቀርቡ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ተመጣጣኝ ክፍያ ለመክፈል እንደችግር የያዛቸው የስፖንሰር ሺፕ ጉዳይ መሆኑን ታብራራለች፡፡ በአሁኑ ወቅት የፈረንሳይ መሰረት ያላቸው እንደ ቢጂአይ እና ቶታል ኢትዮጵያ አይነት ድርጅቶች ተባባሪዎቻቸው መሆናቸውን አስረድታለች ፡፡ አቶ እዝራ

አባተም የፈረንሳይ ባህል ማዕከል የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት በሙዚቃው ዙሪያ በሚያካሂዳቸው መድረኮች በስፋትና በሙሉ አቅማችን መድረኮችን ተጠቅመንባቸዋል በማለት ያስረዳሉ። ጥናት አቅራቢውም በተከታተላቸው የአንድ ዓመት ተከ-ል ዝግጅቶችና ከሰበሰባቸው የጥሪ ካርዶች መረጃ እንዳገኘው አሊያንስ በሙዚቃው ዘርፍ በስፋት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

## 4. የጀርመን ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ

የአውሮፓ ‹አባት› አገር የሚል መጠሪያ ያላት ጀርመን ከኢትዮጵያ ጋር የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከጀመረች የ106 ዓመታት እድሜ ተቆጥሯል ። የኢትዮጵያና ጀርመን የዲፕሎማቲክ ግንኙነት 100ኛ ዓመት እ.ኤ.አ.በ2005 ሲከበር የታተመው መጽሄት እንደሚገልጸው፤

> እ.ኤ.አ. በ1904 ዓ.ም. በጀርመኑ ንጉስ ዊል ሐልም 2ኛ የተሰየመ አማካሪ ቆንስላ በሚል የማዕረግ ስያሜ ሽፋን ፍሪድሪሽ ሮዘን የሚመራው አንድ የመልዕክተኛ ቡድን ወደ ቀድሞዋ አቢሲኒያ ለመምጣት ተነሳ። የጉዞውም ዓላማ ዓጼ ምኒሊክ ዘንድ ቀርቦ መልዕክቱን ማድረስ ነበር። ከረጅም የመርከብ ፤የባቡርና የፈረስ ላይ ጉዞ በኋላ ፍሬድሪሽ ጎዳና ከሚገኘው ቦንሃርት ሬስቶራንት በተደረገለት ድጋፍ እራሱን ያዘጋጀው የጀርመኑ ልዑክ ቡድን አዲስ አበባ ደረሰ።እንደደረሰም ጀርመን በኢትዮጵያ ላይ ምንም አይነት የቅኝ ግዛት ፍላጎት ባለማሳየቷ ሳይሆን አይቀርም በወዳጅነት የተዘረጉ እጆች ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉለት።የልዑክ ቡድኑ የጉዞ ዓላማ የተሳካ ነበር።ማርች 7 ቀን1905 ዓ.ም. በሁለቱ አገሮች መካከል የነጻ ግብይትንና ለጀርመን ዜጎች በመላ አገሪቱ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብትን የሰጠ ውል መፈራረም ቻለ።
>
> (Ethiopia German 100 Years Diplomatic Relations catalogue;1,2005)።

የኢንሳይክሎፒዲያ ኢትዮፒክ ረዳት ኤዲተር ዋልቨርት ስክሚዲት እንደሚሉት የኢትዮጵያና የጀርመን ግንኙነት በጀርመን የስነ መለኮት ምሁራን አማካኝነት ‹‹ የመጽሀፍ ቅዱሷ ሃገር›› ወደሚሏት ኢትዮጵያ ግንኙነት የተጀመረው በመካከለኛው ዘመን መገባደጃ ነው ። በ19ኛው ክ/ዘመን ሚሲዮናውያን በኢትዮጵያና በጀርመን መካከል ያለውን ግንኙነት በዋናነት ለመመስረት ችለዋል። የዲፕሎማሲና የንግድ

ግንኙነቶች የተጀመረው /ከፈረንሳይ፤ ታላቋ ብሪታኒያ እና ከ አውስትሪያ እንኳን / የዘገዬ ነው ። ከ16 ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የጀርመን ተመራማሪዎች ስለኢትዮጵያ የተነገሩ ታሪኮችን ይመረምሩ ነበር። ቅድመ መጽሃፍ ቅዱስ የነበሩ ጥበቦችና አፈታሪኮች ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖራሉ የሚል ጥርጣሬ ስለነበራቸው በ1652 ዓ.ም ኢትዮጵያዊው ተመራማሪ አባ ጎርጎርዮስ በልዑል ኤርነስት አክሰን ጆታ አልተንበርግ ግብዣ የፍሪዴንታል ቤተመንግስትን ተቀላቀሉ። እዚያም ሆነው በልዑሉ ትዕዛዝ የምስራቅ አገሮች ቋንቋና ስልጣኔ ጠበብት ከሆነው ሂኢብ ሉዶልፍ ጋር በመሆን ስለኢትዮጵያ ታሪክና ዘር አመጣጥ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠውን ስራ አከናወኑ። ይፋዊ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የመመስረት ሃሳቡ የቆየ እንደሆነ ይገመታል (Ethiopia German100 Years Diplomatic catalogue፡8፡2005) ።

እንደ ዋልቨርት አገላለጽ ፤ የኢትዮጵያና ጀርመን ግንኙነት እንደገና በተጠናከረ መልኩ ከተመሰረተ በኋላ የደብዳቤ ልውውጥ የተጀመረው በ1870ዎቹ ሲሆን፤ በመጨረሻም ቋሚ የዲፕሎማሲ ግንኙነት እ.ኤ.አ. በ1905 ተመስርቷል ።

## 4.1 የጀርመን ባህል ማዕከል ታሪክ

ጀርመናዊው የስነ ጽሁፍ አባት ና ሊቅ እየተባለ በሚጠራው በጎተ ስም የተሰየመው የባህል ማዕከል በመላው ዓለም በ130 ከተሞች ውስጥ ይገኛል ። የኢትዮጵያው በአፍሪካ ቀዳሚው ማዕከል ነው (ዮናስ ታረቀኝ 8/10/03) ።የጀርመን የባህል ማዕከል /ጎተ/ በአዲስ አበባ የተቋቋመው በ1953ዓ.ም. እንደሆነም መረጃዎች ያመለክታሉ(40th Anniversary Goethe institute ፤2002፤13)። የጀርመን ባህል ማዕከል የተቋቋመው በኢትዮጵያ ወይም በጀርመን መንግስታት ጥያቄ አይደለም ። በጀርመን አገር የተማሩ ኢትዮጵያውያን ጥያቄያቸውን ለኢትዮጵያ መንግስትና ለጀርመን ኢምባሲ በማቅረባቸውና በመፈቀዱ ለማዕከሉ መከፈት የላቀ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ከጥር 1953 ዓ.ም ጀምሮ እንቅስቃሴ በማድረግ በስድስተኛው ወር ሰኔ ላይ ንጉሰ ነገስት አጼ ኃይለ ስላሴ፤ጸሃፊ ትዕዛዝ ተፈራወርቅ ኪዳኔ፤ ልዑል ደጃአዝማች አስራተ ካሳ፤ልጅ እንዳልካቸው መኮንን፤የጀርመን አምባሳደር ፓውሉስ ቮን ስቶልዝማንና ሎሎችም እንግዶች በተገኙበት ማዕከሉ ተመርቆ ተከፍቷል (40th Anniversary Goethe institute ፤2002፤13) ። የመጀመሪያው የጀርመን ባህል ማዕከል አራት ኪሎ ከድላችን ሃውልት ፊት ለፊት የተከፈተ ሲሆን ፤ለአርባ ዓመታት

በዚያው ቦታ አገልግሎት ሰጥቷል ። ላለፉት አርባ አመታትም ስምንት ዳይሬክተሮች የመሩት ሲሆን፤ ከ2005 ጀምሮ የባህል ማዕከሉ ወደ ስድስት ኪሎ በመዛወሩ ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ አገልግሎቱን በመስጠት ላይ ይገኛል ። ከጀርመንና ኢትዮጵያ የ100ኛ የግንኙነት ዓመት ልደት በዓል በኋላ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩልቲ ግቢ ተከራይቶ በመግባት ማዕከሉን በማደስና በማሳመር አገልግሎቱን በመስጠት ላይ ይገኛል። በሚቀጥለው ዓመትም 50 ኛ ዓመቱን እንደሚያከብር ይጠበቃል ።

የጀርመን ባህል ማዕከል(ጎተ) የተቋቋመበት ዓላማ ‹‹በሁለቱ አገሮች መካከል ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ከሁለቱም አገሮች የባህል ልውውጥ የሚደረግበትና መቀራረብን የምንፈጥርበት ነው›› ሲሉ የጎተ ዓለም ዓቀፍ ዋና ጸሃፊ ፕሮፌሰር ጃኪም ፍሊክስ ሊኦናርድ ተናግረዋል (40th Anniversary Goethe institute ፤2002፤5) ። የባህል ማዕከሉ ፕሮግራም ዳይሬክተር የማዕከሉን መቋቋም ዋነኛ ዓላማም ምን እንደሆነ ሲገልጹ፤

> የሁለቱን አገሮች ባህል ለማስተዋወቅና የባህል ልውውጥ ለማድረግ በተጨማሪም የጀርመን ቋንቋና እውቀትን በዓለም አቀፍ ግንኙነት የማስተዋወቅና የማስፋፋት ዓላማ አለን ። የሃገሪቱን ገጽታ በማሳዬትም የባህልና ኢንፎርሜሽን ትስስርን ለመፍጠር እየሰራን ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የዚህ ማዕከል መቋቋም ዓላማም ከዚህ የዘለለ አይደለም / ወ/ሮ ተናኜ ታደሰ/23/9/2001 ዓ.ም/ ብለዋል።

የጀርመን ባህል ማዕከል ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ዶ/ር ኤልከ ካሽል ሞህኒ ማብራሪያም የጎተ ኢንስቲትዩት ተግባሮች ወይም የተቋቋመበትን ዓላማ የበለጠ የሚያጠናክር ነው።

> ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት።የመጀመሪያው በተለይ በኪነ- ጥበብ እና በትምህርት መስኮች ላይ የአቅም ግንባታ ስራዎችን እንሰራለን ።ሁለተኛው ደግሞ

በኢትዮጵያና በጀርመን እንዲሁም በኢትዮጵያና በሌሎች የአውሮፓ ሃገሮች መካከል የግንኙነት መረብ በመዘርጋት በልዩ ልዩ መስኮች ኮሚኒኬሽን እንዲኖር ማድረግ ነው ። ይሄ ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር ብቻ ሳይሆን መላው የአፍሪካ ሀገሮችም ከአውሮፓ ጋር ግንኙነት ሊመሰርቱ የሚችሉባቸው መስኮች ላይ እየሰራንበት እንገኛለን ። በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የኪነ ጥበብ ስራዎች የበለጠ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቁ ልዩ ልዩ መርሃ ግብሮችን ቀይሰን እየሰራን እንገኛለን (ነጋድራስ ጋዜጣ ጥቅምት 15 ቀን 2003 ዓ.ም.)።

በአዲስ አበባ የተመሰረተው የጎተ ኢንስቲትዩት በዚያን ወቅት ከአፍሪካ የመጀመሪያው የባህል ተቋም እንደነበር ቀደም ሲል ተጠቅሷል። የባህል ማዕከሉ ዋነኛ ጠቃሚ ተግባር በኢትዮጵያ፥ በጀርመንና በአውሮፓ መካከል የባህል ልውውጥን ማድረግ እንዲቻል መስራቱ ነው።በዚህ ግንኙነትም የጎተ የባህል ማዕከል በማደራጀትና በመደገፍ የጀርመንን ባህልና ባህላዊ ሁነቶችን በማስተዋወቅ የባህል ውይይት በሁለቱ ሃገሮች መካከል እንዲፈጠር ሲያደርግ ቆይቷል ።

ለባህል ማዕከሉ መቋቋም የጀርመን መንግስት ዋነኛውን ድርሻ ይይዛል ። የአጼ ኃይለስላሴ መንግስት ፈቃደኝነትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የሁለቱን አገሮች ወዳጅነት ለማጠናከር የተቋቋመው ባህል ማዕከል ከተመረቀ ከሁለት ዓመት በኋላ እ.ኤ.አ.1964 በወቅቱ የጀርመን ፕሬዚዳንት ሄነሪክ ሉብኬ (Heinrich Lubke) አዲስ አበባ መጥተው ጎብኝተውታል። የጀርመን ከፍተኛ ባለስልጣን ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ሚስተር ሉብኬ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ናቸው። ፕሬዚዳንቱ ጎተ የባህል ማዕከልን ሲጎበኙ (History of Ethiopia ) ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ›› እ.ኤ.አ.በ1682 በሂዮብ ሩዶልፍ የተጻፈው መጽሀፍ ሳባቸው፤በዚህን ወቅት ለጀርመንና ኢትዮጵያ ግንኙነትም መሰረት እንደሆነ ተናገሩ (2002፤15) ።መጽሀፉ አሁንም ድረስ በባህል ማዕከሉ ይገኛል።

ዓለም በቀዝቃዛው ጦርነት በሁለት ጎራ በተከፈለችበት ዘመን የምስራቅና የምዕራብ ጀርመን ሁለት ኢምባሲዎች በሃገራችን ተከፍተው ነበር ። የምስራቅ

ጀርመኑ ሌላ የባህል ማዕከል አቋቁሞ እንደነበር ቢነገርም በተጨባጭ በመረጃ የተደገፈ አስረጅ ለማግኘት አልተቻለም ።

In time with worsening of relations to the federal Republic of Germany in the 1970s ,relations to the Grerman Democratic Republic improved. The Emperor had already intiated the rapproachement,and in 1973 came the first Embassy of the GDR led by Ambassader Helmut Gurke(1973-1977).From the late 1970s onward relations became sepecially intensive.The GDR made crucial contributions to the national security and also the civil life. (Ethiopia German100 Years Diplomatic catalogue;102,2005)

ኢትዮጵያ በ1970ዎቹ ከጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ ጋር የነበራትን ግንኙነትና ወዳጅነት በማቀዝቀዝ በአንጻሩ ከምስራቁ ክፍል ከጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ መንግስት ጋር በከፍተኛ ደረጃ ግንኙነት የጀመረችበት ወቅት ነው። የዲፕሎማቲክ ግንኙነቱ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት የተጀመረ ቢሆንም በተከታታዮች ዓመታት ይበልጥ ተጠናክሯል። የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክም በወቅቱ ለነበረው የኢትዮጵያ መንግስት ለአገር ደህንነትና ለሲቪል አገልግሎት ድጋፍ አድርጓል።

ይሁን እንጂ ከዚህ በላይ የተገለፀው የመንግስት ፍላጎት ወደ ምስራቅ ጀርመን ተስቦ የነበረ ቢሆንም፤ የባህል ማዕከሉ ለሁለቱም ኢምባሲዎች አገልግሎት ሲሰጥ እንደነበረ መግለጽ ይቻል ይሆናል። የባህል ማዕከሉ የፕሮግራም ዳይሬክተር ወይዘሮ ተናኜ ታደሰም የሚስማሙበት ሃሳብ ለሁለቱም ኢምባሲዎች የባህል ማዕከሉ በጋራ ሲያገለግላቸው እንደነበረ ነው ።

## 4.2. የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ

የሁለቱን ሃገሮች ባህል፥ኪነ ጥበብና ቋንቋ ለማስተዋወቅና ለማስፋፋት የተቋቋመው የባህል ማዕከል በኪነ ጥበብ ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል። ባህል ማዕከሉ የስነ ስዕል፥ የስነ ጽሑፍ ፥ የሙዚቃ ፥ የተውኔት ፥ የዲዛይን ፥ የፊልም፤የፎቶ ግራፍ ልዩ ልዩ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ለኪነ ጥበብ አፍቃሪያን የጀርመንን ፥ የአውሮፓና የኢትዮጵያን ባህል በማስተዋወቅ መልካም የእውቀት መገበያያ መድረክ ፈጥሯል። አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት ልዩ ልዩ የኪነ ጥበብ ስራዎችን ለህዝብ ይፋ በማድረግ የመማማሪያ መድረኮችን አዘጋጅቷል። የጀርመን ባህል ማዕከል ባለፉት 37 ዓመታት እ.ኤ.አ. 1965 እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ 3,366 የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን ያቀረበ ሲሆን፤በአማካይ በዓመት 91 ዝግጅቶችን አቅርበዋል። በአንዳንዱ ዓመታት ዝግጅቶቹ የሉም የሚባልበት ደረጃ እስከ መድረስ (30 ) እና በሌሎቹ ዓመታት ደግሞ በርካታ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን (188 )ድረስ በማቅረብ የኪነ ጥበብ መድረኮችን አዘጋጅተዋል። እ.ኤ.አ.ከ2001 ዓ.ም ወዲህም ቢሆን እንደ ዳይሬክተሩ የኪነ ጥበብ ዝንባሌ ወደ ፊልም አልያም ወደ ስዕል አለበለዚያም ወደ ስነጽሁፉና ሌሎችም በማዘንበል የተለያዩ የኪነ ጥበብ ዘውጎች እየቀረቡበት መድረኩ እንደቀጠለ ይገኛል 40th Anniversary Goethe institute ፤2002፤26)እና(ደራሲ ዳንኤል ወርቁ 8/10/03) ።

በሃገራችን የሚገኙ ምርጥ የኪነ ጥበብ ስራዎችን በገንዘብና በቴክኒክ ከመደገፍ አንስቶ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሳይቀር ሙያተኛውንና ሙያውን በማስተዋወቅ እና ስልጠና በመስጠት ረገድ ከፍ ያለ ሚና ተጫውቷል።ስለ ልምድ ልውውጡ ዶ/ር ኤልከ ሲገልጹ፤

> እኔ ከመጣሁበት ከ 2001 ዓ ም ጀምሮ እንኳን በአንድ የኪነ ጥበብ ዘርፍ የተካሄዱትን ብናገር፡ የተለያዩ የፎቶ ግራፍ ባለሙያዎች ያነሷቸውን ምስሎች በመሰብሰብ ‹‹አዲስ ፎቶ ፌስቲቫል" የተሰኘ ዓለም አቀፍ ፌስቲቫል ከተባባሪዎች ጋር አዘጋጅተናል ። ይህም በፎቶ ግራፍ ጥበብ ወደ መድረኩ እየመጡ ያሉ ወጣቶች ልምድ

ካላቸው ባለሙያዎች ጋር በማገናኘት የመማሪያ እንዲሁም ልምድና እውቀት የሚለዋወጡበትን መድረክ አዘጋጅተናል (ነጋድራስ ጋዜጣ ጥቅምት 15 ቀን 2003 ዓ.ም.)።

ባለፈው ዓመት በ2002 ዓ.ም እንኳን በተካሄደ የፎቶ ኤግዚቢሽን ላይ አምስት የጀርመን የፎቶግራፍ ተማሪዎች ስራዎቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ አምጥተው እንዲያሳዩ ተደርጓል ። በተመሳሳይም አምስት ኢትዮጵያውያን ወደ ጀርመን መዲና በርሊን ሄደው ስራዎቻቸውን እንዲያሳዩ ተደርጓል ። በዚሁ አጋጣሚ ሁለቱም ቡድኖች የየራሳቸውን ባሉበት ቦታ ቀልባቸው የሳበውን ጉዳይ እንዲያነሱ ተደርገው በሁለቱ አገሮች ያለውን የባህል ልውውጥ/ ትስስር/ ለማሳየት ተሞክሯል ። በዘጋቢ ፊልም፣ በሙዚቃ፣ በስነ ጽሁፍ ፣በስዕል ና በሌሎችም የኪነ ጥበብ ውጤቶች ዙሪያ የልምድ ልውውጥ ተደርጓል ፣ እየተደረገም ይገኛል።

## 4.2.1. ስነ ስዕል

በአገራችን የስዕል ኪነ ጥበብ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ ጥበብ መሆኑ ግልጽ ነው። በተለይም በአብያተ ክርስቲያናት ግድግዳ ፥በሸራ፥ በብራና፥ በወረቀት እና በመስቀሎች ላይ በቀለም ወይም በጭረት፥ ባለ ሁለት ጎን/two dimensional/ ሆነው የሚሰሩ የልዑል እግዚአብሄርን፥ የእመቤታችንን፥ የቅዱሳን መላዕክትን እና ጻድቃንና ሰማዕታትን ማንነት የሚገልጡ መንፈሳዊ ስዕሎች ለዘመናት ሲሳሉ ኖረዋል። የነገስታቱ መልክ፥ ገድልና ድርሳናትም የባህላዊ ስዕሉ ማጠንጠኛዎች ሆነው ቆይተዋል። ባህላዊ ስዕሉ ወደ ዘመናዊ የተሸጋገረበትን ሂደት ምን ገጽታ እንደነበረው ታዬ ታደሰ ሲገልጹ፤

> ከዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ዘመናዊ ስዕሎች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፣ ብዛታቸውም እየጨመረ መጥቷል። ሰዓሊዎችም ከህብረተሰቡ ወገንና አጋር መሆናቸው ቀስ በቀስ በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ ያገኙበት ወቅት ነው ። በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ ከኪነ ጥበብ ዘርፎች ጥሩ የኑሮ ደረጃ ለማግኘት ከሚያስችሉ እድሎች አንዱ ሰዓሊነት እየሆነ መጥቷል ። የተለያዩ

> የህብረተሰብ ክፍሎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ስዕል ሙያ እያዘነበለ በመምጣት ላይ ይገኛሉ ። በንግዱ ዓለም ውስጥ እየዘለቁ በመግባት የመታዬት እድል አገኙ ። ስዕሎች በረከቱ ፤ ሰዓሊዎች ትምህርታቸውን እያጠናቀቁ አካባቢያቸውን ማንጸባረቅ ጀመሩ (ታዬ ታደሰ፤ገጽ 90)።

ይህ ዘመን ከየትኛውም ዘመን ይልቅ ዛሬ ሰዓሊያን የተሻለና ሰፊ እድል የሚያገኙበት ዘመን ነው። የእይታ ጥበባት ዘርፎች በርካታዎች ሲሆኑ፤ ካርቱኖች ፥ ሎተሪንግ ፥ የማስታወቂያዎች ጭብጥ ፥ የመጻህፍት ኢሉስትሬሽን፥የግድግዳ ወረቀቶች ዲዛይን ወዘተ በዚህ ዘርፍ ውስጥ ዘልቀው ከገቡ የዕይታ ጥበብ ዘርፎች ጥቂቶች ናቸው ይላሉ።

እንግዲህ ይህ የጥበብ ዘርፍ የማደጉን ያህል የተመቻቸ መድረክ አግኝቶና ተዋውቆ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ የባህል ልውውጥ ለማድረግ ራሱን የቻለ ጋለሪ ያስፈልጋል ።ይህንን ክፍት ቦታ በመሙላት ረገድ የጀርመን ባህል ማዕከል ከ1967 ዓ. ም ጀምሮ የስዕል ኤግዚቢሽኖች የሚታይበት ስፍራ ሆነ ። ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ የስዕል ኤግዚቢሽኖችን የሚያቀርበው የጀርመን ባህል ማዕከል በዋናነት ከሚታወቅበትና መለያው ከሆነው የስዕል ጥበብ ጋር በስፋት በመስራት ላይ ይገኛል ። የባህል ማዕከሉ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እስኪዛወር ድረስ እራሱን የቻለ የስዕል ኤግዚቢሺን ማሳያ ሳይኖረው በቤተ መጻህፍቱ አዳራሽ ነበር የሚያሳየው ። ወደ ስድስት ኪሎ ከተዛወረ በኂላ ግን ራሱን የቻለ የስዕል ማሳያ ጋለሪ ሊኖረው ችሏል(ዮናስ ታረቀኝ፤ 9/10/03)።

ባህል ማዕከሉ ስመ ጥር ሰዓሊ የሆኑትን ና በጀርመን ሃገር ኮሎኝ ዩኒቨርስቲ የስዕልና ግራፊክስ ጥናታቸውን አጠናቀው በዚያው በስደት አገር ባረፉት በሰዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ ስም ቋሚ የስዕል ኤግዚቢሽን ማዕከል እንዲኖረው አድርጓል ። የገብረ ክርስቶስ ደስታ ቋሚ የስዕል ኤግዚቢሽን መከፈት ለባህል ማዕከሉ ከፍተኛ እመርታ መሆኑን ሰዓሊና ቀራጺ በቀለ መኮንን ይናገራሉ ። በዚህ ብቻ ሳይወሰን ለወጣቶችም ሆነ ለታዋቂ ሰዓሊያን ማዕከሉ እያደረገ ያለውን እገዛ የባህል ፕሮግራሙ ዳይሬክተር ወ/ሮ ተናኜ ሲያብራሩ ፤

የጀርመን ባህል ማዕከል በተለይ ወጣት ሰዓሊያንን ለማበረታታት ፤ በቴክኒክ ፥ በፋይናንስና የስዕል ጋለሪ በማመቻቸት ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጋል ። ለጥሩ ደረጃ ካበቃናቸው ሰዓሊያን መካከል በቀለ መኮንንና በሃይሉ በዛብህ የበለጠ እውቅና ያገኙት በዚህ ነው / ወይዘሮ ተናኘ ታደሰ /23/9/2001 ዓ.ም/ ።

የዶ/ር ኤልክ ካስችል ሞህኒን ሃሳብም ከፕሮግራም ዳይሬክተሯ ገለጻ ጋር ይስማማል፡

በቅርቡ ያለውን ሁኔታ ስመለከተው ብዙ ሰዓሊያን እየመጡ ስራዎቻቸውን ኤግዚቢሽን ከፍተው ማሳዬት እንደሚፈልጉ ያማክሩኛል ። እርግጥ ነው በአዲስ አበባ ውስጥ ኤግዚቢሽን ማሳያ ስፍራ እጥረት እንዳለ የሚታወቅ ሃቅ ነው ።በተለይ ደግሞ በመውጣት ላይ ያሉ ወጣት የስነ ጥበብ ባለ ሙያዎች ናቸው ቦታ እያጡ ያሉት (ዶ/ር ኤልክ ካስችል ሞህኒን/15/2/2003 ዓ.ም.)።

ሰዓሊና ቀራጺ በቀለ መኮንን ከተማሪነታቸው ጊዜ ከ1970ዎቹ አንስቶ በባህል ማዕከሉ ቤተኛ መሆናቸውን ይናገራሉ። በታዳሚነት፤በአቅራቢነትና ከዚያም ፕሮግራሙን በመምራት ተሳትፈዋል።

በባህል ማዕከሉ ቀደም ባሉት ጊዜያት በታዳሚነት ከተሳተፉ ከ1980ዎቹ ጊዜ አንስቶ በቡድንና በተናጠል የተለያዩ የስዕል ኤግዚቢሽኖችን አቅርቤአለሁ። በእነዚህ ጊዜያት የማሳያ ጋለሪውን በማግኘቴ ልደርስ ከምችልበት ደረጃ እንድደርስ እገዛ አድርገውልኛል። ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለበርካታ የስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ባለሙያዎች እድሉን አመቻችተዋል። መድረኮችን በአግባቡ መጠቀም የቻለና የራሱ ጥረትን የሚያክል ባለሙያ እራሱን ወደሚፈልገው ደረጃ ለማድረስ ይረዳዋል (8/10/2003 ዓ.ም)።

በባህል ማዕከሉ ዝነኛ የስዕል ባለሙያዎች ዝግጅታቸውን ያቀርባሉ። እነ ዮሀንስ ገዳሙ፤ጥበበ ተርፋ፤በሀይሉ በዛብህ፤በቀለ መኮንን እና ዘሪሁን የትምጌታ ለአብነት ይጠቀሳሉ።ለኢትዮጵያውያን ሴት የስዕል ባለሙያዎች ማዕከሉ ስፖንሰር ያደርጋል። የሴት የስዕል ባለሙያ ጓደኛሞችን ቡድን እንዲቋቋም በማበረታታት በኩል ማዕከሉ ከፍ ያለ ሚና አለው። በአሁኑ ወቅት ቢያንስ በወር አንድ የስዕል ኤግዚቢሽን በባህል ማዕከሉ ይቀርባል ። ቀጣዩን ትውልድ ለማበረታታት ጥረት ያደርጋል ። ወጣት ሰዓሊያንን ለማበረታታት አርት ኮርነር /Art corner /የሚል ፕሮግራም ከፍቷል (40th Anniversary Goethe institute ፤2002፤22) ። ባህል ማዕከሉ ጥበቡን እያገዘ ያለው የታዋቂና ታዳጊ ኢትዮጵያዊያንን ስዕሎች በማቅረብ ብቻ ሳይሆን ከጀርመን ሃገር የሚመጡና ከፍተኛ እውቀና ያላቸው የታዋቂ ሰዓሊያን የጥበብ ስራዎችን ለኢትዮጵያውያን የጥበብ ሰዎችና ታዳሚዎች በማሳየት ጭምር ነው። ይህም በመሆኑ ባህል ማዕከሉ የስዕል ጥበብ ዓለም አቀፍ አንድምታንና የእድገት ደረጃ ለማስተዋወቅ ከፍተኛ እገዛ እያደረገ ነው።

የባህል ማዕከሉ የቤተመጻህፍትና ዶክመንቴሽን ሃላፊ የሆኑት አቶ ዮናስ ታረቀኝ እንደሚገልጹት ለበርካታ ወጣቶች የስዕል ሙያቸው ላይ ከጀርመን አገር በሚመጡ አሰልጣኞች ስልጠናዎችን በመስጠት እና የራሳቸውን የስዕል ፈጠራ እንዲሰሩ በማድረግ እንዲሁም ጀርመን ድረስ በመውሰድ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። በቅርቡ እንኳን እ.ኤ.አ. በ2008 እና 2009 በዜግነት ኢትዮጵዊትና ጀርመናዊት የሆነች የስዕል ባለሙያ ወ/ሮ እናትፋንታ አባተ ለ12 ወጣቶች የስዕል ስልጠናዎችን በመስጠት የወጣቶችን ስራዎችንና የህይወት ታሪካቸውን የሚገልጽ ካታሎግ እስከ ማዘጋጀት ድረስ የደረሰ ስራዎች ተሰርተዋል። ፍለጋ አርት 1 እና 2 ካታሎጎችን በዋቢነት ይገልጻሉ።

ገጣሚ ትዕግስት ማሞ በባህል ማዕከሉ እየቀረቡ ያሉትን የስዕል የጥበብ ስራዎች በተመለከተ በታዳሚነቷ ያስተዋለችውን ስትገልጽ፤

> የጀርመን ባህል ማዕከል የአውሮፓ ሰዓሊያንን በተለያዩ
> ጊዜያት በማምጣት ስራቸውን ማቅረባቸው
> የአብስትራክት፥ ቢዥዋልና ተራኪ የስዕል ይዘትን ገጽታ

የሃገራችን ሰዓሊያን እንዲገነዘቡ የራሱን ሚና ተጫውቷል (15/10/2001 ዓ.ም)።

ዮሐንስ ገዳሙ በጀርመን ባህል ማዕከል በተደጋጋሚ የስዕል ኤግዚቢሽኖችን በማቅረብና የስዕል ፍላጎት ባላቸው አድናቂዎቹ ዘንድ ማዕከሉ በሚሰጠው መድረኮችን በመምራት ውይይቶችን አቅርቧል ። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን የቴሌቪዥን ጣቢያ ኪነ ጥበብ ፕሮግራም አዘጋጅ ፋንታሁን ኤራቦ ከስምንት ዓመታት በላይ በፕሮግራሙ ላይ ሲሰራ የተረዳውን ሲገልጽ ፤ ‹‹በጀርመን ባህል ማዕከል ከሚቀርቡት የኪነ ጥበብ ስራዎች መካከል ሰፊ ሽፋን በመስጠትና ደረጃውን ከፍ በማድረግ በኩል ወደ ስዕሉ ያደላሉ›› ይላል ። በሚቀርቡት የስዕል ኤግዚቢሽኖች ላይ የሚሰጠው ሙያዊና አካዳሚያዊ አስተያየት ና ሞቅ ያለ ውይይት ለጥበቡ ማደግና ከፍ ማለት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ይናገራል ። በተለይም ለአገር ውስጥ ሰዓሊያን ጋለሪውን ከማዘጋጀት አንስቶ፥ የገንዘብ ና ቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት እንዲሁም ተጋባዦችን በፖስተር፥ በኢንተርኔትና በስልክ በመደወል በጥበቡ ዙሪያ እንዲታደሙ ማዕከሉ የዘረጋው አሰራር ለጀማሪ ሰዓሊዎች መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር ነው ። አዳዲስ ሃሳቦችና የአሳሳል ፈጠራዎችን ለማስገንዘብም ስመ ጥር የሆኑ ሰዓሊያንን ከጀርመን ሃገር በማስመጣት የጥበብና የባህል ሽግግር ወይም ልውውጥ በማድረግ ላይ ይገኛሉ (ፋንታሁን ኤሪቦ 15/10/03) ።

ሰዓሊ በቀለ መኮንን በአሁኑ ወቅት ለደረሱበት ዝናና ደረጃ እንዲደርሱና በዓለም አቀፍ መድረኮችም ኤግዚቢሽኖችን እንዲያዘጋጁ የጀርመን ባህል ማዕከል ከፍ ያለ ድጋፍ እንዳደረገላቸው ይናገራሉ ።

ጎተ ባህል ማዕከል ዕውነተኛ የጥበብ ቦታ ነው። ደረጃው ከፍ ያለ ቦታ። የእኛ ሙያ ኪነ ጥበባዊ ዋጋው ከፍ እንዲልና ህብረተሰቡ የጥበቡ ፍቅር እንዲኖረው ያልተቋረጠ ድጋፍ አድርጓል ። ደረጃዎችን በማዘጋጀት የስዕል ሙያ ጥራት ያለውና ተቀባይነቱም እንዲያድግ በጥንቃቄ የሚሰራበት ባህል ማዕከል ነው ። አሁን ደግሞ ወደ ዩኒቨርስቲው ግቢ መግባቱ እውነተኛ አካዳሚያዊ ቦታ እንዲሆን አድርጎታል ። የስዕል ጥበብ እኮ

> በአገራችን አሁን አሁን መሻሻል እየታዬ መጣ እንጂ የትኛው ኢትዮጵያዊ ነው ሥዕልን አይቶ የሚያደንቀው ? የትኛውስ ነው ሥዕል ገዝቶ ወደ ቤቱ የሚወስደው ? አየህ ! ጎተ ለባለሙያውም ሆነ ለጥበብ አፍቃሪው የመገናኛ መድረክ ሆኖ ጥበቡ እንዲያድግ አግዞናል ። ዛሬ ለወጣት ሰዓሊያን መድረኩ የተመቻቸ ነው ። ለጥበብ ባለሙያተኛው መድረኩን ከመስጠት አንስቶ ፤ ፖስተር አሳትሞ በማሰራጨትና አድናቂዎችን በመጋበዝ ከፍ ያለ እገዛ ያደርጋል (ሰዓሊ. በቀለ መኮንን/8/10/03 ዓ.ም)።

ደራሲ ዳንኤል ወርቁ ከሙያቸው በተጨማሪ የስዕል አፍቃሪና ታዳሚ በመሆን ለረጅም ዓመታት ተከታትለዋል። የባህል ማዕከሉ የራሱን የስዕል ደረጃ ለመጠበቅ ያደርግ በነበረው ጥረት ግን ባለሙያው ለአላስፈላጊ እንግልት ይጋለጥ እንደነበረ ይናገራሉ።

> በተለይ በደርግ ዘመን የግል ሥዕል ጋለሪ ማቅረቢያ ባለመኖሩ ባለሙያው ወደባህል ማዕከሉ በሚቀርብበት ወቅት እነ እከሌ ይመስክሩልህ የሚለው አሰራር ለባለሙያው አስቸጋሪ ነበር። መስካሪ የተባሉት መልካም ነገር ባለመናገራቸው ምክንያት የተጎዱ ሙያተኞች ነበሩ። በዚህም ምክንያት የግል ጋለሪዎችም ለመከፈት የተገፋፉበት አጋጣሚዎች ተፈጥሯል። አሁን ይሄ ችግር የለም ። መስራት የሚፈልግ መድረኩ የተመቻቸ ሆኗል። ችግሩ መድረኮችን በአግባቡ ያለመጠቀም ነው።በተለይም ወደ ውጭ አገር ሄደው የሚመለሱ ወጣቶች የራሳቸውንና የራሳቸውን ያልሆነን ነገር ለይቶ ባለመረዳት ሙያቸውንና የስልጠና ትርጉሙን የማዛባት ችግር ይስተዋላል(ደራሲ ዳንኤል ወርቁ 8/10/03)።

የጀርመን ባህል ማዕከል ለስዕል ጥበብ ዕድገት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ከፍተኛ መሆኑን የጥናቱ አጥኚው በቦታው በተመላለሰባቸው ጊዜያት ባለሙያተኞችን፤ዝግጅታቸውንና ታዳሚውን በመመልከት የተረዳው እውነታ ነው ።

## 4.2.2. ስነ ጽሑፍ

በጀርመን ባህል ማዕከል ከሚቀርቡት የኪነ ጥበብ ስራዎች መካከል ስነ ጽሑፍ አንዱ ነው ። በዚህ ንዑስ ክፍል የሚቀርቡ የግጥም ምሽት ዝግጅቶች ፥ የአጫጭር ልቦለድ አጻጻፍና ሂስ፥ የግጥም ንባቦች ፥ የትርጉም ስራዎች፥ የህጻናት ታሪኮች፥ ወጎች፥ ቃለ ተውኔቶች ፥ ቅኔዎች ፥የታሪክ መጣጥፎች፥ልዩ ልዩ ድርሰቶችን፥የፐሬስ ሰርክሎች፥ታሪካዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ሃይማኖታዊ ጽሑፎች ሳይቀር የሚቀርቡበት መድረክ ነው ።

ከታዋቂና አንጋፋ ጸሀፊዎች ወይም ደራሲዎች እስከ ወጣት የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ድረስ በማዕከሉ ስራዎቻቸውን እያቀረቡ ይገኛሉ ። በእነዚህ መድረኮች በሚቀርቡ የስነ ጽሑፍ ስራዎች ታዳሚው ተደስቶና ተደንቆ የሚሄድባቸው ቦታ ብቻ አይደሉም ። ይልቁንም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ከኮተቤ የትምህርት ኮሌጆች እንዲሁም ከዩኒቨርስቲዎች ውጪ ባሉ የስነጽሁፍ ባለሙያዎች፥ ሃያሲዎች ፥ደራሲዎችን በመጋበዝ የስነ ጽሑፍ፥የቲያትሪካል ጥበብ ፥የጋዜጠኝነት፥ የታሪክ ና የማህበረሰብ ትምህርት ክፍሎች መምህራን ውይይቱን በመምራት እና አካዳሚክ ትንታኔዎችን በመስጠት ታዳሚው በኪነ ጥበቡ ዙሪያ የጠለቀ እውቀት የሚገበይበት መድረክን መፍጠር ችሏል።ለዚህ አባባል አብነት የሚሆነው ከዚህ በታች የተገለጸው መረጃ ነው።

> በባህል ማዕከሉ በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ የስነ ጽሁፍ ምሽት/ውሎ/ ቀን አለን ።እስካሁን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህሮቹ ዶክተር ዮናስ አድማሱ፥ ዶክተር ፈቃደ አዘዘ ፥አቶ ዘሪሁን አስፋው፥ አቶ ደረጀ ገብሬ ፥ አቶ ተስፋዬ ገሰሰ፥ አቶ አሰፋ ወርቁ፥ ያቀረቡ ሲሆን ፤ከዩኒቨርስቲው ውጪም ወ/ሮ ውዳላት ገዳሙ፥ አቶ ግርማ በሻህ፥ነብይ መኮንን፥ፍቅረ ማርቆስ ደስታ ፥ ዳንኤል ወርቁን

የመሳሰሉ አንጋፋ የጥበቡ ምሁራን ለሁለት ዓመት ልዩ ልዩ ስነ ጽሑፋዊ ጉዳዮችን አቅርበዋል ። አሁንም በማቅረብ ላይ ይገኛሉ ። ራሳቸው ከሚያቀርቡት በተጨማሪ ወጣት የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች በሚያቀርቡት ጽሁፍ ዙሪያ ሙያዊ ትንታኔና ውይይት በመስጠት ለኪነ ጥበቡ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል (ወ/ሮ ተናኜ ታደሰ/23/9/2001 ዓ.ም) ።

ባህል ማዕከሉ በሥነ ጽሁፍ መርሃ ግብሩ ከጀርመን የትርጉም ስራዎች ንባብ በተጨማሪ የኢትዮጵያውያን ስራዎች ብቻ በሆኑና አካዳሚያዊ ውይይቶችና ትምህርቶች የተላለፉባቸው መርሃግብሮችን በመዘርጋት እ.ኤ.አ.ከ1999 እስከ 2002 አቶ ዘሪሁን አስፋው ፤ ከ2003 እስከ 2005 ዶክተር ፈቃደ አዘዘ መርሃግብሮችን በመምራትና በማዘጋጀት ለስነ ጽሁፍ ኪነ ጥበብ ሙያዊ እውቀታቸውን ለጥበቡ ባለሙያዎችና ታዳሚዎች አስተላልፈዋል። ካቀረቧቸው ዝግጅቶች መካከል የተወሰኑትን መጥቀስ መረጃውን የበለጠ ያዳብረዋል።

እ.ኤ.አ.ሚያዚያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ‹‹የኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ በመጪው ሚሊኒየም ያለበት ፈተና›› በሚል ርዕስ አቶ ዘሪሁን አስፋው ባዘጋጁት መርሃ ግብር ደራሲ ጸሐይ መላኩና ሐይለ መለኮት መዋዕል፥ የአጭር ልቦለድ ጸሐፊ የዝና ወርቁና ሳሙኤል ልጅ ዓለም ያቀረቡት የስነ ጽሁፍ ዝግጅትን ማንሳት ይቻላል ። በዚሁ ዓመት ከግንቦት 10 እስከ 14 ድረስ በአቶ ዘሪሁን አስፋውና ከጀርመን በመጣው ሚስተር ሚካኤል ሂውልስ የጎተ ግጥሞች ትርጉም አውደ ጥናቶች ተካሂደዋል።እ.ኤ.አ. ሚያዚያ 2000 ዓ.ም.በአቶ ዘሪሁን አስፋው አርታኢነት ዘሪሁን አስፋው፣ብርሃኑ ገበየሁ፣አሰፋ ወርቁ፣ ፋንታሁን እንግዳ፣ ፍቅረ ማርቆስ ደስታ፣ ወ/ሮ ሙሉ እመቤት ዘነበ፣ ማንያዘዋል እንደሻው፣ ተስፋዬ ገሰሰ እና አቶ ነብይ መኮንን ተርጓሚነት የወልፍ ጋንግገተ፣ ፍሬድሪክ ሽልድሪን፣ የነጆሴፍ ቮን አይሽንዶርፍ፤ሄነሪክ ሃይነ፤ ራይነ ማሪያ ሬልከ፤ ፖውል ሴላን፣ ቤልቶርተ ብሬኽት፣ ጉንተር ግራስ፣ አንስማጉንስ ሂንሴንስበርገር፣ የግጥም ስራዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አማርኛ ተተርጉመው በሃገር ፍቅር ቲያትር ቀርበዋል (ሙሉ ዝርዝሩን በአባሪ 1 መግለጫዊ መዘርዘር ላይ ይገኛል)።

አቶ ዘሪሁን አስፋው ስላቀረቧቸው ዝግጅቶች ሲያብራሩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዲን በነበሩበት ወቅት ናታሺያ ዜሊንገር ከተባለች የባህል ማዕከሉ ዳይሬክተር ጋር በነበራቸው ግንኙነትና የስነ ጽሑፍ ባለሙያ ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በርካታ ውጤታማ ስራዎችን አዘጋጅተዋል፡፡ ከትርጉም ስራዎች ጀምሮ የነበረውና ያዘጋጇቸውን ዝግጅቶች በተመለከተ የሚከተለውን ገልጸዋል፡፡

> እኔ ያዘጋጀሁት አንዱ ትልቁ ስራ የጀርመን ቅኔያት በሚል የጀርመን ግጥሞችን ወደ አማርኛ የተረጎምነውና የታተመው ነው፡፡ ከሚስ ናታሺ ጋር በነበረን ግንኙነት የጎተን 250 ኛ ዓመት ልደቱን ምክንያት በማድረግ የሱን የሥነ ግጥም ስራዎችን ለህዝብ ለማስተዋወቅ ነበር ፡፡ ግጥሞች ለመተርጎም ነበር ሃሳቤ፤ በኂላ ተወዳጅ የሆኑ ሌሎችንም የጀርመን ገጣሚያን ስራ በእንግሊዘኛ የተተረጎሙትን እንድመርጥ ተስማማን ፡፡ መረጥኩ፡፡ ከዚያ በኂላ በትርጉሙ ላይ የሚሰሩትን ሰዎች መረጥኩ፡፡ ስለትርጉም ስልጠና ሰጠሁ፡፡ ከጀርመን የመጣው ሚስተር ሚካኤል ሂውልሰም ስልጠና ሰጠ፡፡ በመጨረሻም 34 ግጥሞች ተተረጎሙ (15/10/03)፡፡

ከትርጉም ግጥሙ በተጨማሪ፤የሴት ደራሲያንን ለማበረታታት የተወሰኑ ሴቶች ደራሲዎችን ስልጠና በመስጠት፤የአጭር ልቦለድ ጸሐፊዎችን በመጋበዝ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ በማድረግ፤የኪነ ጥበብ አርት ሂስ ምን እንደሚመስል የኢትዮጵንና የጀርመንን የተመለከትንበት፤በሌላ በኩል ደግሞ በጀርመን ኢምባሲ ባልደረባ ማስዝ ሹግረፍ የተባሉት የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያንን ስራ በእንግሊዘኛ በመተርጎም በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ለማድረግ በነበራቸው ፍላጎት፤ከባህል ማዕከሉ ጋር በመተባበር ለሙከራ የአንድ ሴት ደራሲያንን አንድ አጭር ልቦለድ አቶ ዘሪሁን አስፋው እንዲመርጡ በማድረግ የየዝና ወርቁን “የመመረቂያው ልብስ” የሚለውን ወደ እንግሊዘኛ ለመተርጎም ተችሏል፡፡ የተተረጎመውም ስራ በውጭ አገር ዜጎች ዘንድ ሊሆን ይችላል በሚል ሀሳብ በእነ ሹግራፍ መኖሪያ ቤት የተጋበዙ እግንዶች በተገኙበት ደራሲዋ እንድታነበው ተደርጓል፡፡ በወቅቱም የተገኙት እግዶች ድርሰቱን

እንደወደዱት ታውቋል። (Reporter News paper April 2,1997)። እንደታሰበው የሌሎቹ ሴት ደራሲዎችን ሥራ በዚህ አይነት አስተርጉሞ ለማሳተም እቅድ ቢያዝም እነሹግራፍ የሥራ ጊዜያቸው በመሄዳቸው የታቀደው የማሳተም ሀሳብ ሳይቀጠልበት ቀርቷል (ዘሪሁን አስፋው 15/10/03 ዓ.ም.)። የአቶ ዘሪሁን አስፋው ዝግጅት በሥነ-ጽሁፋዊ ሂስ ላይ የተደረገ ነው። ይህንንም እሳቸው እንዲህ ገልጽውታል።

> ሥነ-ጽፋዊ ሂስ በወቅቱ ብዙ ሀሳቦች ይሰነዘሩ ስለነበር ከማዕከሉ ዳሬክተር ጋር ተመካክረን አንድ የሥነ-ጽፋዊ ሂስ ኘሮግራም እንዲዘጋጅ ተስማማንና በዚህ መሠረት እኔ በኢትዮጵያ ያለውን የሥነ-ጽሁፍ ሂስ ሁኔታ ምን እንደሚመስል አጠቃላይ ቅኝት አቀረብኩ። ከጀርመን የመጡት ክርስቶፎር ብላስ የተባሉት በጀርመን ስላለው አጠቃላይ ሂስ ገለፃ አደረጉ (ዘሪሁን አስፋው 15/10/03 ዓ.ም.)።

በሃምሌ 6 2000 ወ/ሮ ኢሌኒ መኩሪያ በመራችው መርሃ ግብር ፊርማዬ አለሙ በአማርኛ ግጥሞቿን ስታነብ ሳራ ክሪሽ ወደ እንግሊዘኛ ተርጉማ በማንበብ የስነ ፅሑፍ ዝግጅቶችን አቅርበዋል። የህጻናት መጻህፍት በኢትዮጵያ አውደ ጥናቶችን ሪናቲ አህረንስ ክራመር በዚሁ ወቅት ሰጥተዋል። እ.ኤ.አ 28/5/01 ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ጋር በመተባበር በአጭር ልቦለድ አጻጻፍ ዙሪያ የትርጉም አውደ ጥናት ተካሂዷል።እ.ኤ.አ.23/4/02 በኢትዮጵያ የህጻናት መጻህፍት ደራሲዎች የተደረሰው ‹‹አኩኩሉ›› መጽሐፍ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

ዶክተር ፈቃደ አዘዘ ካዘጋጇቸው የስነጽሁፍ ዝግጅቶች መካከልም በ28/1/2003 ዓ.ም ዶ/ር ዮናስ አድማሱ የራሳቸውን ግጥሞች ያቀረቡበት የግጥም ንባብ ጊዜ፤በ20/3/2003 ዓ.ም.የተመረጡ የገጣሚና ጸሐፊ ተውኔት ደበበ ሰይፉ ግጥሞችና የህይወት ታሪክ የቀረበበት፤በ15/32003 ዓ.ም. የተመረጡ የሰይፉ መታፈሪያ ግጥሞችና ስራዎቹ ዙሪያ የቀረበበት፤በ23/10/2003 ዓ.ም.የተመረጡ የገ/ክርስቶስ ደስታ ግጥሙና ስዕሉ አጠቃላይ የህይወትና የስራ ልምዱ የቀረበበት፤በ26/2/2004 የወጣቶች ድምጽ ክፍል አንድ የሶስት ወጣት ሴቶችና ሁለት ወጣት ወንዶች ያልታተሙ ግጥሞቻቸውን ያቀረቡበትና ውይይት የተካሄደበት በጥቂቱ ይጠቀሳል(ሙሉ ዝርዝሩን በአባሪ 1 መግለጫዊ መዘርዝር ላይ ይገኛል)።

በወቅቱ ይቀርቡ ስለነበረው ዝግጅትና ስለተዘጋጀው ዝግጅት የተገኘውን ውጤት አስመልክቶ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ሲገልጹ፤

> እኔ በወቅቱ አቀርባቸው የነበሩት የስነ ጽሑፍ ዝግጅቶች ውጤት አግኝቸባቸዋለሁ፡፡ያን ጊዜ ጀማሪ የነበሩ የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ናቸው ዛሬ ታዋቂ ደራሲ ሆነው የምናያቸው፡፡ ያኔ በማቀርባቸው ስራዎች ጊዜ ተወስደና በጥንቃቄ የሚካሄዱ በመሆናቸው በርካታ ታዳሚዎች ነበሩ፡፡ በሌሎች ዝግጅቶች ላይ የማታዬውን የታዳሚ ቁጥር አዳራሹ ጠቦ ከጫማ ስር ቁጭ ብለው የሚከታተሉ የጥበቡ አፍቃሪዎች ነበሩ፡፡በርካታ ታዳሚዎች ቦታ አጥተው የሚመለሱም ነበሩ፡፡ዝግጅቶች ከቀረቡ በኂላ ይቀርቡ የነበሩ አካዳሚያዊ ውይይቶችና አስተያየቶች እጅግ ጠቃሚዎች ነበሩ፡፡ ይደገሙ የሚባሉ የስነ ጽሑፍ ዝግጅቶች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ የገብረ ክርስቶስ ደስታን መጥቀስ ይቻላል (20/10/03 ዓ.ም.)፡፡

ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ባቀረቧቸው የስነ ጽሑፍ ዝግጅቶች ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ላይ ብቻ ያተኮሩ ከመሆናቸውም ባሻገር የስመ ጥር የስነ ጽሑፍ ሰዎች የግጥም ስራዎቻቸውና ታሪካቸው ያቀረቡበት መድረክ ለብዙ የጥበቡ አፍቃሪነን ፤ጀማሪ የስነ ጽሁፍ ባለሙያዎች ጥሩ የመማሪያ መድረክ ነበር፡፡ከዚህ ጎን ለጎን የወጣቶችን ስራ በተለያዬ መልኩ እንዲያቀርቡ የተደረገበትና የአማርኛ-አረብኛ ስነ ጽሁፉ ተወዳጅ ዝግጅቶች እንደነበሩ ዶ/ር ፈቃደ ያስረዳሉ(20/10/03 ዓ.ም.)፡፡

የባህል ማዕከሉ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይወሰን በክልሎች ጭምር የስነጽሁፍ ዝግጅቶች እንዲቀርቡ በማድረግ ለኪነ ጥበቡ እድገት በትጋት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡የጀርመንን ስነ ጽሁፎች/ አጫጭር የልቦለድ ታሪኮች በታዋቂ ጸሀፊዎች ወደ አማርኛ በመተርጎም ከዚያም ግምገማ እና ውይይት ተደርጎባቸው የማተሚያ ወጪያቸው ተችለው ለህትመትና ስርጭት በቅተዋል ፡፡ በዚህ ላይ አንድ መረጃ አቀባዬ ዝርዝር ማብራሪያ ሰጥተውኛል፡፡

ባለፉት ዓመታት እ.ኤ.አ.በ 2010ዓ.ም. ከህግ ፊትና ሌሎች አጫጭር የጀርመን ልቦለድ ታሪኮች በሚል በዮናስ ታረቀኝ፣ዳንኤል ወርቁ፣ፍስሃ ሳህሉና አስቻለው ከበደ የተተረጎመ መጻህፍ ታትሟል። አያ ተንኮሉ የሚል የህጻናት ተረት በ2008 ዓ.ም. በዮናስ ታረቀኝ ተተርጉሞ ታትሟል። ጉረኛው አውራ ዶሮ እና ሌሎቹ በ2011ዓ.ም በሙሉ ወርቁ ተተርጉሞ ታትሟል። የጀርመን ቅኔያት ከወልፍ ጋንግ ገተ እስከ ጉንተር ግራስ በሚል በአቶ ዘሪሁን አስፋው አርታኢነት፣ብርሃኑ ገበየሁ፣ፍቅረማርቆስ ደስታ፣አሰፋ ወርቁ፣ፋንታሁን እንግዳ፣ተስፋዬ ገሰሰ ፣ማንያዘዋል እንደሻው እና አቶ ነቢይ መኮንን በ1993 ዓ.ም.ተርጉመው ለህትመት በቅቷል።ጥንቸል እሸኑከር እና ሌሎቹ አጫጭር የጀርመን ተረቶች መጽሀፍ ሁለት በሙሉ ወርቁ በ2011ዓ.ም. ተተርጉሞ ታትሟል። መንገድ ስጡኝ ሰፊ የግጥም ትርጉም በ2006 ዓ.ም.በሄራን ሠረቀ ብርሃን ተተርጉሞ ታትሟል። የቤርቶልት ብሬንት የዘመናት ታሪክ በ1997 ዓ.ም በበየነ ወ/ገብርዔል ተተርጉሟል። ኩኩሉ ተረቶች ለህጻናት በሚል ርዕስ አሉላ ፓንክረስት፣ፊርማዬ  አለሙ፣ማጫ  ጫማ  አርጋቸው፣ማይክል ዳንኤል፣ናታሻ ስሊንጋር፣ሪናቴ አህረንስ፣ ሳሙኤል ልጅ ዓለም፣ተስፋዬ ገ/ማርያም፣ተስፋዬ ገሰሰ እና የወይንእሸት አስፋው በ2002 ዓ.ም. ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር ታትሟል ። የወጣቱ ቨርተፍ ሰቀቀኖች እ.ኤ.አ.በ2004 በተስፋዬ ገሰሰ ተተርጉሞ በመጽሃፍ ታትሟል። ቴአትርም ተሰርቷል። ናትናኤል ጥበቡም እ.ኤ.አ በ2000 ዓ.ም በነብይ መኮንን ተተርጉሞ በመጽሃፍ መልኩ ታትሟል ፣ቴአትርም ተሰርቷል(ደራሲ ዳንኤል ወርቁ 8/10/03 እና ዮናስ ታረቀኝ 9/10/03) ።

የሰዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታን ታሪክ ግጥሞችንና ስዕሎችን የሚገልጽ ‹‹ The Painter and Poet ››በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. በ 2006 ዓ.ም ካታሎግ መጽሀፍም ታትሟል። የጀርመን ባህል ማዕከል መጽሐፍትን በማሳተም በኩል ትልቅ ድጋፍ ማድረጉን አቶ ዘሪሁን አስፋው የሚስማሙበት አስተያየት ነው(15/10/03)።

ከህትመት ስራው ሌላም የጀርመን ባህል ማዕከል ከ 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ‹‹አዲስ አበባ ታንብብ›› የሚል ፕሮጀክት በመቅረጽ የንባብ ባህል እንዲዳብር በሚካሄደው ስራ ላይ ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል። አዲስ አበባ ታንብብ ፌስቲቫል በኢትዮጵያ አንባቢ ትውልድ የመፍጠርን ራዕይ የሰነቀ ሲሆን ፣ የንባብን ባህል በተለይም በህጻናት እና ወጣቶች ዘንድ የማስረጽ፣ አዋቂዎችም

እንዲያነቡ የማነቃቃት ዓላማዎች እንዳሉት አቶ ዳንኤል ወርቁ ይናገራሉ ። በዚሁ የንባብ ባህል እንዲዳብር በሚደረገው እንቅስቃሴ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ከሚገኙ ት/ቤቶች ለተውጣጡ ህጻናት ተማሪዎች የተመረጡ ድርሰቶችን የሚነበቡበት ዝግጅቶች ተካሂደዋል ። ታዋቂ ግለሰቦች በተመረጡ ት/ቤቶች ለተማሪዎች ድርሰቶችን አንብበዋል። የመጻህፍት አውደ ርዕይ፣ የኪነ ጥበባት ምሽቶች ተካሂደዋል ። በዚህ የንባብ ልምድን የማዳበር መርሃ ግብር ከአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ የክልል ከተሞችም እየተሳተፉ እንደሚገኙ ይናገራሉ። የንባብ ፌስቲቫሉ ዓላማ በአብዛኛው የከተማው ነዋሪ የንባብ ባህልን ለማስረጽ የተመረጡ ግጥሞችና አጫጭር ልቦለዶች የተቀረጸባቸው ኦዲዮ ሲዲዎች ለሕዝብ በነጻ ተሰራጭተዋል ። በየሁለት ወራቱ በሚቀርበው የንባብ ፕሮግራም የጀርመንን ስነ ጽሁፍ ቴክኒክና ታሪኮችን እንዲሁም አጻጻፎችን እንዲረዱ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል። ተማሪዎችም የራሳቸውን ታሪክ እንዲጽፉ ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪ ከህግ ፊትና ሌሎችም የጀርመን አጫጭር ልቦለዶች ከሚለው የትርጉም ስራዎች ታሪኮች መካከል አራት ስራዎች(ገራፊው፣ጠረጴዛ ጠረጴዛ ነው፣ ቀይዋ ድመት እና ከህግ ፊት ) የሚሉት ሰዓሊያን በብሩሽ፣የሙዚቃ ባለሙያዎች በድምጽ እንዲሁም የዳንስ ባለሙያዎች በእንቅስቃሴ እንዲገልጽዋቸው ተደርጓል (ዳንኤል ወርቁ 9/10/03)።

አቶ ዮናስ ታረቀኝ የተባሉ መረጃ ሰጪዬም ‹‹ የንባብ ባህልን ለማዳበር መሰራት ያለበት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ በመሆኑ የኢትዮጵያ ታንብብ ብሄራዊ የንባብ ቀን እንዲኖረን እስከ ማድረግና የእኛን አርአያነት ተከትለው የቋንቋ ሰዎችና የቤተ መጻህፍት ባለሙያዎች በያሉበት ስራውን እንዲያስፋፉት ነው የምንሰራው ይላሉ ። ለዚህም መምህራንን አሰልጥነናል ። እኛ በሰልፍ ላይ በምናደርገው የታሪክ ንባብ ብቻ ሳይሆን በራሳቸው የስነ ጽሑፍ ንባብ እንዲቀጥሉ ነው የምንፈልገው ። እስካሁን በአዲስ አበባ በ10 ትምህርት ቤቶች በሳምንት ለአምስት ቀናት የንባብ ፕሮግራም ተካሂደዋል። በአዳማ ፣ መቀሌ፣በዲላ፣ሃዋሳ፣ድሬዳዋ ከተሞች የንባብ ፕሮግራሞች ተካሂደዋል ። በቀጣይ በየከተማቸው ከተማችን ታንብብ የሚል ፕሮጀክት ቀርጸው እንዲመጡ ጥያቄ አቅርበንላቸዋል ሲሉ ያብራራሉ››(8/10/03)።

በባህል ማዕከሉ ከሚቀርቡ የስነ ጽሑፍ ስራዎች መሳ ለመሳ ማህበራዊ ጉዳዮች እየተነሱ የውይይት መድረክ ሆነው የቀረቡበት ጊዜም ቀላል አይደለም ። በተለይም ኢትዮጵያ የምትታወቅበትንና ለዓለም ምሳሌ ትሆንባቸዋለች ተብሎ በሚነገረው የሃይማኖት መቻቻል ላይ ሰፊ ጊዜ የወሰዱ መድረኮች ተዘጋጅተዋል ። ሃይማኖት እየተገለጸ÷ታሪካዊ ትስስር እየተደረደረ÷ ስነ ጽሑፋዊ እንድምታዎች እየተተነተኑ÷ማህበራዊ መስተጋብሩና ትውፊታዊ አመክንዮዎች በአንድምታ እየተፈቱ ውይይቱን ለማቅረብ ተችሏል። በህብረተሰቡ ዘንድ የቆየውን የመቻቻል ባህል አጉልተው በማውጣት ለሌሎች አገሮች የኢትዮጵያን ልምድ የሚያስተዋውቁበትን አጋጣሚ ፈጥረዋል (ደራሲ ዳንኤል ወርቁ 8/10/03፤አቶ ዮናስ ታረቀኝ 9/10/03)።

በማዕከሉ በርካታ የጥናት መርሃ ግብር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፤ ከኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ጋር በማከናወን ተከታታይ የሆኑ ዝግጅቶችን በማካሄድ ላይ ነው ። ‹‹ዘመናዊነት በኢትዮጵያ›› የሚሰኝ ወርሃዊ ፕሮግራም በመቀረጽ ወርሃዊ መርሃግብር የምርምር ስራዎችን በማቅረብ ላይ ይገኛል ።በእነዚህ የምርምርና የውይይት መድረኮች ስነ ጽሑፍና ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ለውይይት ይቀርባሉ። በፕሬስ ዳይጀስትና ሰርክል ላይ በባለሙያዎች ሰፊ ውይይቶች ተካሂደዋል ።

በዲሞክራሲ ÷በወጣትነት ÷ በዘመናዊነት በመሳሰሉት ርዕሶች የውይይት መድረኮች ተፈጥረዋል ። ማዕከሉ ከውይይቶች በተጓዳኝ የኢንሳይክሎፒዲያ ኢትዮፒክ እንዲዘጋጅና እንዲታተም እገዛ አድርጓል ። ለአንዳንድ አንጋፍና ጀማሪ ደራሲያን የስነ ፅሑፍ ና የምርምር ስራዎችን በማሳተም አልያም የመጽሀፉን የምረቃ ወጪና ተጋባዦችን በመጥራት ለኪነ ጥበቡ ማደግ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል። የንባብ ባህል እንዲያድግ ‹‹ አዲስ አበባ ታንብብ›› በሚል የዘመቻ ርዕስ ሰፊ የሆነ የንባብ ሳምንታትን ማዕከሉ አከናውኗል ።እዚህ ላይ የአንዳንድ ታዳሚዎችን አስተያየት ማየቱ ሃሳቡን የበለጠ ያዳብረዋል። በእነዚህ የንባብ ሳምንቶች በርካታ የልብ ወለድ÷ ትምህርታዊ ና ታሪካዊ መጻህፍት ለንባብ ቀርበዋል ። በተለያዩ የስነ ጽሑፍ ውጤቶች ላይም ውይይቶችን በማካሄድ የንባብ ባህል ልምድ እንዲዳብር አድርገዋል። በእነዚህ ዝግጅቶች ወጣትና ጀማሪ ደራስያን የፈጠራ ስራዎቻቸውን በማቅረብ÷ የግጥም እና ሌሎች የስነ ጽሑፍ ስራዎቻቸውን ለታዳሚዎቻቸው ከማቅረባቸውም ባሻገር አንዳንድ ስራዎቻቸውን በማስመረቅ ከጥበብ አፍቃሪያን ጋር ፊት ለፊት የሚገናኙበትን መድረክ

አመቻችተውላቸዋል ። በዚህም እንደታዳሚ በርካታ ትምህርቶች ቀስመናል(ዘሪሁን መኮንን፤ዘሃራ ሰይድ 7/10/03) ።

በጎተ ባህል ማዕከል የስነ ጽሑፍ ስራዎችዋን ካቀረቡት ወጣት ገጣሚዎች መካከል ገጣሚ ትዕግስት ማሞ ትገኝበታለች።ትዕግስት የማዕከሉን አስተዋጽኦ ስትገልጽ ለጥበብ ዕድገትና ማበብ ከፍ ያለ ሚና እንዳላቸው እያስረዳች ነው ።

> የጀርመን ባህል ማዕከል መድረክ ለስራዎቼ መሰረት ነው። ከመድረኮቹ ያገኘኋቸው ጭብጨባዎች፥ ሂሶች፥ ትችቶችና ምስጋናዎች ለዚህ እንዳበቁኝ ይሰማኛል። ለበርካታ ወጣት ደራስያን እጃቸውን ለማፍታታትና ከአንጋፋ ጸሃፊዎች እውቀትና ልምድ የምንገበይባቸው መድረኮች ናቸው ። አሁንም ቢሆን ለእነዚህ ባህል ማዕከላት ያለኝ አክብሮት በሚያዘጋጁት ልዩ ልዩ የኪነ ጥበብ ስራዎች እንድከታተላቸው ና ጥሩ እውቀት እንዳገኝባቸው ስለሚያስችሉኝ ከባህል ማዕከላቱ አልጠፋም ። ከውጭ አገር ታዋቂ የሙዚቃ ፤ የስነ ስዕል ፤ የስነ ጽሑፍና የዳንስ ባለሙያዎች በማስመጣት የአገራቸውን ባህል ያስተዋውቁናል ፤ ስለሆነም እጅግ ከፍ ያለ ጥቅም እያበረከቱ ይገኛሉ /15/10/2001 ዓ.ም/።

በጀርመን ባህል ማዕከል ኢትዮጵያውያን የስነ ጽሑፍ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ የጀርመን፥ የአውሮፓና የሌሎችም የአፍሪካ አገሮች ባለሙያዎችን ወይም ደራሲዎችን ይጋበዛሉ። የስነ ጽሑፍ ስራዎቻቸውን ለጥበቡ አፍቃሪያን በማቅረብ የእውቀትና የኪነ ጥበብ እንዲሁም የባህል ሽግግር በማድረግ ላይም ይገኛሉ፤ በማለት የሚያስረዱት ሌላው መረጃ አቀባይ የባህል ማዕከሉን አዘውትረው የሚታደሙት ና በግጥም ስራዎቻቸውም የሚሳተፉት ሰዓሊ፤ቀራጺና ገጣሚ በቀለ መኮንን ናቸው ።

የባህል ማዕከላቱ ለስዕልና ለሙዚቃ የሚሰጡትን ያህል ለስነጽሑፍ መድረኩን አልፈጠሩም። እንዲያውም በአመዛኙ የውጪ ዜጎች በመሆናቸው ታዳሚዎቻቸው

ለእይታ ጥበባት እንጂ ለስነ ጽሑፍ ትኩረት አይሰጡም ለሚለው አስተያየት ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ የሚከተለውን ይናገራሉ።

> አዎ ! የስዕሉን ያህልና የሙዚቃውን ያህል ለስነ ጽሑፉ ትኩረት አይሰጡም። ለምን ይመስልሃል። ሥዕሉን አሳድገውታል። ጥሩ ሽያጭም ዋጋም አለው። ወደ ስነ ጽሑፉ ስትመጣ የቋንቋ ጉዳይ አንድ ነገር ሆኖ፤ የቃላት ጉዳይ ነው። በቀላሉ ትርጉሙ፤ መልዕክቱ ይገባሃል። ስለዚህም ጥንቃቄ ካልተደረገና በተከታታይ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን መልዕክቶች በመድረኮቹ ቢቀርቡ ለኢምባሲዎች የሚመች አይሆንም። ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱን ይጎዳል። ስለዚህም ብዙም ትኩረት አያደርጉበትም (20/10/03 ዓ.ም.)።

በአጠቃላይ የባህል ማዕከሉ ለስነ ጽሑፍ ኪነ ጥበባዊ እድገት የተለያዩ መድረኮችን ከማዘጋጀት አንስቶ÷ለአቅራቢዎቹ የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመስጠትና የጥበቡ አድናቂዎች በጥበቡ ዙሪያ እንዲታደሙ በመጋበዝ ዙሪያ መለስ ሚና ያለው ተግባር እየተጫወተ መሆኑንና ኢትዮጵውያንም በአግባቡ ሙያቸውን መጠቀም እስከቻሉ ድረስ መድረኮቹ ለጥበቡ ማደግ በራቸው ክፍት እንደሆነ መናገር ይቻላል።

## 4.2.3. ሙዚቃ

የጀርመን ባህል ማዕከል ከሚያቀርባቸው የኪነ ጥበብ ሥራዎች መካከል ሙዚቃ አንዱ ነው። ባህል ማዕከሉ ለሙዚቃ እድገት የነበረው አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አይደለም ። ፈረንሳዊው የኢትዮጵያን ሙዚቃ አጥኚና ተመራማሪ ሚስተር ፍራንሲስ ፋልሲቶ ስለ ኢትዮጵያ ሙዚቃ ምንነትና እድገት ሲናገር፤

> የኢትዮጵያ ሙዚቃ ኢትዮጵያ እንደአገር ያደረገችው ጉዞ ነጸብራቅ ነው ። የምዕራባውያንም ሆነ የሌሎች ተጽዕኖ ሙሉ በሙሉ ያረፈበት አይደለም ። ይህ ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ህዝቦች ጋር በቀላሉ ለመቀላቀል ካለመቻላቸው

ጋር የመጣ እንደሆነ ባለሙያዎች ሃሳብ ይሰጣሉ ። ኢትዮጵያ በራሷ ደሴት ውስጥ በመኖሯ የኢትዮጵያ ሙዚቃ የተለዬ ቃና እንዲኖረው አስችሏል ይላል /27/3/2002 ዓ.ም/።

የአገሪቱ የሙዚቃ ገጽታ እንዲህ ከሆነ የኢትዮጵያ ሙዚቃ በተለያዩ መድረኮች እንዲተዋወቅና ለሙዚቃው እድገት እገዛ ለማድረግ ባህል ማዕከሉ መንቀሳቀሱን የባህል ማዕከሉ የፕሮግራም ዳይሬክተር ወይዘሮ ተናኜ ይናገራሉ።

በጎተ ባህል ማዕከል እንደሌሎች የኪነ ጥበብ ስራዎች ሁሉ በሙዚቃ ላይ በስፋት እንቀሳቀሳለን። የተለያዩ የሙዚቃ መድረኮችን በመፍጠር ሙዚቃዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል ። በሙዚቃው ዜማ ፥ በግጥሙ ላይ ፥ በይዘቱና ባነሳው ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ፥ በሙዚቃው ቅንብርና በመሳሰሉት ገጽታዎች የአካዳሚክ ባለሙያዎች ከያሬድ ትምህርት ቤት በማስመጣት ውይይቶች እንዲካሄድባቸው ይደረጋል ። የጀርመን ባህል ማዕከል አንዱና ዋነኛ መለያው የሙዚቃ ጥበብ አፍቃሪዎች ሙዚቃውን አድምጠውና ተዝናንተው እንዲሄዱ ብቻ ሳይሆን በውይይቶች ተሳትፈውና የተሰማቸውን ስሜት ተንፍሰው እውቀት ገብይተው እንዲሄዱ ማድረግ ነው (23/9/2001 ዓ.ም ) ።

በተደጋጋሚ በጀርመን ባህል ማዕከል የሙዚቃ ስራዎቻቸውን ካቀረቡት የኪነ ጥበቡ ባለሙያዎች መካከል አርቲስት ግርማ ይፍራሸዋ ይጠቀሳል ። አርቲስት ግርማ በባህል ማዕከሉ የሙዚቃ ዝግጅቶች ዙሪያ እንደሚገልጸው ፤

በኢትዮጵያ የባህል ሙዚቃ መሳሪያ ምንነት ጥበባዊ ፋይዳና አጠቃቀም ለማሳደግ ሙያተኞችን በማበረታታትና ስራዎቻቸውን ለህዝብ የሚያቀርቡበት ዕድል በማመቻቸት ማዕከሉ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል (የአሊያንስ 100 ኛ

ዓመት መጽሄት ላይ ስለጀርመንና ፈረንሳይ ባህል ማዕከላት የተናገረው 45፤2007) ፡፡

እንደ ግርማ አይነት የሙዚቃ ሰዎች በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ አገር ሳይቀር መድረክ በማመቻቸት የኢትዮጵያን ሙዚቃ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት እንዲያገኝ የተለያዩ ድጋፎችን አድርጓል ፡ ወደ ውጭ አገር ሙሉ ወጪያቸውን በመቻል የኢትዮጵያን ባህልና የኪነ ጥበብ ስራዎችን ÷ሙዚቃውን ከነአለባበሱና ውዝዋዜው በተለይም ለአውሮፓ ህዝብ እንዲያሳዩ የእድገት በሩንም የከፈቱላቸው በርካታ ወጣት ሙዚቀኞች አሉ።

> ፈረንሳይ ሀገርም ሄጂ በሻርትርና ለሴ ከተሞች ለመጫወት የበቃሁት አልያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ እና የጀርመን ባህል ማዕከል ባደረጉልኝ ድጋፍ ነው። በዚህ ዝግጅት ላይ አብረውኝ የሰሩት ድምጻዊ ሚካኤል በላይነህ፤ ፈረንሳዊው ቫዮሊን ተጫዋች ፓትሪስ ለግራን እና ጀርመናዊው ቼሎ ተጫዋች ማርክስ ሌንዝ ነበሩ። በዚህ አጋጣሚም የተመሰረተው አራትዮሽ የሙዚቃ ባንድ በፈረንሳይ፤በጀርመንና በኢትዮጵያ ዝግጅቱን አቅርቧል (ግርማ ይፍራሸዋ (የአሊያንስ 100ኛ ዓመት መጽሄት ላይ ስለጀርመንና ፈረንሳይ ባህል ማዕከላት የተናገረው 45፤2007) ፡፡

የባህል ማዕከሉ፤ የሃገራችንን ሙዚቃዎች በተለያዩ መድረኮች ላይ በማቅረብ ብቻ የተጀመረው የኢትዮጵያ ሙዚቃ ፌስቲቫልን ለማስፋፋት ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ሰፊ አስተዋጽኦ አድርገው የውለታቸውን ያህል ሰፊ ክብርና ዕውቅና ላልተሰጣቸው ቅድሚያ በመስጠት ከዓመት ዓመት አንጋፋዎችን የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን በመዘከርና በማስታወስ በዘንድሮው ዓመት ለአስረኛ ጊዜ በተለያዩ ዝግጅቶች ለማክበር ችሏል ፡፡ በዘንድሮው ዓመት የተካሄደው የሙዚቃ ፌስቲቫል ሲቃኝ፤ በጎተ ኢንስቲትዩት አውደ ጥናት በማዘጋጀት መታሰቢያነቱን ለታዋቂው አርቲስትና ኮሜዲያን ጌታቸው ደባልቄ እና ለትራምፔቱ ንጉስ መርዓዊ ስጦት በማድረግ ትልቅ የሙዚቃ ፌስቲቫል አካሂዷል ፡፡ እ.ኤ.አ. በ20/9/10 ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ የሸክላ

ሙዚቃን ያስቀረጹበትን 100ኛ ዓመት አስመልክቶ በጎተ ኢንስቲትዩት ሙዚቃቸውን በማዳመጥና ውይይት በማድረግ ለአርቲስቱ ልዩ የመታሰቢያ ዝግጅት ለማቅረብ ተችሏል ( ሮዝ መጽሄት ቅጽ 4 ቁጥር 60 መጋቢት 2002 ገጽ 18-20) ፡፡

የባህል ማዕከሉ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ፌስቲቫል ዝግጅት ላይ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ የአገራችንን ሙዚቃ የሚጫወቱ የውጭ አገር ሙዚቀኞች እንዲመጡና ሙዚቃውን በመጫወት የሙዚቃችንን ዓለም አቀፋዊነትና ተቀባይነት መመልከት የሚቻልበትን መድረኮች በተደጋጋሚ ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል ፡፡ ለአብነት ያህል ETH/ኢት/ የሚባል የሙዚቃ ባንድን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ስማቸው እንደሚያመለክተው በስፋት የሚታወቁት የኢትዮጵያን ሙዚቃ በጃዝ ስልት በመጫወት ነው ፡፡ ‹‹ukan Daz ››/ዩካን ዳዝ/ የተባሉ ከፈረንሳይ የመጡ የሙዚቃ ባንዶች ሲሆኑ፣ የኢትዮጵያን ሙዚቃ ከመጫወት በተጨማሪ ታዋቂውን የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች ተጫዎችና ድምጻዊ አስናቀ ገብረ የስን በአባልነት በማከል ልዩ ጣዕም ያለውን የኢትዮጵያ ሙዚቃ በዘመናዊ መልኩ አቅርበዋል (ፍራንሲስ ፋልሲቶ 13/12/2001/)፡፡

በኢትዮጵያ ሙዚቃ በመማረክ የአገራችንን ዘፈን በመጫወት ዓለም ዓቀፋዊ ተቀባይነቱ እንዲያድግ የበኩላቸውን ሚና የሚጫወቱ በርካታ ባንዶችን መጥቀስ ይቻላል ፡፡እንዲያውም አንዳንድ ኦርኬስትራዎች ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያን ሙዚቃ ብቻ የሚጫወቱ ሆነዋል ፡፡ በአሜሪካ÷ በካናዳ÷ በእንግሊዝ ÷ በሆላንድ ÷በፈረንሳይ÷ በእስራኤል ÷ በጃፓንና አውስትራሊያ ሳይቀር የአገራችንን ሙዚቃ የሚጫወቱ ማግኘት ተችሏል (ፍራንሲስ ፋልሲቶ 13/12/2001/)፡፡

ሚስተር ፋልሲቶ እንደገለጸው ማዕከሉ የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለውጪው ዓለም በማስተዋወቅና ተወዳጅ እንዲሆን በማድረግ እንዲሁም ከውጭ አገር የሙዚቃ ሰዎችን በማምጣት የአገራቸውን ሙዚቃና የባህል ሽግግር እንዲፈጠርና ዘመናዊ ሙዚቃ እንዲሰርጽ አድርጓል ፡፡ ወ/ሮ ትናኜ ታደሰ ይህንኑ ሃሳብ እንደሚከተለው ገልጸዋለች፣

> በተለያዩ ጊዜያት የጀርመን ብቻ ሳይሆን የአውሮፓና የአፍሪካ የሙዚቃ ቡድን አባላት ወደ ሃገራችን መጥተው ስራቸውን አቅርበዋል ፡፡ የኢትዮጵያና ጀርመን 100ኛ ዓመት የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ሲከበር እንኳን 60

አባላት የያዙ ሙዚቀኞች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የባህል አዳራሽ የሙዚቃ ስራቸውን ለታዳሚው አቅርበዋል (ወ/ሮ ተናኜ ታደሰ /23/9/2001 ዓ.ም/ ፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ፌስቲቫል ዋነኛ ዓላማውን በተመለከተ የባህል ማዕከሉ የፕሮግራም ዳይሮክተር ወ/ሮ ተናኜ ታደሰ እንደሚገልጹት፤የኢትዮጵያን ሙዚቃ ትዕይንት ማሳደግ÷ ለኢትዮጵያን ሙዚቀኞች ጉልበት መስጠት ÷ የገንዘብም ሆነ የቴክኒክ ችግሮች ያጋጠማቸውን ጀማሪዎች ማበረታት መሆኑን ያስረዳሉ ፡፡

የባህል ማዕከሉ ለአገራችን የሙዚቃ ጥበብ እድገት በተለያዩ ጊዜያት በሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ድጋፎችና ለጥበቡ እውቅና በመስጠት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለማስተዋወቅ ከፍ ያለ እገዛ አድርጓል ፡፡

በዚህ ሃሳብ ላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የያሬድ መዚቃ ት/ቤት ዳይሬክተር የሆነው እዝራ አባተ የተለዬ አመለካከት አለው፡፡

> የጀርመን ባህል ማዕከል ሙዚቃን አካዳሚያዊ በሆነ መልኩ የተለያዩ ዲስኮርሶች እንዲቀርቡ በማድረግ ሙዚቃና ልማት፤ መዚቃና ባህል፤ ሙዚቃና ማህበረሰብ የመሳሰሉ ዝግጅቶች በማቅረብ ምርምራዊ ስራዎችን በማቅረብ በኩል ጥሩ መድረኮች ፈጥረዋል፡፡ በሌላ በኩል ለኢትዮጵያ ሙዚቃ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቅ አድርገዋል የሚለውን አልቀበለውም፡፡ ሙዚቃው በራሱ እየተሰማ፤እነመሐሙድ አህመድ በራሳቸው የወጡ እንጂ፤ሚስተር ፍራንሲስ ወይም ባህል ማዕከላቱ አይደለም እንዲታወቁ ያደረጉት፡፡ እርግጥ ፍራንሲስ ፕሮሞተር ስለሆነ እየተደመጠ ያለውን ሙዚቃ የበለጠ ሊያስተዋውቀው ይችላል(እዝራ አባተ ፤16/10/03 ዓ.ም.) ፡፡

ባህል ማዕከሉ ካቀረባቸው የሙዚቃ ዝግጅቶች ማካከል የተወሰኑትና ለመጥቀስ ያህል እ.ኤ.አ በ28/3/06 ሃይሉና ጓደኞቹ ባንድ ፤ ሚካኤል ላወር በ9/3/06 ክላሲክ

ጊታር ፤በ14/9/07 ኩንቴንት ቻንትሊ ከጀርመን የመጣ ባንድ በአዲስ አበባ ባህል አዳራሽ፤በ29/11/2010 አካሌ ውቤ ከፈረንሳይ የመጣ ባንድ ዝግጅታቸውን ካቀረቡት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው ( ሙሉ ዝርዝሩን መግለጫዊ መዘርዝር ላይ ይገኛል ) ፡፡

በአገሪቱ ታሪክ ለሙዚቃ ስራ ብዙ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ኢትዮጵያውያን የመታሰቢያ ዝግጅቶችን በማካሄድ በሙዚቃ ስራቸው ላይ ምርምር ና ውይይት በማድረግ ረገድ የተለዬ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ፡፡ ዋናው የባህል ማዕከላቱ ዓላማ የራሳቸውን ሙዚቃና ባህል ማስተዋወቅ ቢሆንም በሙዚቃ መድረኮች ላይ በአግባቡ መጠቀማቸውንና ከውጪ አገር የሚመጡ የሙዚቃ ባለሙያዎች ስልጠናዎችን በባህል ማዕከላት ካደረጉ በኂላ በያሬድ የሙዚቃ ት/ቤት ስልጠናውን እንዲሰጡ ስለሚደረግ መጠቀማቸውን አቶ እዝራ አባተ ይናገራሉ ፡፡ በሌላ በኩል የጀርመን ባህል ማዕከል ለስዕሉንና ለስነ ጽሁፉን የሰጠውን ትኩረት ያህል ለሙዚቃው ሰፊ መድረክ አለመስጠቱን የዚህ ጥናት አቅራቢ ለሚያቀርበው ሙግት ደራሲ ዳንኤል ወርቁ ይስማሙበታል፡፡ የጀርመን ባህል ማዕከል ለሚያዘጋጃቸው የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች የስፖንሰር ችግርን ባይጠቅስም ጀርመን በቀል የሆኑ እንደሉፍታንዛ አየር መንገድ አይነቶች በአጋርነት እንደሚሰሩ ከጥሪ ወረቀቱ ላይ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

# 5. የጣሊያን ባህል ማዕከል ታሪክና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ

በኢትዮጵያ ኢምባሲያቸውን በቀዳሚነት ከከፈቱ አውሮፓዊ አገሮች አንዷ ጣሊያን ናት::ኢምባሲ በመክፈት የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ከጀመረች ከ1889 ዓ.ም አንስቶ 114 ዓመት እድሜ አስቆጥራለች :: የጣሊያንና ኢትዮጵያ ግንኙነት በአጼ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት ጊዜ የጀመረ ቢሆንም ከቅኝ ግዛት ፍላጎትና ካልገዛም ባይነት ጋር በተያያዘ መልካም ግንኙነት ነበራቸው ባይባልም ከ1940ዎቹ መጀመሪያ በኋላ መልካም ግንኙነትን በመፍጠር በተለያዩ ማህበራዊና የባህል እንዲሁም የልማት ስራዎችን ለመስራት ተችሏል :: በዚህ ሂደት ውስጥ የኢጣሊያ የባህል ማዕከል እ.ኤ.አ. በ1960 ዓ.ም.ተቋቋሟል::

## 5.1. የጣሊያን ባህል ማዕከል ታሪክ

ባህል ማዕከሉ የአምሳ አንድ አመት እድሜን አስቆጥሯል :: የባህል ማዕከሉ መቋቋም ዋነኛ ዓላማ ምን እንደሆነ የጣሊያን ኢምባሲ የባህል አታሼና የባህል ማዕከሉ ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ብሩኖ ቢሊቶ ጥያቄ አቅርቤላቸው ሲመልሱ፤

> የኢጣሊያንና ኢትዮጵያ ግንኙነት ታሪካዊና ረጅም እድሜ ያስቆጠረ ነው :: የባህል ማዕከሉ የጣሊያንን ባህልና ቋንቋ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅና የሁለትዮሽ የባህል ግንኙነትና ልውውጥ ለማድረግ የተቋቋመ ነው :: በጣሊያን ባህል ማዕከል ልዩ ልዩ የባህል መድረኮችና ዝግጅቶችን ከጣሊያን አገር በማስመጣት የማስተዋወቅና የኢትዮጵያን ባህልና የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴዎች በስፋት የማስተዋወቅ ዓላማም አለው(ፕሮፌሰር ቡሩኖ ቤሊቶ/7/8/2001ዓ.ም)::

የጣሊያን ባህል ማዕከል እ.ኤ.አ አቆጣጠር በ1960 ዓ.ም ኢምባሲው በሚገኝበት አካባቢ የተቋቋመ ሲሆን፤ ከ14 ዓመታት በኋላ አሁን ወደሚገኝበት በላይ ዘለቀ መንገድ ሰሜን ሆቴል አካባቢ ኢምባሲው ባሰራው ህንጻ እ.ኤ.አ በ1974 ሊዛወር ችሏል :: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የባህል ማዕከሉ የባህል÷የኪነ ጥበብና የቋንቋ ትምህርት ቤቱን በተጠናከረ መልኩ እያካሄደ ይገኛል :: በመላው ዓለም በ90 ሃገሮች እንደሚገኙት የባህል ማዕከላት ሁሉ ከኢጣሊያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር በመሆን የጣሊያንን

ቋንቋና ባህል በመላው ዓለም እንዲስፋፋ በመስራት ላይ ይገኛል ( የባህል ማዕከሉ ዌብ ሳይት ስለ ባህል ማዕከሉ በሚገልጸው ላይ)።

## 5.2. የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ በጣሊያን ባህል ማዕከል

የጣሊያን ባህል ማዕከል የጣሊያንና የኢትዮጵያን አገሮች ባህል ልዩ ልዩ የኪነ ጥበብ ስራዎችን መድረክ በማዘጋጀት ለአድማጭና ተመልካቹ አማራጭ የኪነ ጥበባት እንቅስቃሴ ማሳደጊያ ማዕከል ሆኖ ቆይቷል ። በተለይም በሙዚቃው ዘርፍ ኢትዮጵያውን እምብዛም ባልለመዱትና በማያዘወትሩት የሙዚቃ ስልቶች ታላላቅ የክላሲክ ና ጃዝ እንዲሁም የኦፔራ የሙዚቃ አይነቶችን በማቅረብ አድማጮችን አዝናንተዋል።የባህል ልውውጥም አድርገዋል ። የዳንስ ዝግጅቶችን በማድረግ ከውጪ አገር እንደ ባሊ ዓይነቶችን አስተዋውቀዋል ።

የጣሊያን ባህል ማዕከል የአገራችንንም የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች የሙዚቃ ጭፈራና እስክስታ በማቅረብ የባህል ትውውቁን በማሳደግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። የጣሊያንና ኢትዮጵያውያን ሰዓሊዎች ኤግዚቪሽን ስራዎችን ያቀርባል ። ሳይንሳዊና ሰብዓዊ ጉዳዮች ላይ አውደ ጥናቶችንና ውይይቶችን በማዘጋጀት ሰፊ የሆነ የባህል ÷ የኪነ ጥበብና የእውቀት ሽግግር በማድረግ ይታወቃል ። የጣሊያን ባህል ማዕከል እንቅስቃሴ እንደ ፈረንሳይና ጀርመን የጎላ አይደለም። እንዲያውም በአንጻራዊነት ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑን፤ከቅርብ ዓመታት ወዲህም እየተቀዛቀዘ መምጣቱን የጥበብ ስራዎችን የሚከታተሉና የሚያቀርቡ ባለሙያዎች የሚጋሩት ሃሳብ ነው ( ደራሲ ዳንኤል ወርቁ ፤ ሰዓሊና ቀራጺ በቀለ መኮንን እና ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኤሬቦ ) ። ባህል ማዕከሉ በግሉ ከሚያሰናዳቸው የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች በተጨማሪ ከአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ እና ከጀርመን የባህል ማዕከል ጋር በጋራ የሚያዘጋጁቸው መርሃ ግብሮች አሉ ( ወ/ሮ ተናኜ ታደሰ 23/9/2001 ዓ.ም. )። የዚህ ጥናት ትኩረት በሆኑት የኪነ ጥበብ ዘውጎች ላይ ያሉትን ክንውኖች አንድ በአንድ እንመልከት።

## 5.2.1. ስነ ስዕል

የአንድ ሃገር የእድገት ደረጃ የሚገመገመው በውስጡ በሚገኙት የሕብረተሰብ ባህላዊና ጥንታዊ የስራ ውጤቶች መሆኑ ግልጽ ነው ። ከእነዚህም መለኪያዎች አንዱ ስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ነው ። የስነ ስዕል ሙያ ለአንድ ህብረተሰብ ታሪክና እድገት የሚያደርገው አስተዋጽኦ በቀላል የሚገመት አይደለም። ስነ ስዕል በብዙ አገሮች ውስጥ ከውበታዊ እሴት አልፎ ተግባራዊ በሆነና ብልጽግናን በሚያበረክት ደረጃ በየኢንዱስትሪው አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ነው ።

ወደ አገራችና ሰዓሊያንና የስዕል ስራዎች ስንሸጋገር የኢትዮጵያ ሰዓሊያን በሁለት መሰረታዊ ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ ። ከፊሎቹ በዘልማድ ሙያውን የተካኑ ሲሆኑ ፤ከፊሎቹ ደግሞ በዘመናዊ የስነ ጥበብ ትምህርት ቤቶች ሙያውን ያጠናቀቁ ናቸው። የዘመናዊ ሥዕል ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ የተከፈተው በ1950 ዓ. ም. ነው። ሆኖም ቀደም ሲል ስለሙያው መስፋፋት መሰረቱን ከጣሉት ውስጥ አገኘሁ እንግዳ ፥ አበበ ወልደ ጊዮርጊስ ና አለፈለገ ሰላም ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ እንደነበር ታሪክ ያስታውሳቸዋል( ታዬ ታደሰ ፤ገጽ 3 ) ።

እንግዲህ ከዘመናዊ ትምህርት ቤት የሚመረቁ ሰዓሊያን የፈጠራ ስራዎቻቸውን የሚያቀርቡበት መድረክ ባለመኖሩ ሲቸገሩ የቆዩ ሲሆን ፤የመጀመሪያውን የስዕል ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት ለሰዓሊያን ከጥበብ አድናቂዎቻቸው ጋር እንዲገናኙ ጥርጊያውን በመክፈት ማለትም በ1956 ዓ.ም. የጣሊያን ባህል ማዕከል ቀዳሚ በመሆን ባለውለታ መሆኑን በስዕል ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

> የጣሊያን ባህል ማዕከል የሙዚቃውን ያህል ባይሆንም የስዕል ስራዎች የሚቀርቡበት መድረክ ነው። ላለፉት ዓመታት የበርካታ ሰዓሊያን ስራዎችን አቅርበዋል። ይሄንን መድረክ ማዘጋጀታቸው ለሰዓሊያን አማራጭ የኤግዚቢሽን ማሳያ ቦታ ሆኖ ቆይቷል (በቀለ መኮንን 9/10/03) ።

ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኤሪቦም የአቶ በቀለን ሃሳብ ይጋራል‹‹እኔ በተከታተልኳቸው መድረኮች፤ዮሐንስ ገዳሙ አውታር ዳይሜንሽን ክበብ የሚባል በስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ላይ ባለሙያዎች ለረጅም ዓመታት ምናልባትም ከ1991 እስከ

1997 ዓ.ም አካባቢ ሞቅ ያለ ውይይት ይካሄድ እንደነበረ አስታውሳለሁ››(ፋንታሁን ኬሪቦ 14/10/03)፡፡

ከአገራችን ስመ ጥር የስዕል ባለሙያዎች አንስቶ ጀማሪ ሰዓሊያን በጣሊያን የባህል ማዕከል መድረኮችን በማመቻቸት አድናቂዎቻቸውንና የኪነ ጥበብ አፍቃሪያንን በማገናኘት ማዕከሉ ድልድይ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል ፡፡ እንዲያውም የጣሊያን ባህል ማዕከል ከኪነ ጥበብ ዘርፎች ሁሉ ለስዕል ልዩ ፍቅር እንዳለው ይነገራል ፡፡

> የባህል ማዕከላችንን ከሌሎች አገሮች የባህል ማዕከላት ለዩት የሚያደርገው ለሥነ ስዕል ኪነ ጥበብ ከፍ ያለ ቦታ በመስጠቱ ነው ፡፡ በየጊዜው የሥዕል ኤግዚቢሽን በማዕከላችን ማካሄድ የተለመደ ነው ፡፡ለበርካታዎቹ አሁን ለደረሱበት ዝና የማዕከላችን አስተዋጽኦ የላቀ ነው ፡፡ ከጀማሪዎች እስከ አንጋፋ ሰዓሊዎች በእኛ ማዕከል በኩል ያለፉ ናቸው( ፕሮፌሰር ብሩኖ ቢሊቶ /7/8/2001ዓ.ም)፡፡

በጣሊያን ባህል ማዕከል የስዕል ሥራቸውን ካቀረቡት ባለሙያዎች መካከል ሰዓሊ መዘምር ልሳነ ወርቅ ÷ መዝገቡ ተሰማ ÷ጌታ መኮንን÷ ጌታቸው ዮሴፍ ÷ ታደሰ መስፍን ÷በቀለ መኮንን ÷ዘሪሁን የትምጌታ ÷ ዳንኤል ታየ ÷ሰዓሊና ዲዛይነር ሰይፉ አበበ ይጠቀሳሉ ( ሙሉ ዝርዝሩን ከመግለጫዊ መዘርዝሩ ይገኛል )፡፡ የቀዳሚዎቹ ሶስቱ ሰዓሊያን የሃሳብና የአሳሳል ሥልቶች የተለያዩና የራሳቸውን ኢትዮጵያዊ አሻራ ይዘው ዓለም ዓቀፋዊ ዝናን ያገኙ ናቸው፡፡ ሰዓሊ መዘምር ስለባህል ማዕከሉና ሥለ ራሱ የኪነ ጥበብ ስራ ገልጾልኛል ፡፡

> ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ. ም / በቅርቡ ማለት ነው/ በባህል ማዕከሉ « የጥንታዊ ጥበብ አሻራ »በሚል ስራ አቅርቤ ነበር ፡፡ስዕሎቼ በቅዱሳን መጽሀፍት ታሪኮች ላይ በመመስረት በእንጨት ላይ የተቀረጹ ስዕሎች ናቸው፡፡ኢትዮጵያዊ ተረኮችን ከሃይማኖት ጋር አዛምጄ ነው ያቀረብኩት ፡፡ ለበርካታዎቹ ልዩ ፍቅርን እንደፈጠሩ አስታውሳለሁ፡፡ ዋናው ቁም ነገር ከአድናቂዎችህ ጋር እንድትገናኝ መድረኩን በማመቻቸት በኩል የባህል

ማዕከሉ ትልቁን ድጋፍ ማድረጉ መጠቀስ አለበት (የጥሪ ካርዱ ላይ ስለ ሰዓሊው ከተገለጸው የተወሰደ)፡፡

አርቲስት መዘምር ከአርሶ አደር ቤተሰብ የተወለደና እድገቱም በሰሜን ሸዋ አካባቢ ነው፡፡አስተዳደጉ በፈጠረው ተጽዕኖ ምክንያት በስዕል ስራዎቹ ሁሉ የሚታየው የገጠሩን ማህበረሰብ ህይወትና የዕለት ከዕለት ኑሮ የሚያንጸባርቅ ሆኖ እናገኘዋለን ፡፡ ሰማዩ የአህያ ሆድ ሲመስል የገጠሩ ምስል ፥ ገበሬ ወደ እርሻ ሲያመራ ፥የውቂያ ጊዜ ያለውን ክንውን፥ አመሻሽ ላይ ከብቶች ወደ ማደሪያቸው ሲሄዱ የሚታየውን ትዕይንት የመሳሰሉትንና ሃይማኖታዊ ባህላዊ ትስስር ያላቸውን ስዕሎችን አርቲስቱ በባህል ማዕከሉ በተደጋጋሚ በማቅረብ ይታወቃል (ስለ ሰዓሊው የባህል ማዕከሉ ባስተዋወቀው የመጥሪያ ወረቀት ላይ ከተጻፈው የተወሰደ ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም)፡፡

አርቲስት ሰይፉ አበበም በተመሳሳይ የጣሊያንን ባህል ማዕከል መድረክ በመጠቀም አሁን ለደረሰበት ዝናና ክብር የበቃው በባህል ማዕከሉ መሆኑን በኩራት ይናገራል ፡፡ የግራፊክስ አርት ዲዛይነር የሆነው አርቲስት ሰይፉ ከኢትዮጵያ ውጪ በጣሊያን ፥ጀርመን፥ ፈረንሳይ ፥ እንግሊዝ ፥ ራሺያ ፥ አሜሪካ፥ ካናዳ ና የአፍሪካ አገሮች ለበርካታ ጊዜ የስዕል ኤግዚቢሽን በማቅረብ ከፍ ያለ እውቅና አግኝቷል፡፡

የባህል ማዕከሉ የጥበብ አፍቃሪያን የመገናኛ መድረክ ለወጣት ሰዓሊያን የጥበብ እጃቸውን የሚያፍታቱበት ማዕከል መሆኑን ያስረዳል ፡፡

> እኔ ከ16 ዓመት በፊት ከአርት ስኩል እንደወጣሁ የመጀመሪያ ኤግዚቢሽኔን ያቀረብኩት በጣሊያን ባህል ማዕከል ነው ፡፡ በወቅቱ ታዋቂና አንጋፋ አርቲስቶች በመገኘታቸው በአንድ ጊዜ ሁለት ስሜቶችን ነበር ያስተናገድኩት ፡፡ የመጀመሪያው ስራዬን የሚያናንቁብኝ መስሎኝ ፍርሃት ተሰማኝ ፡፡ በሌላ በኩል ግን የእኔን የጀማሪውን ስራ ለማዬት በመምጣታቸው ኩራት ኩራት አለኝ ፡፡ አየህ ያቺ ! የመጀመሪያ ስራዬን በዚያ መድረክ ማቅረቤ ዛሬ ለደረስኩበትና በአውሮፓና አሜሪካ በዝነኛ የሥዕል ጋለሪዎች እንዳቀርብ አስችሎኛል (አርቲስት ሰይፉ አበበ ፤26/10/2001ዓ.ም)፡፡

በባህል ማዕከላቱ የኪነ ጥበብ ስራዎችን ከሚከታተሉት የጥበብ አድናቂዎች መካከል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ የነበሩት ዶክተር አያሌው ሲሳይ ይጠቀሳሉ ። ዶክተር አያሌው በጣሊያን ባህል ማዕከል ስለሚቀርቡ የስዕል ኤግዚቢሽኖች ምን ገጽታ እንዳላቸው እና በአጠቃላይ ከኪነ ጥበብ ማሳደግ አንጻር የማዕከላቱ አስተዋጽኦን ጠይቀያቸው ነበር። በጣሊያን ባህል ማዕከል በሚቀርቡ ኢትዮጵያዊ አሻራ ባላቸው ስራዎች እንደሚመሰጡና አዳዲስ የፈጠራ ስራዎችን ይዘው የሚቀርቡ አዳዲስ ወጣት የኪነ ጥበብ ባለሙያ እየመጣ መሆኑን ይናገራሉ ። የባህል ማዕከላቱ እያቀረቡት ያለው ልዩ ልዩ የኪነ ጥበብ ስራዎች የአገሪቱን መልካም ስም ከመገንባት አንስቶ ፣ለዜጎች የስራ እድልን የሚፈጥር፣ ባለሙያውን በፈጠራ ስራው ተጠቃሚ የሚያደርግ ፣ ዓለም አቀፋዊ የባህልና ኪነ ጥበብ ሽግግርን የሚፈጥርና ቱሪዝምን ከማስፋፋት አንጻር ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ዶክተር አያሌው አስረድተዋል ። በመሆኑም የባህል ማዕከላቱ ላለፉት 51 ዓመታት ለኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ማደግ ና በአገሮች መካከል መልካም ግንኙነት በመፍጠር የባህል ሚናን ጉልህ ድርሻ ያሳዩ ተግባራት ማከናዎናቸውን ተናግረዋል ።

በባህል ማዕከሉ ኢትዮጵያውያን ሰዓሊዎች ብቻ ሳይሆኑ ፣ ከጣሊያን አገር ስመ ጥር ዝነኛ ሰዓሊዎች የኪነ ጥበብ ስራዎቻቸውን ይዘው በመቅረብ የባህልና የስዕል ጥበብ እውቀት ሽግግርና ልውውጥ አድርገውበታል ።

## 5.2.2. ሥነ ጽሑፍ

በባህል ማዕከሉ ግጥሞች ፥ወጎች ፥አጫጭር ልቦለዶች ፥ ታሪካዊ ፥ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ልዩ ልዩ የሥነ ፅሑፍ ስራዎች ይቀርባሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከጣሊያንኛ ወደ አማርኛ የተመለሱ/የተተረጎሙ/ የፈጠራ ስራዎችን በማሰናዳት የስነ ጽሑፍ አፍቃሪያንን የጥበብ ስራዎች ለታዳሚዎች ያቀርባሉ።

በማዕከሉ የስነ ጽሑፍ ስራዎቻቸውን ካቀረቡት ሙያተኞች መካከል ፍሬዘር አድማሱ ፥ምስራቅ ተረፈ፥ አበባው መላኩ ፥ምህረት ከበደ ፣ጌትነት እንየው፥ ፍቃዱ ተክለማርያም ፥እሸቱ ጥሩነህ ፥በቀለ መኮንን፣ትእግስት ማሞ፣ሐይማኖት ዓለሙ፣ ልዑል ሰገድ ረታና ሌሎችም የገብረ ክርስቶስ ደስታ ማስተዋሻ በሚልና ሃገሬ በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. ግንቦት 14 ቀን 2009 ዓ.ም ስራቸውን አቅርበዋል (ዝርዝሩን

ከመግለጫዊ መዘርዝሩ ይገኛል) ፡፡ እነዚህ የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ስራዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ማዕከሉ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ፡፡ በማዕከሉ ስራዎቻቸውን በማቅረባቸው የተገኘውን ጥቅም ፍቃዱ ተክለ ማርያም እንዲህ ሲል ይገልጸዋል ፡፡

> የጣሊያን ባህል ማዕከል ለስነ ጽሁፍ ማደግ የበኩሉን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በተደጋጋሚ በየአመቱ በሚያወጣቸው መርሃ ግብሮቻቸው ከጀማሪ እስከ አንጋፋ የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች መድረኩን እንዲያገኙ ያመቻቻል ፡፡ በእነዚህ መድረኮች የስነ ጽሑፍ ፍቅር ያለው ታዳሚ በመገኘት የጥበብ ስራዎችን ይኮመኩማል (አርቲስት ፍቃዱ ተ/ማርያም /5/10/2001 ዓ.ም) ፡፡

በጣሊያን ባህል ማዕከል በሚቀርቡ የሥነ ጽሑፍ ምሽት ዝግጅቶች ከአንድ አንድ ወቅታዊ ጉዳይ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ዝግጅቶችም አሉ ፡፡ለምሳሌ ከኢትዮጵያ የድል ቀኖች ፥ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላት/ቀናት/ ወይም ከጣሊያን የድል ና ህዝባዊ በዓላት አልያም አውሮፓውያን ታዋቂ የበዓል ሳምንቶች ጋር ተያይዞ የተለያዩ ዝግጅቶች ይቀርባሉ ፡፡ በእነዚህ መርሃ ግብሮች የሚቀርቡት የስነ ጽሑፍ ዝግጅቶች ወይ በማዕከሉ ጋባዥነት አለበለዚያም ስነ ጽሑፍ በሚያዘጋጁ ማህበራት ተነሳሽነት ነው ፡፡ አልፎ አልፎም የደራሲያንን ስብስብ ጥያቄ እንደሚስተናገድ ፕሮፌሰር ቡሩኖ አስረድተዋል ፡፡

> የስነ ጽሑፉ /ለምሳሌ የግጥሙ /ይዘትን እኛ ላንገመግመው እንችላለን ፡፡ የግምገማ ውጤቱን የምታየው በጥበቡ አፍቃሪያን ዘንድ በሚሰጠው ምላሽ ነው ፡፡ እኛ ለስነ ጽሑፍ እድገት የምናደርገው ድጋፍ አዳራሽና መጠነኛ ኩኪስ እንዲሁም ፖስተር ከማዘጋጀት አንስቶ ጥሪ የማድረግ ተግባራት ብቻ ናቸው ፡፡ በባህል ማዕከሉ በርካታ ወጣትና አንጋፋ ደራሲያን የግጥም አጫጭር ና ረጅም የልብ ወለድ እንዲሁም የትርጉም ስራዎቻቸውን የመጽሃፍ ምረቃ ዝግጅቶች ያካሄዳሉ ፡፡ ማዕከሉ ለጣሊያንኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ማደግና መስፋፋት ጠንክሮ በመስራት ላይ እንደሚገኝና ለዚህም

የሚያገለግል የተሟላ ትምህርት ቤት ከነ ቤተ መጻህፍቱና ቤተሙከራው የተደራጀ መሆኑን ፕሮፌሰር ቡሩኖ ይናገራሉ (ፕሮፌሰር ቡሩኖ/7/8/2001ዓ.ም)::

በአጠቃላይ ሲታይ የጣሊያን ባህል ማዕከል ለሃገራችን የስነጽሁፍ ዕድገት አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። እንደሌሎቹ የባህል ማዕከላት ሁሉ ለአማተር የስነ ጽሑፍ ሙያተኞች ዕደገት ያለው ድርሻም መድረኩን ከመስጠቱ አንስቶ ጥሪዎችን በማስተላለፍ በኩል አበረታች የሚባል ነው።

## 5.2.3 ሙዚቃ

የጣሊያን የባህል ማዕከል ለሙዚቃ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። የአገር ውስጥ ሙዚቀኞች የተለያዩ የፒያኖ ፥የሳክስና የማሲንቆ ሙዚቃዎችን እንዲሁም የህብረ ዝማሬና የባንድ ሙዚቃዎችን በተናጠልና በቡድን እንዲያቀርቡ ያላቸውን ጥበባዊ ክህሎት የሚያሳዩበት መድረክ ያመቻቻል።በዚህ ላይ የማዕከሉ ዳይሬክተር የሚከተለውን ብለዋል።

> በማዕከላችን የተለያዩ ሙያተኞች የራሳቸው የፈጠራ ስራ የሆኑ የፒያኖ፥ የሳክስፎን ሙዚቃ ጨዋታና የማሲንቆ ሙዚቃን ከሌሎች ዘመናዊ የጃዝ ዘፈኖች ጋር በማዋሃድ የሚፈጥሩትን ልዩ የሙዚቃ ጣዕም ለማጣጣም የሚያስችል ዝግጅት ይካሄዳል። የህብረ ዝማሬዎችና መዝሙሮች አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከዳንስ ጋር የተዋሃዱና በተለያዩ ቅኝቶች በሙዚቃ መሳሪያዎች ታጅበው የሚቀርቡበት ዝግጅቶችም አሉን ። በአብዛኛው ግን ከጣሊያን አገር የሚመጡ ዕውቅ የሙዚቃ ባለሙያዎችን በማስመጣት የክላሲካል ሙዚቃ፤የክላሲካልና ጃዝ ሙዚቃዎችን በባህል ማዕከሉ፤በሂልተን አዲስ፤በብሔራዊ ቲያትር እንዲሁም አልፎ አልፎም ቢሆን እስከ ክልሎች ድረስ ሄደው እንዲያሳዩ እናደርጋለን። በያሬድ ሙዚቃ

ትምህርት ቤትም ሙዊ ገለጻና ሌክቸር እንዲሰጡ እናደርጋለን (ፕሮፌሰር ቡሩኖ/7/8/2001ዓ.ም)።

የጣሊያን ባህል ማዕከል ከስዕሉና ስነ ጽሑፉ በላቀ ደረጃ በሙዚቃ ዝግጅቶቹ በርካታ ኢትዮጵያውያንና አውሮፓውያን ተከታታዮች አሉት። ብዙውን ጊዜ የሚያተኩረው የተለያዩ የአዘፋፈን ስልቶችና የመሳሪያ ተጫዋቾች ዙሪያ ነው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር አቶ እዝራ አባተ ስለጣሊያን ባህል ማዕከል የሚገልጸው በሚከተለው መልኩ ነው።

> ያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ከሶስቱም የባህል ማዕከላት ጋር በጋራ ይሰራል። እንዲያውም ከጣሊያን ባህል ማዕከል ጋር በምናደርገው አብሮ የመስራት ሂደት ውስጥ ስልጠና ወይም የሙዚቃ ልምዳቸውን የሚሰጡ ባለሙያዎቹ ከመምጣታቸው በፊት በትምህርት ቤቱ ፕሮግራም እንዲያዝላቸው ያደርጋሉ።እኛም ዝግጅታቸውን ካቀረቡ በኋላ በትምህርት ቤታችን በሚሰጡት ሙያዊ ትንታኔና የራሳቸውን የሙዚቃ ልምድ ለእኛ የሚያካፍሉበት አሰራር ከእነርሱ የዳበረ የሙዚቃ እውቀት እንድንካፈል ይረዳናል (እዝራ አባተ 16/10/03ዓ.ም.)።

በጣሊያን የባህል ማዕከል የሚቀርቡ የሙዚቃ ዝግጅቶችን በተመለከተ፤አቶ እዝራ እንደሚገልጸው በ1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በርካታ የሙዚቃ ኮንሰርቶችን ያቀርቡ ነበር። ከሌሎችም ባህል ማዕከላት በላቀ ደረጃ ጣሊያን ባህል ማዕከል ነበር ወደ ሙዚቃው የሚያደላው። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን አሊያንስም፤ የጀርመኑ ባህል ማዕከልም በሙዚቃው ላይ ነቃ ያለ ተሳትፎ ማድረግ ጀመሩ ይላል። ያም ሆኖ የጣሊያን ባህል ማዕከል ያቀርባቸው የነበረው የሙዚቃ ዝግጅቶች የራሳቸው ሙዚቃ ላይ ብቻ ነበር ትኩረታቸው። እስከ 1980ዎቹ መጨረሻ ድረስ በዚሁ ባሕል ማዕከል የሚቀርበው ዝግጅት ክላሲካል ሙዚቃ ነበር። ከ1990ዎቹ ወዲህ ከክላሲካል በተጨማሪ የጃዝ ሙዚቃን ማቅረብ ጀምረዋል (እዝራ አባተ 16/10/03 ዓ.ም.)።

በቅርቡ የቬትሆቨን የልደት በዓልን ምክንያት በማድረግ እዝራ አባተ እና የያሬድ ትምህርት ቤት የክር ሙዚቃ ተጨዋቾች እ.ኤ.አ.ህዳር 15,2010 ዝግጅታቸውን ያቀረቡ ሲሆን፤የያሬድ ሙዚቃ ተማሪዎች ህዳር 22,2010፤ጣሊያናዊው ካርሎ ሚቼን ህዳር 23,2010፤ፈረንሳዊው ክርስቲን ቻሪሮን ህዳር 29,2010፤ ጀርመናዊው ኢጎር ሌቪት ጥቅምት 4,2010 ፤ግርማ ይፍራሸዋ ጥቅምት 11,2010 ፤ የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ተማሪዎች ጥቅምት 18,2010 ፤ የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ተማሪዎች ታህሳስ 6,2010፤የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ተማሪዎች ታህሳስ 13,2010 ዝግጅታቸውን በተለያዩ ቦታዎች አቅርበዋል ( ሙሉ ዝርዝሩን መግለጫዊ መዘርዝሩ ላይ ይገኛል)።

የሙዚቃ አቀናባሪው ዮሃንስ በላይ የጣሊያን ባህል ማዕከል በሚያዘጋጀው የሙዚቃ ዝግጅት ቀርቶ አያውቅም ።ስለዝግጅቶቹ ሲገልጽልኝ ፤

> የመኖሪያ ሰፈሬ ለባህል ማዕከሉ ቅርብ በመሆኑ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶችን ከልጅነት አንስቶ ስከታተል ነው ያደግሁት። ከምመለከታቸው የሙዚቃ ኮንሰርቶችና ቅንብሮች ሁሉ ይስበኝ የነበረው ወንድና ሴቶች እየተቀባበሉ በህብረ ዝማሬ የሚጫወቱት እንደገና ደግሞ ከጣሊያን አገር የሚያስመጧቸው የክላሲካል ፤ የኦፔራ ዘፋኞች እና ቫሊ ዳንሱ ይማርከኝ ነበር/17/8/2001 ዓ.ም/።

የገብረ ክርስቶስ ደስታን ሙት ዓመት ለመዘከር እ.ኤ.አ ግንቦት 14,2009 በተካሄደ ዝግጅት ግርማ ይፍራ ሸዋ፤ ሳክስፎኒስት አክሊሉ ዘውዴ፤ዋሽንት ተጨዋቹ ዮሐንስ አፈውርቅ፤ ከበሮ ተጨዋቹ አምሃየሱስ አሰፋ፤ የድምጽ ኢንጂነሩ ኒቱሽ ይልማ፤ ድምጻዊ ሩት ዱንካን የተጫወቱ ሲሆን፤በዘመናዊ ዳንስ ዳንኤል ደምሴና መክቡል ጀማል ዝግጅታቸውን አቅርበዋል( ዝርዝሩን መግለጫዊ መዘርዝሩ ላይ ይገኛል)።

የባህል ማዕከሉ የኢትዮጵያውያንን ሙዚቃ በተወሰነ ደረጃ ቢያቀርብም በዋናነት ግን የጣሊያንን ሙዚቀኞች÷ድምጻውያንን በማስመጣት እንዲሁም የዳንስና የተውኔት ባለሙያዎችን በመጋበዝ ከአለባበሳቸው ጋር ባህላቸውን ያስተዋውቃሉ። በተለይም ጣሊያኖች በሚታወቁበት የኦፔራ ዘፈኖች በተደጋጋሚ ታዋቂ ዘፋኞችን የባህል ማዕከሉ

በማስመጣት በማዕከሉ፥ በሂልተን አዲስ እና በሌሎችም ኮንሰርቶችን ለማሳዬት በሚያስችል መድረኮች ያቀርባሉ ። ይህንኑ ሃሳብ የሚጋራው ሌላው መረጃ ሰጪዬ ጋዜጠኛ ፋንታሁን ኤሪቦ ነው። አቶ በቀለ መኮንንና ደራሲ ዳንኤል ወርቁም በጣሊያን ባህል ማዕከል የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴዎች እየቀዘቀዙ የመጡ መሆኑንና የሙዚቃ ስራ ብቻ ያውም በአመዛኙ የጣሊያንን ሙዚቃ ብቻ የሚያቀርቡ ሲሆን ከአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ጋርና ከጀርመን ባህል ማዕከል ጋር በትብብር የሚቀርቡ ዝግጅቶች ብቻ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

## 6. የሶስቱ ባህል ማዕከላት ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ ተመሳሳይነትና ልዩነት

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ኢምባሲ ከሚገኝባቸው ውስን አገሮች መካከል አገራችን ኢትዮጵያ በሰስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች:: ከ 93 በላይ አገሮች ኢምባሲዎች፤ ዓለም አቀፍ የረድኤትና ልዩ ልዩ ድርጅቶች ከአገራችን ጋር የሁለትዮሽ ግንኙነት መስርተው የፖለቲካና ዲፕሎማሲ ግንኙነታቸውን እያካሄዱ ይገኛሉ :: ከእነዚሁ አገሮች መካከል በላቀ ደረጃ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት በመፍጠር በባህልና በኪነ ጥበብ ረገድ የተለየ ቅርበት እንዲኖር በማድረግ የባህል ማዕከላት ከፍተው የሚንቀሳቀሱት ከተጠቀሱት ውጪ የራሺያ ኢምባሲን ጨምሮ ፈረንሳይ ፥ጀርመንና ጣሊያን ናቸው :: ለሙያው ዘርፍ እድገት የቋንቋና የባህል ልውውጥ በማድረግ ረገድ በሰጡት የትኩረት አቅጣጫዎቻቸው አንድነትና ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል ::/ ለነገሩ በሃገራት ቀደምት አምባሲ የከፈቱ ብቻ ሳይሆኑ የባህል ማዕከላትን አቋቁመው ለረጅም ጊዜ የቀጠሉ ብቸኛ ሃገራትም ናቸው /::

በባህል ማዕከላቱ መካከል የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን ሲያቀርቡ የአገራቸውን ባህልና የኪነ ጥበብ ትሩፋት የማስተዋወቅና የማስፋፋት ዋነኛ ዓላማ ያላቸው ሲሆን ፤ የአውሮፓውያንን ባህልና የፊልም ፌስቲቫል ሳምንቶችን የሚያከብሩበት ተግባራቸው ያመሳስላቸዋል :: ሌሎች የአውሮፓ አገሮች የማያደርጉትን ተግባር በመፈጸም እነዚሁ አገሮች ትኩረት በመስጠት ተመሳሳይነት አላቸው ::

የባህል ማዕከላቱ ለባህልና ኪነ ጥበብ ዝግጅቶች የሚንቀሳቀሱትን ያህል የቋንቋ ትምህርታቸውን ከሌሎች የአውሮፓም ይሁን አሜሪካን ጨምሮ የማይተገብሩትን ተግባር እነዚህ አገሮች ትምህርት ቤቶችን በመክፈት ቋንቋቸውን በማስፋፋት በኩል ተመሳሳይ ተግባሮችን ያከናውናሉ ::

ሶስቱም አገሮች በኪነ ጥበብ ዘርፍ በዋናነት የትኩረት አቅጣጫቸው በሙዚቃ፥ በስነ ስዕልና ስነ ጽሑፍ ላይ መሆኑ ተመሳሳይነታቸውን ያጎላዋል :: እንዲሁም ለኢትዮጵያውያን የኪነ ጥበቡ ታዳሚዎች ግብዣ ጥሪ የሚያደርጉበት አጠራር ተመሳሳይነት ይስተዋልበታል :: በኢምባሲዎች፥ በታላላቅ ሱፐር ማርኬቶች ፥በዩኒቨርስቲዎች፥ ፖስተራቸውን ከመለጠፍ አንስቶ በዝግጅቶቻቸው ወቅት ለሚያውቋቸው የዘወትር ታዳሚዎች ኢሜል በማድረግ ጥሪ ያስተላልፋበታል ::

የባህል ማዕከላቱ ለኢትዮጵያውያን የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የጥበብ ስራቸውን እንዲያሳዩ መድረኩን በማመቻቸትና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት ከአድናቂዎቻቸው ጋር እንዲገናኙ የሚያደርጉበት የአሰራር ስልታቸው አንድነታቸውን ያመለክታል ፡፡ በአገር ውስጥ በጀመሩት ድጋፍ መነሻነትም በርካታዎችን ለዓለም አቀፍ ዝናና ታዋቂነት ደረጃ እንዲሸጋገሩ በማስቻሉ ረገድ የጋራ ተመሳሳይ ተግባር ይታይባቸዋል ፡፡

የባህል ማዕከላቱ ለኢትዮጵያውያን የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች መድረኩን በመፍጠር ለታዋቂነትና ዝነኝነት ደረጃ እንዲበቁ የሚያግዙትን ያህል የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝ በማድረጉ በኩል ተመሳሳይ አሰራሮችን ይከተላሉ ፡፡ ለታዋቂ የሙዚቃ ሰው ወይም ሰዓሊ የውጪ አገር ጉዞውንና መድረኮችን በማመቻቸት ረገድ ትልቅ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ ፡፡

በሶስቱ የባህል ማዕከላት ሌላው ተመሳሳይ ተግባራቸው የየአገሮቻቸውን ታዋቂና ስመ ጥር የኪነ ጥበብ ሰዎችን ወደ ኢትዮጵያ በመጋበዝ የተለያዩ ስራዎቻቸውን በመድረክ ላይ በማቅረብ ለኢትዮጵያውያን የኪነ ጥበብ አፍቃሪያን የጥበብና የባህል ሽግግር በመፍጠር ትልቅ ትኩረት ሰጥተው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ሙያዊ ትንታኔና ልምዱን እንዲያካፍል የሚያደርጉት አሰራርም ተመሳሳይነት ይታይበታል፡፡ ከአገራቸው የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች በተጨማሪ ቋንቋቸውን ተናጋሪ ከሆኑ የአፍሪካ፥ የአውሮፓና ከሌሎችም አገሮች በማስመጣት የኪነ ጥበብ ትሩፋታቸውን ለኢትዮጵያውያን በማቅረብ ሰፊ የሆነ የማስተዋወቅ ስራዎችን ያከናውናሉ ፡፡

በሌላ በኩል የአንዱ ባህል ማዕከል የኪነ ጥበብ ዝግጅት በሚያቀርብበት ወቅት ሌላው የባህል ማዕከል ተመሳሳይ ዝግጅት በማዘጋጀት ለተመልካች እንዳያስቸግርና የፕሮግራም መደራረብ እንዳይፈጥር በመነጋገርና «እንደዚህ አይነት ፕሮግራም አዘጋጅቻለሁ» በሚል የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ረገድ ተመሳሳይነት ይስተዋልባቸዋል ፡፡

ለሚያዘጋጁት ማናቸውም አይነት የኪነ ጥበብ የፈጠራ ስራዎች ከነናቸው ታዋቂ ኢትዮጵያውያንን በመጋበዝና የማማከሩን ስራ በመስጠት ለዝግጅቱ ማማር ትኩረት እንደሚሰጡበትና በስተመጨረሻም የተዋጣለት ዝግጅት በማቅረብ በጥበብ አድናቂዎች ዘንድ ተወዳጅ ዝግጅቶች እንዲያቀርቡ የሚያድርጉበት የአሰራር ስልት ተመሳሳይነት እንዲታይባቸው ያደርጋቸዋል ፡፡

በፈረንሳይ ፥ጀርመንና ጣሊያን የባህል ማዕከላት ኪነ ጥበባዊ እንቅስቃሴ ዙሪያ ተመሳሳይነት የመኖሩን ያህል በሚያቀርቡት ዝግጅትና አቀራረብ ዙሪያ ደግሞ ልዩነት

እንዳላቸው እንመለከታለን ። በቅድሚያ ፈረንሳይን መመልከት ይኖርብናል ። የፈረንሳይ ባህል ማዕከል አሊያንስ ኢትዮ- ፍራንሲስ በሚል በአዲስ አበባ ና በድሬዳዋ የቋንቋ ትምህርት ቤቶችን ከፍቶ በእነዚሁ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ የኪነ ጥበብ ትሩፋትን በማቅረብ የኪነ ጥበብ አፍቃሪዎችን ፋላጎት በማርካት በኩል ጉልህ ሚና ይጫወታል ። በዚህም በስሙ ከሁለቱም የባህል ማዕከላት የላቀ ታዋቂነትን አግኝቷል(ዳንኤል ወርቁ፤በቀለ መኮንን፤እዝራ አባተ)። በሌሎች የባህል ማዕከላት በኩል ግን ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ከተሞች ዝግጅቶችን አያቀርቡም።

የፈረንሳይ የባህል ማዕከል ከሁለቱ ማዕከላት በዋናነት የሚለየው በሙዚቃ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራቱ ነው ። «የኢትዮጵያ የሙዚቃ ፌስቲቫል» የሚል ዝግጅት ከማዘጋጀት አንስቶ ዝነኛ የሙዚቃ ሰዎች የሚታወሱበትን መድረክ በመፍጠር እንዲሁም አሁን አሁን በከተሞች አካባቢ እየቀነሰ የመጣውን የአዝማሪዎች የሙዚቃ ስራ መድረክ በመስጠትና ቅርጹን ይቀይር እንጂ ባህላዊነቱ እንዳይጠፋ የሚያደርጉት ድጋፍና አስተዋጽኦ እንዲሁም በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኙና ከውጪ አገር የሙዚቃ ባለሙያዎች ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ በማድረግ በኩል የሚያደርጉት ልዩ ልዩ የሙዚቃ እንቅስቃሴዎች ከሌሎች የባህል ማዕከላት እንዲለዩና መታወቂያቸው እንዲሆን አድርጓቸዋል ። በኢትዮጵያ የሙዚቃ ፌስቲቫል የተቀረጹትን ጥራታቸው ከፍ ባለ የውጪ ስቱድዮዎች ተዘጋጅተውና በሲዲ መልኩ ተቀርጸው እንዲቀርቡ የሚያደርጉት አሰራርም ልዩ ያደርጋቸዋል ። በሌላ በኩል ግን ይሔው የሙዚቃ ስራቸው ከአካዳሚያዊ ይልቅ የመዝናናት ተግባር ላይ ብቻ ማተኮሩም ልዩ እንዲሆን ያደርገዋል(እዝራ አባተ)።

በሙዚቃ በኩል ኢትዮጵያውያንን በፈረንሳይና በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ትርዒታቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ ረገድም ከሌሎቹ ባህል ማዕከላት በላቀ ደረጃ ተጠቃሽ ያደርጋቸዋል ። በርካታ የውጪ አገር ዜጎችን የአገራቸውንና ፈረንሳይኛ ተናጋሪ የሆኑ አገሮችን ወደ አገር ውስጥ በመጋበዝ የተለያዩ የሙዚቃ ስራዎቻቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ ረገድም የፈረንሳይ ባህል ማዕከል ተወዳዳሪ የለውም ። በሌላ በኩል አሊያንስ የኢትዮጵያንና የፈረንሳይን ሙዚቃ በማዳቀል፤በመቀላቀልና በማዋሃድም ሙዚቃቸውን የሚሰሩበትና የሚያቀርቡበት ሂደትም አለ ። አሊያንስ የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ በአብዛኛው ትኩረት ሲያደርግ ከሙዚቃው በመቀጠል የስዕል ኤግዚቢሽኖች በማዘጋጀት ረገድም ከፍተኛ ስራ ያከናውናል ። የስነ ጽሑፉ ግን ዝቅተኛ ነው።

ወደ ጀርመን የባህል ማዕከል ስንመጣ በስነ ስዕል ÷ ሙዚቃ ÷ ስነ ጽሁፍ ና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ማዕከሉ ከሌሎች የባህል ማዕከላት የሚለይበትን አስመልክቶ የፕሮግራሙ ዳይሬክተር ወይዘሮ ተናኜ እንደሚገልጹት፤

> የጎተ ኢንስቲትዩት /የጀርመን ባህል ማዕከል/ የሚያቀርባቸውን የኪነ ጥበብ ስራዎች ዝግጅታቸውን ካቀረቡ በኋላ ተደምሞና ተደንቆ የሚታለፍባቸው ሳይሆኑ ፤ትምህርታዊ ውይይቶችን በማካሄድ ወደ ትምህርታዊ ውይይት እንዲያዘነብሉ ይደረጋል ፡፡ ስዕልም ይሁን ሙዚቃ ስናዘጋጅ ውይይት እንዲደረግ እናደርጋለን ፡፡ የዘርፍ ባለሙያተኞችን በመጋበዝ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ ዲሞክራሲ እና ሶሻል ተቋማት የሚል ረጅም ጊዜ ውይይት ተደርጓል ፡፡ በሃይማኖቶች ዙሪያም ውይይት ተደርጓል (ትናኜ ታደሰ ታደሰ/23/9/2001 ዓ.ም)፡፡

የጀርመን ባህል ማዕከል በውይይቶች ላይ ትኩረት በማድረግ የኪነ ጥበቡን ስራ ለማሳደግ ጥረቶችን አድርጓል ፡፡ አዳዲስና ያልተሞከሩ ርዕሰ ጉዳዮችን በመፍጠር ህብረተሰቡ የመነጋገሪያ አጀንዳ እንዲያደርጋቸውና የእነዚያ የለውጥ ውጤቶች ተጠቃሚ እንዲሆን የፈር ቀዳጅነትን ስራ ይሰራል ፡፡ ለምሳሌ የንባብ ባህል እንዲዳብር« አዲስ አበባ ታንብብ» የሚል የንባብ ሳምንት አዘጋጅቶ ህብረተሰቡ የአመለካከት ለውጥ በማምጣት እንዲንቀሳቀስ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በስነ ጽሑፉ ዙሪያ የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፎች ላይ ሙያዊ ውይይትና ለወጣቶች እድል የሰጠ ዝግጅት አድርጓል፡፡ በርካታ የጀርመን ገጣሚያንን፤የአጭር ልቦለድ ስራዎችንና ታሪኮች እንዲተረጎሙና እንዲታተሙ አድርገዋል፡፡

ማዕከሉ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከገባ በኋላ ለስመ ጥሩ የስዕል ሰው ገብረ ክርስቶስ ደስታ ቋሚ የስዕል ኤግዚቢሽን ማሳያ ማቋቋሙ ልዩና ለባለሙያው እውቅና በመስጠት እንዲታወቅ ያደረገበት አሰራሩ ከሌሎቹ የባህል ማዕከላት እንዲለይ ያደርገዋል፡፡

እምብዛም የማይደፈረውን የክርስትናና የእስልምና እምነቶች ተከባብሮና ተቻችሎ የመኖር ምስጢርን በምርምርና በውይይት በማካሄድ ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አገራችን የራሷ የሆነ ጥበብ እንዳላት ለማሳየት ተችሏል፡፡

የባህል ማዕከሉ በተለያዩ የዓመቱ ጊዜያት ባወጣቸውና በሚያወጣቸው የትርኢትና ውይይት መርሃ ግብሮች መሰረት በጥበብ ዙሪያ/ በሙዚቃ ÷በስነ ጽሑፍ÷

በስነ ስዕል÷ በተውኔት ÷ በፊልም ÷ በዳንስ / በፕሬስ ዳይጀስት ዙሪያ÷ በሴቶች በመሳሰሉት የሚያደርገው ተሳትፎ ከሌሎች ባህል ማዕከላት እንዲለይ ያደርገዋል ::

የጣሊያን ባህል ማዕከል ቀዳሚ ትኩረቱ ስዕል ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ወደ ሙዚቃው አዘንብሎ ይገኛል። በርካታ የስዕል ባለሙያዎች የስዕል ስራቸውን በማቅረብ ለከፍተኛ ዝና የበቁበት መድረክ መሆኑን ነው የሚናገሩት። ባህል ማዕከሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የስዕል ኤግዚቪሽን በማሳየትም ቀዳሚ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የበርካታ ሰዓሊያን ኤግዚቪሽን ለማቅረብ ተመራጭ ቦታ መሆን ወደ ስዕሉ ዘርፍ እንዲያተኩር እንዳስገደደው ፕሮፌሰር ቡሩኖ ያስረዳሉ።

ሌላውና ማዕከሉን ልዩ የሚያደርገው የሙዚቃ ዝግጅት የሚያቀርቡ የውጭ አገር ዘፋኞችን ከጣሊያን አገር ያስመጣል እንጂ ቋንቋውን ይናገራሉ በሚል ከሌሎች አገሮች ዘፋኞችንና የዳንስ ባለሙያዎችን አስመጥቶ የኪነ ጥበብና የባህል ትውውቅ ለማድረግ አይፈልግም ::የክላሲካል፣ የኦፔራ ዘፈኖችንን በብቸኝነት በማቅረብና የባሊ ዳንሶችን በማስመጣትና በማስተዋወቅ ረገድ ማዕከሉን ለየት ያደርገዋል።ከአገራችን የሙዚቃ ባለሙያዎች ዘመናዊ ባንዶችና የፒያኖ ሙዚቃዎች ላይ የማተኮር ባህሪዎች ይስተዋልባቸዋል። ለያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ለሚያቀርባቸው ህብረ ዝማሬ ዘፈኖች የባህል ማዕከሉ የተለየ ክብር በመስጠት ላይ በማተኮሩ ከሌሎች ባህል ማዕከላት ይለያል ::

የጣሊያን ባህል ማዕከል በሌሎች ወጣ ባሉ ስራዎች ከሚታወቅበት አንዱ የከተሞችን ውበት አርክቴክቸራል ስዕሎች የቀድሞዋ አዲስ አበባ ከተማ ምን ትመስል እንደነበረና ቀጣይዋ አዲስ አበባ ምን እንደምትመስል የዘርፉ ባለሙያዎች የራሳቸውን ምናባዊና እውናዊ አርክቴክቸራል ንድፍ በማቅረብ ውይይት የሚያደርጉበት አሰራር ነው።ማዕከሉ ከሌሎች የሚለየውን የትኩረት አቅጣጫ አስመልክቶ ፕሮፌሰር ቡሩኖ እንደሚገልጹት በሳይንስና ተክኖሎጂ ዙሪያ ከዩኒቨርሲቲ ና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጋር በማወዳደርና ሽልማት በማዘጋጀት የተፎካካሪነት ስሜት እንዲፈጠር በማድረግ ወጣቶች ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ልዩ ፍቅር እንዲያድርባቸው በማድረግ ማዕከሉ ይንቀሳቀሳል ::

## 7. ማጠቃለያና ይሑንታዎች

ይህ ጥናት የፈረንሳይ ፣ የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከሎች የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ታሪክ ላይ ያተኮረ ነው:: በቀዳሚነት ሃገራችን ከሌሎች አገሮች ጋር የሁለትዮሽ ግንኙነት በአንኮበሩ ቤተመንግስታቸው ከጀመሩበት ከ1889 ዓ.ም. ዐጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት አንስቶ እስካለንበት ዘመን ድረስ ከ93 አገሮች ጋር የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ግንኙነት በማድረግ ላይ ትገኛለች ። ከእነዚህ ሁሉ አገሮች መካከል የራሳቸውን የቋንቋ ትምህርት ቤት በመክፈት የየአገሮቻቸውን ቋንቋና ባህል በማስፋፋትና በማስተዋወቅ ረገድ ሶስቱ አገሮች ከፍ ያለ ሚና እየተጫወቱ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል ።

ከአንድ መቶ አራት እስከ አንድ መቶ አስራ አራት ዓመት በዘለቀው የሶስቱ አንጋፋ አውሮፓዊ አገሮችና የኢትዮጵያ የሁለትዮሽ ግንኙነት ከፖለቲካዊና ዲፒሎማሲያዊ ግንኙነት በላቀ ደረጃ ወደ ህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ደረጃ እንዲያድግ የኪነ ጥበብና የባህል እንቅስቃሴዎች እገዛ አድርገውለታል ። በጥናቱ ላይ የየአገራቱን ታሪካዊ የግንኙነትና አጠቃላይ ጉዞ ለመዳሰስ ተሞክሯል ። በዚህ ጉዞ ውስጥ እነዚህ ባህል ማዕከላት መነሻቸው የቋንቋ ትምህርት መስጠት ቢሆንም በሂደት ግን የኪነ ጥበብ ዘርፍ ላይ ትኩረት በመስጠት የአገራቸውንም ሆነ የአገራችንን ኪነ ጥበብ በማሳደግና በማስተዋወቅ ረገድ ተንቀሳቅሰዋል ።

በባህል ማዕከላቱ ዝግጅታቸውን በማቅረብ በሚቀርቡ ዝግጅቶች በመታደም እውቀትንና መዝናናትን ያገኙ እድምተኞች የሚገልጹ መረጃ ሰጪዎች መኖራቸውን በጥናቱ ውስጥ ለማግኘት ተችሏል።

በእነዚሁ የቋንቋ ትምህርት ቤቶች የባህል ማዕከላትን መክፈታቸውና የኪነ ጥበብ ስራዎችን እንዲታዩ እንዲሁም እንዲቀርቡ ማድረጋቸው ቋንቋውን በቀላሉ ለማስረጽና ለመግባባት ከማስቻሉም ባሻገር ስለ አገራቸው ባህልና የኪነ ጥበብ ስራዎች ኢትዮጵያውያን እንዲያውቁትና መልካም አስተሳሰብና ወገናዊ መቀራረብ ለመፍጠር እንዳስቻለ ለመረዳት ተችሏል ።

የባህል ማዕከላቱ በዋናነት የአገራቸውን ባህልና ኪነ ጥበብ ማስተዋወቅና ማስፋፋት ቢሆንም ዓላማቸው በሂደት ግን የኢትዮጵያን ባህልና ኪነ ጥበብ በማስተዋወቅና

መድረኩን በመፍጠር፤ሙያውና ባለሙያዎች እንዲተዋወቁ እገዛ ማድረጋቸውን ከጥናቱ ለማግኘት ተችሏል፡፡ በተለይም የስዕል ጥበብ እምብዛም ዕውቅና ባላገኘበትና መድረክ እንኳን አግኝተው ከአድናቂዎቻቸው ጋር መገናኘት በማይችሉበት ወቅት/ በ1950 ዎቹ/ መድረኩን በመፍጠር ኤግዚቢሽኖችን በማዘጋጀት እንዲተዋወቁና ሙያው እንዲያድግ ከዚያም ሲያልፍ በስዕል ሽያጭ መተዳደር እንደሚቻል ሰፊ እገዛ አድርገዋል ፡፡ ለበርካታ ጀማሪ ሰዓሊዎች መነሻ ና ማደጊያ ስፍራዎች ሆነዋል፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ እንዲሆኑና የኪነ ጥበብ ስራዎቻቸውን በዝነኛ ዓለም አቀፍ ጋለሪዎች ለማሳየት እንዲበቁ የባህል ማዕከላቱ ድጋፍ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም ፡፡

በተመሳሳይም ለአገራችን ሙዚቃና ሙዚቀኞች በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሙያውና ሙያተኞች እንዲታወቁና በሙያቸውም እድገት እንዲያገኙና እንዲጠቀሙ ባህል ማዕከላቱ ላቅ ያለ ድጋፍ አድርገዋል ፡፡ በርካታ አንጋፋ የሙዚቃ ሰዎች መታሰቢያ ቀኖች እንዲኖራቸው በማድረግ የጥበብ ስራዎቻቸው እንዲታወሱና እንዲዘከሩ በማድረግ የአስተዋሽነት ሚናን ተጫውተዋል ፡፡ ከውጭ አገር ታዋቂ የሙዚቃ ባለሙያዎችን በማስመጣት ልዩ ልዩ የሙዚቃ ኮንሰርቶችን በማዘጋጀት÷ከማዝናናቱም ባሻገር በሌክቸርና የሙያ ልምድን በማካፈል ለሙዚቃ ትምህርት ቤቱ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ የዳንስና ሰርከስ እንዲሁም በሙዚቃ መሳሪያዎችና በታዋቂ ዘፋኞች ስራ ውይይትና ምርምር በማድረግ ለሙያው ማደግ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በበገና ÷ በማሲንቆ ÷ በከበሮ ና በዋሽንት በመሳሰሉት ዙሪያ አውደ ጥናቶችን በማቅረብ በሙዚቃ መሳሪያ ምርምር በማካሄድ በጥበቡ ዙሪያ እውቀት እንዲኖር በማድረግ፤ታዳሚዎች የባህል ሙዚቃ እንዲማሩና የሙዚቃ መሳሪያዎች በአገር ውስጥ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ እንዲታወቁ ማዕከላቱ ድጋፍ ማድረጋቸውን ከዝግጅታቸው መረጃዎች ለማግኘት ተችሏል፡፡

ለስነ ጽሑፍ የኪነ ጥበብ እድገትም ቢሆን ከጀማሪ የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች አንስቶ እስከ አንጋፋ የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች÷ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር፤የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማሕበር፤ለኢትዮጵያ ህጻናት ድራሲዎች ማህበር እና ለአማተር የስነ ጽሑፍ ማህበራት የስነ ጽሑፍ ዝግጅታቸውን እንዲያቀርቡ በማመቻቸት ÷ አንዳንድ የስነ ጽሑፍ ስራዎችን በማሳተምና በማስተርጎም በርካታ

ስራዎችን ለንባብ እንዲቀርቡ ተደርገዋል ። የንባብ ባህል እንዲዳብር በማድረግም ለስነ ጽሑፍ ማበብ የአንባብያንን ቁጥር የማሳደግና ለስነ ጽሑፍ ንባብ ፍቅር እንዲኖር አዲስ አበባ ታንብብ አይነት ፕሮጀክቶች ተቀርጸው እንቅስቃሴዎች በመካሄድ ላይ ናቸው።

ከውጭ አገርም ታዋቂ የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎችን በማስመጣት ሙያዊ ትንታኔ ስለ ስነ ጽሑፍ፤ ሂስ የትርጉም ስራዎች የእውቀት ሽግግር እንዲኖር በማድረግ በኩል በተለይም የጀርመን ባህል ማዕከል ተንቀሳቅሷል ።

በተመሳሳይም የምናጠናው የኪነ ጥበብ ዘርፍ ባይሆንም ለተውኔት÷ ለልብስ ዲዛይነሮች÷ ለቁንጅና ተወዳዳሪዎች÷ ለፊልም ባለሙያዎች÷ለዳንሰኞች÷ ለጋዜጠኞች÷ለቅርጻ ቅርጽ ሞያዎች የኪነ ጥበብ እድገት የባህል ማዕከላቱ ያደረጉት ድጋፍ ሊነገርለት የሚገባ እውነት ነው ።

በሌላ በኩል እነዚሁ አገሮች የኪነ ጥበቡንና የባህል ትውውቅ እንዲሁም የቋንቋ ማስፋፋቱን የሚያከናውኑት በአገራቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ድጋፍ አማካኝነት ነው ። ይሁን እንጂ በአገራችን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን የባህል ማዕከላቱን እንቅስቃሴ በቅርበት ያለመከታተላቸውና በሚቀርበው ዝግጅት ላይ የራሳቸውን ሚና ወይም ገጽታ ግንባታ ለመስራት አለመሞከራቸውን ለማስተዋል ተችሏል ። በዚህ አጋጣሚ ስለ ሃገራችን ጉዳይና የህዝባችንን ሁኔታ ለየአገራቱ የመልካም መተሳሰብና ምኞት መግለጫዎች የሚሰጡት እንኳን ራሳቸው የየኢምባሲዎቹ የባህል ማዕከላት መሆናቸውን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው ። እዚህ ላይ መነሳት የሚገባው የባህል ሚኒስቴር የኪነ ጥበባቱ ዘርፍ ባለሙያዎች ያሉት ከመሆኑ አንጻር ሚኒስቴሩን ጨምሮ የተለያዩ ባለሙያዎች የኪነጥበባቱን ዝግጅቶች መከታተል ቢችሉ ባህል ማዕከላቱም የመንግስት ክትትልና ድጋፍ እንደሚደረግላቸው በማመን የበለጠ በዚህ ዙሪያ ስራዎችን ለመስራት የሚችሉበትን እድል ማስፋት ይቻል ነበር የሚል ሃሳብ አለ።

እዚህ ላይ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴርን ለማንሳት ተሞከረ እንጂ የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና የፌዴራል ባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር በባለቤትነት ስሜት ባህል ማዕከላቱ የሚሰሩትን አለመከታተላቸውና ምን እንደሚቀርብ እንኳን አለማወቃቸው አጥኚውን አግራሞት የፈጠረበት ጉዳይ ሆኗል ።እዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የተቻለው በባህል ማዕከላቱ ዙሪያ መረጃ ለማግኘት ቃለ መጠይቆችን

በማዘጋጀትና በአካል ተገኝቼ የሚመለከታቸውን አካላት ባነጋገርኩበት ወቅት ምንም አይነት መረጃ እንደሌላቸውና ወደፊት የሚሰሩትንና የሚያቀርቡትን የኪነ ጥበብ ስራዎች ለመመልከት እንደሚሞክሩ በመግለጻቸው ያገኘሁት መልስ ነው ።

በመሆኑም በሃገራቱ መካከል የባህልና የኪነ ጥበብ ልውውጡና እንቅስቃሴው እንዲጠናከር ፤እንዲሁም አገራችንን በትክክል የሚወክሉ የኪነ ጥበብና ባህል ስራዎች እንዲቀርቡ ከማዕከላቱ ጋር በጋራና በትብብር በቅርበት መስራት ያስፈልጋል ። የኪነ ጥበብ የፈጠራ ስራዎች በሚቀርቡባቸው በእነዚህ ባህል ማዕከላት ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ ለሚያደርጉ ወጣቶች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ዘላቂነት ያለው የኪነ ጥበብ መፍለቂያ መድረኮች እንዲሆኑ ሙያዊ ና የቴክኒክ እገዛዎችን መስጠት ይኖርባቸዋል ።

እንደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፤ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ አይነቶች የትምህርት ክፍሎቻቸው በስነ ጽሑፍም ይሁን በቲያትሪካል አርት፤በሙዚቃ፤በስዕል፤ በፎክሎርና በአጠቃላይ ለኪነ ጥበብና ባህል ቅርብ የሆኑ የትምህርትና የምርምር ክፍሎች ከባህል ማዕከላቱ ጋር በጋራ የሚሰሩበትን አሰራር ቢዘረጉ የላቀ ሙያዊ መደጋገፍና በአገራት መካከል የተሻለ የባህል ልውውጥና የእውቀት ሽግግር ማምጣት ይቻላል የሚል እምነት አጥኚው አለው ።

የባህል ማዕከላቱም ለሚያቀርቧቸው ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ሃሳቡን ከማመንጨት አንስቶ እስከ ማስፈጸሙ ድረስ ባለው ሂደት ልሂቃኑን ከየሙያ ዘርፉ በማማከርና በማሳተፍ በስፋት ቢንቀሳቀሱ በአንዳንድ ዝግጅቶቻቸው ዙሪያ የሚነሱ ቅሬታዎችንና ችግሮችን ለመቅረፍና በትክክል ለታለመለት ዓላማ ለማዋል ያስችላል።የበለጠ አካዳሚያዊና ከመዝናናት ባለፈ እውቀት የሚገበይባቸው መድረኮች ማድረግም ያስችላቸዋል።

በተመሳሳይም የባህል ማዕከላቱ የሚያቀርቧቸው ዝግጅቶች ዘላቂነት ያለውና ለኪነ ጥበቡ ማደግ አስተዋጽኦ በማድረግ በኩል እንደያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ላሉትና አርት ስኩል ላሉት የዶክትሬት ዲግሪ ስልጠና በአገራቸው የሚያገኙበትን እድል ቢያመቻቹ ፤ይሄም ካልተቻል ለአንድ ዓመት ወይም ሴሚስተር ታዋቂ የአገራቸውን ምሁራን አስመጥተው ኮርስና ስልጠና ቢሰጡ በርካታ ባለሙያዎችን ለማፍራት ስለሚያስችል ይህንኑና መሰል የመሳሪዎች ድጋፍ በማድረግ ዘላቂ በሆኑ ስራዎች ላይ ቢሳተፉ ስራቸውን ሙሉ ያደርገዋል የሚል እምነት አለ። የያሬድ ሙዚቃ

ት/ቤትን የሰራው የቡልጋሪያ መንግስት መሆኑ ዘላቂ ስራ ለመስራቱ ማሳያ ሊሆነን ይችላል፡፡

እንዲሁም ባህል ማዕከላት በሚቀርቧቸው የሙዚቃ ስራዎች ላይ ከመዝናናቱ ባለፈ በተለይም የአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ በሳልና ምርምራዊ ሙዚቃውን ወደሚያሳድገው ተግባር ሊሳቡ እንደሚገባ መጠቆም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ባህል ማዕከላት በሚያቀርቧቸው ትልልቅ ፌስቲቫሎች ከራሳቸው ወጪ በተጨማሪ የስፖንሰር አድራጊዎች እጥረት አንዳንዴ ዝግጅቶችን ለማከናወን እስከመፈታተን ደረጃ የሚደርስበት አጋጣሚዎች እየተፈጠሩ ከመሆኑ አንጻር (ወ/ሮ መርሴማ ታሪኩ ፤5/10/03 ዓ.ም) በቀዳሚነት የራሳችንን የኪነ ጥበብ ስራዎች የምናስተዋውቅ ከመሆናችን አንጻር ፤የባህል ሚኒስቴር በዋናነት እና በተከታይም የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ድጋፍ በማድረግ ፌስቲቫሎች የሚቀጥሉበትን ሁኔታ በጋራ ሊያስቡበትና ሊሰሩ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በባህል ማዕከላቱ ድጋፍ የልምድ ልውውጥ ለማድረግና ስልጠና በአገራቸው የአጭር ጊዜ ስልጠና ለመስጠት ባደረጉት መጠነኛ እንቅስቃሴ በተለይም በስዕል፤በሙዚቃ እና በቲአትር ዝግጅታቸውን እንኳን ሳያቀርቡ የመጥፋት ሂደቱ ቀጣይ ስራውንና የኪነ ጥበብ ስራቸውን ለመስራት እንዳይችሉ እንቅፋት እየፈጠረ መሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው ፡፡ በዚሁ ችግር ምክንያት አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ የፖሊሲ ለውጥ ማድረጉንና ባለሙያዎችን አስመጥቶ ስልጠናውን መስጠት መጀመሩን ወ/ሮ መርሴማ አስረድተዋል፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ችግር የውጪውን ልምድ ለመካፈል እንቅፋት ሆነ ማለት ነው ፡፡ በስዕል ዘርፉም በተለይ በጀርመን ባህል ማዕከል ወደ ውጪ አገር ደርሰው የሚመጡ ወጣቶችም ተግባር የራሳቸው የሆነን ሙያና ማንነት እስከመርሳት የመድረሱ ተግባር የውጪ ጉዞ ልምዱን ውጤታማ አላማድረጉን የሚያሳስብ ጉዳይ ነው፡፡

የባህል ማዕከላቱ ለኪነ ጥበብና የባህል እድገት እያከናወኑት ያለው ተግባር ይበል የሚያሰኝ መሆኑ ከላይ የተገለጸው ማስረጃ እንዳለ ሆኖ፤ዝግጅቶች ከተላላፉ በኋላ ስለ ዝግጅቶች የሚያስረዳ ማስረጃ በጽሑፍ፤ በድምጽ ወይም በካሜራ ተቀርጾ አለመቀመጡ ስራቸውን ጎደሎ የሚያደርገው መሆኑን ለማረጋገጥ ይቻላል ፡፡ችግሩ

በሶስቱም ባህል ማዕከላት የሚታይ ቢሆንም በጣሊያን ባህል ማዕከል ያለው ግን በተለይ በቤተመጻህፍቱ ውስጥ ስለቀረቡ ዝግጅቶች መረጃ አለመገኘቱ ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል።

ይህንን ጥናት ለማዘጋጀት በባህል ማዕከላቱ ውስጥ በተገኘሁበት ወቅት ያጋጠመኝ የመጀመሪያው ትልቁ ፈተና የተሰነደ መረጃ ለማግኘት መቸገሬ ነው። እዚህ ላይ ሁሉም የባህል ማዕከላት ዘመናዊና የተደራጁ ቤተ ንባባት/መጻህፍት/ አላቸው ። ይሁን እንጂ የጀርመን እጅግ አነስተኛ መረጃዎች ከማግኘቴ ውጪ በሌሎቹ ከዚህ ቀደም ያቀረቧቸውን የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች በተመለከተ መረጃ አላስቀመጡም ።

ስለሆነም ሶስቱም የባህል ማዕከላት ለቀጣይ አጥኚዎችና ትውልድ ሆነ መረጃ ፈላጊዎች በየጊዜው የሚያቀርቧቸውን የኪነ ጥበባት ዝግጅቶች በጽሁፍ እና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ቀርጸው ቢያስቀምጡ የተሻለ ተግባር መሆኑን ለመግለጽ እፈልጋለሁ ።

በተጨማሪም እነዚህን የኪነ ጥበባትና የባህል ዝግጅቶች ከማቀድ አንስቶ ሂደቱን በባለቤትነት የሚመራና የሚከታተል ቋሚ ስራው ይኸው ብቻ የሆነ ባለሙያ እንደሚያስፈልጋቸው መጠቆም ይፈለጋል ። በተለይም በጣሊያን ባህል ማዕከል ባለሙያ ባለመኖሩ መረጃ ሰጪ አካል ለማግኘት አስቸጋሪ ያደርገዋል ። ስለዚህም ባለሙያው የህዝብ ግንኙነት ሊሆን ይችላል ።የህብረ ትርኢቶች ወይም የባህል ባለሙያም ሊሆን ይችላል ። ዋናው ቁም ነገሩ መረጃዎችን ከማደራጀት አንስቶ ለመረጃ ፈላጊው ከእንግልት ነጻ ሆኖ ትክክለኛ መረጃውን ለማግኘት እንዲችሉ የማመቻቸቱን ስራ እንዲሰራ እማድረጉ ላይ ነው። የባህል ማዕከላቱን ተግባርም ለህብረተሰቡ በአግባቡ በመግለጽ መልካም ገጽታን የመገንባቱን ስራ መወጣት እንዲችል ማድረግ ያስፈልጋል ።

## ዋቢ መፅሐፍት


መታሰቢያ መላኩ፣ የሙዚቃ መማርያ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991ዓ. ም።

ታዬ ታደሰ፣ አንዳንድ የኢትዮጵያ ሰአሊዎች አጭር የህይወት ታሪክ ከ1869-1975 ዓ.ም፤ክፍል አንድ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤1976

ቢሮ ዣክ፤ ፈረንሳይና ኢትዮጵያ፤ የመቶ አመት ወዳጅነት አጭር የታሪክ ማስታዋሻ/ዣክ ማዕከል፤1989 ዓ.ም

አባተ መንግስቱ፤ መሰረታዊ የስዕል ጥበበ መማሪያ፤አዲስ አበባ፤ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፤ 1992

አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ፤ የመቶኛ ዓመት ክብረ በዓል የወጣ ፤መፅሔት፤ 2000 ዓ.ም

ሮዝ መጽሄት ቅጽ 4 ቁጥር 60 መጋቢት 2002 ።ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፤2002

ነጋድራስ ጋዜጣ ጥቅምት 15 ቀን 2003 ዓ.ም.። ብርንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፤2003 ዓ.ም.

ደስታ ተክለወልድ፣ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

Ashenafi, Kebede. The Music of Ethiopia: Its Development and Cultural Settings. Ph.D Dissertation In Music. Middletown: Wesleyan University, 1971.

_______. Roots of Black Music. Trenton Newgersy: Africa World Press, 1995.

Bunt ,Cyril Gothic Painting , London : Avalon press,1947

Cultural center The New Encyclopedia Britannica. New York:Oxford University Press , 2009.

Edward J.ward,The Social Construction of Community.Delhi Bombay:Calcutta,Madras Karachi,1997

Ethiopia German100 Years Diplomatic Relation catalogue;, 2005

Goldstein, Kenneth S. A Guide for Field Workers in Folklore. London: Folklore Associates, Inc., 1964.

Gordon, Marshall, The concise Oxford Dictionary of Sociology,New York:Oxford University Press,1994.

Gotshalk, D.w. Art and The Social Order,Dover publication. 1962

Hauser, Arnold. The Social History of Art,NewYork; vintage books, Vol 3, 1952

Levari, Norma. The Art and Hostory of Books.New York:James H.Heineman Inc,1968

Leslie A.white.The evolution of culture:McGraw Hill Book Company,Inc.1959

Pierre Bourdieu. Cultural Reproduction and Social Production. Putnam: Cooper Square Publishers Inc,1973

Powne, Michael. Ethiopian Music: An Introduction: Asurvey of Ecclesiastical And Secular Music And Instruments. London: Oxford University Press. 1968.

Teklehaimanot Gebreslassie. "A Brief Survey Study of the Azmaris in Addis Ababa." Proceedings of The International Symposium on The Centenary of Addis Ababa. Institute of Ethiopian Studies. Addis Ababa University,1986. pp.161-170.

Zenebe Bekele. Music in the Horn: Preliminary Analytical Approach to the Study of Ethiopian Music. Sweden: Stockholm, 1987.

40th Anniversary Goethe institute ፤2002

Reporter News paper, Encouragment toward Global literary completion, April2, 1997

# አባሪዎች

አባሪ 1

## መግለጫዊ መዘርዝር

### የፈረንሳይ ባህል ማዕከል

ሥዕል

ማስታወሻ ፡በዝግጅቶች ላይ የተጠቀሱት ቀኖች እ.ኤ.አ ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | የኪነ ጥበባዊ ዝግጅቱ ርዕሰ ጉዳይ | አዘጋጅ | አቅራቢ | የተካሄደበት ቦታ | የተካሄደበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በሴቶች ውበት መደነቅ በተሰኘ ርዕስ የቀረበ ስዕል | | ነብዩ ተስፋዬ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | ህዳር9-23,2005 |
| 2 | የኢትዮጵያ ስዕሎች በጥንታዊት የትግራይ ቤተክርስቲያን | | ጃኩሲ ሜርሲ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | ህዳር፣10፣2005 |
| 3 | የሰው ፊቶች | | በሃይሉ በዛብህ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | ሚያዚያ 5-22፣2006 |
| 4 | ጎታ፤ተረት ተረት | | ኤልያስ ስሜ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | ግንቦት4-20/2006 |
| 5 | ከአዲስ አበባ-ድሬድዋ የምድር ባቡር ሰራተኞችን ህይወት የሚያሳይ ስዕልና ቅብ | | | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 29/11/07 |
| 6 | የአርት ታሪክ | | በሃይሉ በዛብህ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 7/12/07 |
| 7 | የጋራ ስዕል | | አዲስ ገዛሃኝ፤አስናቀ መለስ፤አዱኛ ካሳ፤ብሩክ ማሞ፤ ምህረት ዳዊት ፤ለይኩን | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 7/11/08-19/11/08 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ናሁሰናይ | | |
| በድሬደዋ ፤ሐረርና አዲስ አበባ የተመለከታቸውን የዘይት ቅቦች ስዕሎች | | ጁሊያንስ ሶል | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 28/11/08-8/12/08 |
| በአማርኛ አልፋ ቤቶች ላይ ስዕል የቀረበ | | ሱዚ ጫኔ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 15/1/08 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | ዘሪሁን የትም ጌታ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 8/12/08-28/12/08 |
| የተፈጥሮ ስዕል | | ገነት ዓለሙ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 17/3/09-28/3/09 |
| ጥንታዊ ሥዕሎችና ግራፊክስ | | ባርባራና ወርቁ ጎሹ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 31/3/09-14/4/09 |
| የኤሪክ ዱቦይስ ስዕሎች | | ፍራግ ማንትስ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 16/4/09-28/4/09 |
| 27 ሰዓሊያን ኢትዮጵያውያን 27 የአውሮፓ ከተሞችን በስዕላቸው ይገልጻሉ | | 27 ሰዓሊን | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 7/5/09-13/5/09 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | ደስታ ሐጎስ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 28/5/09-10/06/09 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | ዳዊት አበበ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 16/6/09-1/7/09 |
| አዲስ አበባ በውስጧ የያዘችው የተለያየ አኗኗር የሚያሳይ ስዕል | | አዲስ ገዛሃኝና ዓዲስ አለም ዘውዴ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 5/09/09-15/09/09 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 18 | ሥላሴ ስዕል በሶስት ሰዓሊያን | | ሰባስቲን<br>ካሉክስ፤ኢየሩ<br>ሳሌም አበራና<br>ለይኩን<br>ናሁሰናይ | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 25/09/09-<br>10/10/09 |
| 19 | የስዕል ኤግዚቢሽን | | ዳዊት<br>አድነው | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 13/10/09-<br>30/10/09 |
| 20 | የስዕል ቅብ | | ፓስካል ዴኑ | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 15/11/09-<br>19/11/09 |
| 21 | የጉዞ ማስታወሻ ስዕል | | ኒኮላስ ዴሉ | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 24/11/09-<br>10/12/09 |
| 22 | የስዕል ሽያጭ ባዛር | | የተለያዩ<br>ሰዓሊዎች<br>ስራ | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 12/12/09-<br>13/12/09 |
| 23 | ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስዕሎች | | ተከስተ<br>ይበይን | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 17/12/09-<br>30/12/09 |
| 24 | የኩመካና ቀልድ ስዕሎች | | ጆል<br>አሊሴንድራ | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 12-25/1/10 |
| 25 | ባዶ ክፍሎች | | እንግዳ ጌጥ<br>ለገሰ | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 16/2/10-1/3/10 |
| 26 | የስዕል ኤግዚቢሽን | የሰርቢ<br>ያ<br>ኢምባ<br>ሲ | ኢሊጋ<br>ኢቫንጂኪ<br>የሰርቢያዊት<br>ዓለም አቀፍ<br>ተሸላሚ<br>ስዕሎች | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 12-20/3/10 |
| 27 | ወዲያና ወዲህ የስዕል ኤግዚቢሽን | | ሐይሉ በዛብህ | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 24/3/10-6/4/10 |
| 28 | የስዕል ኤግዚቢሽን | | በፓሪስ ፍሪ<br>የሆነው<br>ሚካኤል ቤተ<br>ስላሴና የአስኒ<br>ጋለሪ ባለቤት<br>ቆንጂት | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 13-26/4/10<br><br>ሚካኤል<br>በ1993፤2006 ና<br>2007<br>ቆንጂት በ2005 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ስዩም | | እቅርበዋል |
| ጧትንና የተፈጥሮ ወቅትን የሚያንጸባርቁ ስዕሎች | | ዮሴፍ ሉሌ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 7/5/10-19/5/10 |
| ህይወትና ግድግዳ | | እንዳለ ደሳለኝ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 23/5/10-3/6/10 |
| መለከት የመጀመሪያውን የስዕል ኤግዚቢሽን በምልክቶች ዙሪያ | | ማትያስ ሉሉ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 9/6/10-22/6/10 |
| ፊት ለፊት | | ቴዎድሮስ ሐጎስ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 10/11/10-22/11/10 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | ያዕቆብ በቀለ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 25/11/10-3/12/10 |
| የህጻናት ርዕይ ዙሪያ የተሰራ ኤግዚቢሽን | | አለማየሁ ረጋሳ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 7-17/9/11 |
| የቀቢው ማስታወሻ | | መዝገቡ ገረመው | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 24/9/10-7/10/10 |
| ሁለትና ሶስት ዳይመንሽናል ሚዲያ አርት | | አክሊሉ ተመስገን | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 12/10/10-25/10/10 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | መርዕድ ታፈሠ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 8/3/11-31/3/11 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | አንዳርጌ አስፋው | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 23/3/11-31/3/11 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | ዡቬየር ቬርሆስት | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 8-16/4/11 |
| ነጻ የስዕል መንደር፤ውብ አካባቢ በቡድን የቀረበ | | ሔኖክ ጌታቸው፤ምህረት ከበደ፤ሄለን ዘሩ፤ሙሉጌታ ካሳ፤ታምራት ገዛህኝ፤ዳንኤል አለማየሁ፤አምበርብር ሽፈራው፤ሮቤል ተመስገን፤ጎሳ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 204/11-4/5/11/ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ኦዳ፤ አክሊሉ ተመስገን፤ ተስፋሁን ክብሩ፤ ሰለሞን ጸጋዬ፤ ለይኩን ናሁሰናይ፤ ዳዊት ዓለሙ፤ ሲሳ ወ/ጊዮርጊስ፤ ፍሬዘር አድማሱ፤ ሂሩት ግዛው | | |
| የስነ ሰብዕ ዘመናዊ የስዕል ኤግዚቢሽን | | ኤሊያስ ስሜ መስከረም አሰግድ | አሊያንስ፤ ጎተ፤ ጣሊያን ባህል ማዕከል፤ ብሪቲሽ ካውንስል | |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | ወርቅነህ በዙ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 15/2/11-28/2/11 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | በቸርነት ዓለም | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 4/5/11 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | ጌታቸው ብርሃኑ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 18/5/11-25/5/11 |
| የስዕል ኤግዚቢሽን | | በሃይሉ በዛብህ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 3/5/11-8/5/11 |

## ሙዚቃ

| ቁ | የኪነ ጥበባዊ ዝግጅቱ ርዕሰ ጉዳይ | አዘጋጅ | አቅራቢ | የተካሄደበት ቦታ | የተካሄደበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| | የአዝማሪ ምሽት | | ገነት ማስረሻና ባንዷ | አሊያንስ | ህዳር,24፣ 2005 |
| | የአዝማሪ ምሽት | | አበባው አንዳርጌና የእርሱ ቡድን | | ታህሳስ 2005 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የሙዚቃ ኮንሰርት | ኢዳን ሪቼ የሙዚቃ ፕሮጀክት በአማርኛና ኢብራይስጥኛ | ከእስራኤል የመጣ የሙዚቃ ዝግጅት | አሊያንስ ከዕስራኤል ኢምባሲ ጋር | ጥር 11,2006 |
| የኢትዮጵያን ሙዚቃ እንወቅ | የኢትዮጵያን ሙዚቃ የማሳወቅ ስልጠና ለአንድ ቀን ይካሄዳል | በገና ደርዳሪዋ ሶስና ገ/የሱስ፣እንዳልካቸው የኔሁን ባለማሲንቆ፣ምትኩ ከበደ ባለ ከበሮ፣አይችሉህም መንግስቱ በዋሽንት | አሊያንስ ኢትዩ | ጥር 11,2006 |
| አምስቱ አንጋፋ ዘመናዊ ሙዚቀኞች | ግርማ ነጋሽ፣ባህታ ገ/ህይወት፣ማህሙድ አህመድ፣ጌታቸው መኩሪያ እና መኮንን በቀለ ከአፍሮ ሳውንድ ጋር | | ሂልተን ሆቴል | ጥር 13,2006 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አራቱ ሴት ድምጻውያን | ትግስት አፈወርቅ፤ዝናሽ ጸጋዬ፤ዙሪያሽ አብዩ፤እንደልቤ ማንደፍሮ | | አሊያንስ | ጥር 17,2006 |
| ታይግሪ ዴስ (ግንደ ቆርቁር)ፕላንትኔስ/ ከፈረንሳይ/የመጣ ባንድ ከኢትዮጵያውያን ጋር | | | ኮፊ ሐውስ እና አሊያንስ | ጥር 20,21,2006 |
| የጃዝ ኮንሰርት | | ካለ ባንድ መሪ | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | ታህሳስ 15,2005 |
| የአዝማሪ ምሽት | አክሱማይት የባህል ቡድን፤አምሳሉ ምትኬ እና ቡድኗ | | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | ጥር 12,2006 |
| ሙዚቃና ጃዝና ስነጽሁፍ | የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር | ዶ/ፈቃደ አዘዘ፤አበባው መላኩ፤ ምስራቅ ተረፈ፤ፍሬዘር ዘለቀ | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 2/12/09 |
| የሙዚቃ ኮንርት | | ፈረንሳዊ ቴነር | አሊያንስ ኢትዮ | 24/11/07 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ሳክስፎኒስት ሶፊ አሎር | ፍራንሲስ | |
| ጃዝ ሙዚቃ | | በዋን ባንድ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 12/01/08 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | | የዞንግ ኮንሰርት ልዩ የፈረንሳይ ሙዚቃ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 23/02/08 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | | ቴክ የተባለ የካሜሮን የከበሮ ሙዚቃ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 27/3/09 |
| የክላሲካል ፒያኖ | | ፈረንሳዊቷ ካቶር ዛጅማንኮ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 27/3/09 |
| የአዝማሪ ምሽት | | አባይ ባህል ባንድ አስራት ቦሰና እና ጋሻው መስፍን ማሲንቆ፤ ሰላምነሺ አየለ ዘፋኝ ፤ቡድኑ በኬንያ ተጋብዞ ዝግጅቱን አቀርቧል፡፡ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 9/4/09 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት የጃዝ ሙዚቃ | | ሳቫርድ ላኦ የተባሉ የፈረንሳይ የጃዝ ሙዚቀኞች | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 7/5/09 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ስምንተኛው የኢትዮጵያ ሙዚቃ ፌስቲቫል | ጌታቸው ደባልቄ እና ሚስተር ፍራንሲስ ፋልሲቶ | ስለሺ ደምሴ፤የደራሼና ወላይታ ዘፋኞች፤የሃ ባንድ ና ፊሊፕ ሐርፒን፤ውዳሴ ባንድ፤ የቀድሞ ኦርኬስትራ ፤ደቦ ባንድ፤ኮራል ዱ ኤጁ ኤም፤ተፈሪ ባንድና እንግዶቹ፤ዘሪቱ፤ልዩ የጎንደር አዝማሪ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 15-26/5/09 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | | ከፈረንሳይና ከኢትዮጵያ የተውጣጡ ሙዚቀኞች | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 20/6/09 |
| ሙዚቃ ከኦሞ ሸለቆ ጥናት | የፈረንሳይ የጥናት ማዕከል | ፈረንሳዊው ባስቲን ላጋታ ከ2003 እስከ 2006 ያጠናውን የኦሞ ሸለቆ ሙዚቃ መሳሪያዎች አቅርቧል | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 25/10/09 |
| መለከት ጃዝ | | ጊታሪስቱ ግሩም ግዛው፤ኪቦርድ አብይ ወ/ሃና እና ዮናስ ጎርፌ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 2/10/09 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዲስኮ ዘፈን ከዳንስ ጋር | | የስፔንና ላቲኖ ዳንስ በፈረንሳይ የ1960ዎቹ ሙዚቃ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 3/10/09 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | | ፈረናሳዊው አኮርዲዮን ተጫዋች ጂን ጃኪዮስ፤ጆርጅ ብራንስ ና ጆልፋብሩ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 9/10/09 |
| የጃዝ ብሉስ ሙዚቃ | | ባስቶንና ባቡሽካ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 23/10/09 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | የስፔን ኢምባሲ ከአሊያንስ ጋር በመተባበር ቺሊ ኮን ካርኔ ኮንሰርትአዘጋጀ | በ1960ዎቹ ና በ1970ዎቹ ፈንክ ኢንች ፤ኢድሪስ መሐመድና ፓኪዮቶዲ ሪቪራ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 7/11/09 |
| የአዝማሪ ምሽት | | ናትናኤልና ጓደኞቹ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 17/12/09 |
| የገና ኮንሰርት | | ዘሪቱ ከበደ ከመሃሪ ብራዘርስ ጋር | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 5/1/10 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | | ሜክሲኳዊው ሙዚቀኛ ሊጂ ሊኦና ጓደኞቹ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 15/01/10 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | | ከፈረንሳይ የመጣ ባንድ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 22/01/10 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሙዚቃ ታቲ አፒክ ባንድ | | ግሩም መዝሙር ኢንስፓየር የሆነበትን ከፊልም ጋር ተቀናብሮ የቀረበ | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 6/2/10<br>-8-12/2/10 |
| የአዝማሪ ምሽት | | እቴነሽ ዋሴና ባንዷ መሰለ አስማማው፤እንደሻው ቻልዬ፤አስራት አያሌው፤ይስሃቅ ሞገስ፤መሳይ አበባዬና ፍቅርተ ተካ | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 5/3/10 |
| 9ኛው የኢትዮጵያ ሙዚቃ ፌስቲቫል | ጌታቸው ደባልቄና ሚስተርፍራንሲስ ፋልሲቶ | አሊያንስ፤ብሔራዊ ቲያትር፤ጎተ ኢንስቲትዩትና ክለብ አሊዜ በጋራ አዘጋጁት<br>ዩካን ዳንዝ ከፈረንሳይ የመጣ ባንድ ፤ጋሞ ሙዚቀኞች ኑብያን አርክ፤ማጋ ቦ ከብራዚል፤አፍሪካን ጃዝ ስኩል፤አርባ ምንጭ ፌስቲቫል | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 12-20/3/10 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሲኒማና ሙዚቃ | | አንድሪያ ሳቯጅ ፊልም እያሳዬ አንቲፓፐ አካ ቴሌፓፐ፤ሶሎሞን ታካሻ እና ስቲፍ ሙዚቃ አቅርበዋል | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 31/03/10 |
| ቴክ ሙዚቃ | | ቲክ፤ሳዛቦ እና ጃዝማሪያስ(ከካሜሮ ን፤ፈረንሳይ እና ኢትዮጵያ ተውጣጡ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 9/4/10 |
| ዘሾፒንግስ ሙዚቃ | | ዘሾፒንግስ ከፈረንሳይ የመጣ በኢትዮጵያ አቅርቦ በሌሎች አፍሪካ አገሮች ይዞራል | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 16/4/10 |
| የፒያኖ ሙዚቃ | | ክርስቲያን ቻርያሮን | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 21/4/10 |
| ሙዚቃ | | ራስክዋንተሰብ ከአስኮቲክስ ባንድ ጋር | በካፌ ዴ ላጋሬ | 2/6/10 |
| መዚቃ/የኢትዮጵያ ሳምንት በፓሪስ | | አስናቀ ገ/የስና ዩካን ዳንዝ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 9/6/10 |
| ሙዚቃ ኮንሰርት | | ባስቶንና ባቡስካ ከፈረንሳይ የመጣ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 19/6/10 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ባንድ በፈረንሳይና አማርኛ | | |
| | የሙዚቃ ኮንሰርት | | ክርስቲያን ቻርያፎን የፒያኖ ሙዚቃ | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 3/12/10 |
| | የሙዚቃ ኮንሰርት | | አካሌ ውቤ ባንድ ከፈረንሳይ በመምጣት የ1960ዎቹናየ1970 ዎቹ | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 4/12/10 |
| | የሙዚቃ ናዝር ኢቫንዲይና ሱፐርኖቫ | የአሜሪካ ኢምባሲ ከአሊያንስ ጋር በመተባበር አዘጋጅ | ናዝር ኢባ ዲይና ሱፐርኖባ ከዋሽንግተን ዲሲ የጃዝ ኢለመንቶች፣በፖፕ አፍሮ ኩባ፣አፍሮ ብራዚልንና ሌሎችንም አቅርበዋል። | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 15/12/10 |
| 4 | የአዝማሪ ምሽት | | አዳነ ተካ | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 17/9/10 |
| 5 | የሙዚቃ ኮንሰርት | | አሊያ ኪታ በላፎን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያው የአፍሪካ ሞረምባና ዛይሎሮን ቅልቅል ነው። የምዕራብ አፍሪካ | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 18/3/11 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዘፈንን ከጃዝ እና<br>መሳሪያ ጋር<br>አዋህዶ ያቀርባል | | |
| | | ራስ<br>ኩንታሰብ፤ቴዲዳን | አሊያንስ<br>ኢትዩ | 18/3/11 |
| የመጀመሪያው<br>የታሪክ፤የባህልና<br>ሙዚቃ ፌስቲቫል<br>በኢትዮጵያ | | ቦብሂ ኤፍ ኤም<br>፤ኪንግ ኮንግ፤ራስ<br>ዮሃንስ፤ ሀይሌ<br>ሩት፤ ሄሪ ታከል<br>ስቴንስ፤ቀኒ<br>ዓለም፤ አፍሪካ<br>ዳንስ፤ዜላ አፍሪካ<br>ጋይል | ፍራንሲስ | |
| የሙዚቃ ኢንጂነር<br>24ቱ ድምጾች | | ጂሮንቪዘር አዲስ<br>አበባና ሲጎበኝ<br>ከመርካቶ ብረት<br>ተራ እስከ ካዛንቺስ<br>አዝማሪ ቤት<br>ያየውን በ24<br>ድምጾች አቅርቧል | በጎተ<br>በአሊያንስ | 24/3/11<br>28/3/11 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | | ካሜሩናዊ ጃኩስ<br>ግሪግ ቤሌቦ<br>ቅንብሩን አቅርቧል | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 1/4/11 |
| | | ዩካንዳንዝ<br>ከፈረንሳይ፤አስናቀ<br>ገ/የሱስከኢትዮጵያእ | አሊያንስ<br>ኢትዩ<br>ፍራንሲስ | 4/1/11 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የሙዚቃ ኮንሰርት | | ትሪኦ ከስዊስ እና ጂጂ ሚታሚታ | | |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | | ራስኩንታሰብ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 28/1/11<br>4/2/11 |
| የአዝማሪ ምሽት | | ብርቱካንና ኢየሩሳሌም የበሃል ምሽት | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 18/2/11 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት ሳምንት<br>የኪቮክ ቫልዲያን የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ፈጣሪ | | የተለያዩ ኦርኬስትራና ባንድ ከከተማው አስተዳደር፤ፖሊስ፤ ያሬድ ሙዚቃ ት/ቤትና ናዝሬት ት/ቤት ባንድ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 20/2/11 |

ስነ ጽሁፍ

| ተ.ቁ | የኪነ ጥበባዊ ዝግጅቱ ርዕስ ጉዳይ | አዘጋጅ | አቅራቢ | የተካሄደበት ቦታ | የተካሄደበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሳኒ አፍሪካ የፍቅር ደብዳቤ | | ረመዳን ሱሌማን | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 7/6 /2006 |
| 2 | የአንድ ሰ ዓት ግጥም | | ፈረናሳዊያን ገጣሚ ባውዲላሪ እና ፓውሎ ቬራኒ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 10/1/08 14/02/08 |
| 3 | የአንድ ሰዓት ግጥም | | የፈረንሳዊ የሴንት ጆን ፐርስ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 16/4/09 |
| 4 | የህጻናት ስነ ጽሁፍ (6 ታሪክ ያሉትና በአማርኛና እንግሊዘኛ የተዘጋጀ መጽሀፍ)አልነጋም፤እማግልገሌና ጥቁር ፍየሌ ተነበዋል | የኢትዮጵያ ህጻናት ደራሲያን ማህበር ያዘጋጀው | | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 24/5/09 |
| 5 | መጽሀፍ ቅዱስን ወደ ግዕዝ መቼ ተተረጎመ የሚለው ቀርቧል | | ዳንኤል አሰፋ | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 4/6/09 |
| 6 | የጆብ ሉዶልፍ ስለኢትዮጵያ በ1861 የጻፈው ወደ ፈረንሳይኛ ተተርጉሞ ቀርቧል | ጆብ ሉዶልፍ | | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 5/11/09 |
| 7 | የአንድ ሰዓት ግጥም<br>በኔ ሞት የሚለውን የሙሉቀን መለሰ የዘፈን ግጥም<br>እመጣለሁ እያልሽ መቅረቱን ካልተውሽ<br>እኔ ያንቺ አልሆንኩም አንቺም የእኔ አልሆንሽ | ገጣሚ ሸዋ ልዑል መንግስቱ | | አሊያንስ ኢትዩ ፍራንሲስ | 18/11/09 |

## የጀርመን ባህል ማዕከል

### ስዕል

| ተ.ቁ | የቀረበው ኪነ ጥበብ | አቅራቢ | አዘጋጅ | ቦታ | ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የገብረክርስቶስ ደስታ የስዕል ስራዎች | | ዮህንስ ገዳሙ | የጀርመን ባህል ማዕከል | 6/3/06 |
| 2 | የስዕል መድረክ | ማህሌት አብርሃም | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 3-10/11/98 |
| 3 | የ1960ዎቹ ግራፊክ አርት | ከጀርመን የመጣ | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 12-24/11/98 |
| 4 | የስዕል ኤግዚቢሽን | ዘሪሁን የትምጌታ እና ሐንሰን ባሂ | የጀርመን ባህል ማዕከል ከአስኒ ጋለሪ ጋር | የጀርመን ባህል ማዕከል | 4-9/4/99 |
| 5 | ዘመናዊው የኢትዮጵያ ስዕል በተለያዩ ሰዓሊያን አቀራረብ | ዮሐንስ ገዳሙ | የውይይት መድረክ | የጀርመን ባህል ማዕከል | 25/1/2001 |
| 6 | አርትና የኢትዮጵያ ህዝብ | ዮሐንስ ገዳሙ | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 10/5/01 |
| 7 | የስዕል ኤግዚቢሽን | የቢርቶት ብሪቼት | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 2/4/02 |
| 8 | ኢንስታሌሽንና ፐርፎርማንስ አርት | በዮሐንስ ገዳሙ ና ሊዮ | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 18/4/02 |
| 9 | የበርሊን ግንብ የፈረሰበት 20ኛ ዓመት | | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 11/11/09 |
| 10 | ሰላማዊ | የሊፒዚግ | | የጀርመን | 20/11/09 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አብዮት | ስዕሎች | | ባህል ማዕከል | |
| 11 | የስነ ተዋልዶና ኤች አይቪ ኤድስ የቅብ ስዕል | | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 1/12/07 |
| 12 | አርትና ፖለቲካ | በዮሐንስ ገዳሙና በጆ ጃስትራም | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 9/10/08 |
| 13 | የስዕል ኤግዚቢሽን | | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 4-11/4/08 |
| 14 | ፍለጋ ቁጥር 2 የስዕል ኤግዚቢሽን | የእናት ፋንታ ውቤ | 12 ወጣት ሰዓሊያን | የጀርመን ባህል ማዕከል | 12/03-2/4/08 |
| 15 | ነጻ አርት ፍለጋ ሶስተኛ | የእናት ፋንታ ውቤ | 12 ወጣት ሰዓሊያን | የጀርመን ባህል ማዕከል | 9/4/2009 |
| 16 | አርትና አካበቢ ከዚህ ወዴዬት እንሂድ | | | ብሪትሽ ካውንስል | 20/1/11 |
| 17 | ከማስታወስ ወዲያ ስዕል | | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 3/3/11 |
| 18 | የሰውነት ላይ ቅቦች(ንቅሳቶች) | ዮሐንስ ገዳሙ | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 20/6/02 |

## ሥነ ጽሑፍ

| የቀረበው የኪነጥበብ ዝግጅት | አዘጋጅ | አቅራቢ | ቦታው | የቀረበበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| የአርት ሂስ በኢትዮጵያና ጀርመን አውደ ጥናት በኢትዮጵያ ከደርግ ውድቀት በኋላ እና በጀርመን ከተዋሃደች በኋላ እንዲሁም ታሪካዊ የአርት ሂስ በሁለቱ አገሮች | ዘሪሁን አስፋው | ዘሪሁን አስፋውና ከጀርመን ስነጽሁፍ ሂስ ክርስቶፍ ብላስ | ጀርመን ባህል ማዕከል | 26-28/10/1998 |
| የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ በመጪው ሚሊኒየም ያለበት ፈተና | ዘሪሁን አስፋው | ደራሲ ጸሐይ መላኩና ሐይለመለኮት መዋዕል፤የአጭር ልቦለድ ጸሐፊ የዝና ወርቁ ና ሳሙኤል ልጅዓለም | ጀርመን ባህል ማዕከል | 16/4/1999 |
| የጎተ ግጥሞች ትርጉም አውደ ጥናት | ዘሪሁን አስፋው | 10 ምርጥ ግጥሞች ከሚስተር ሚሃኤል ሂውልስ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ | ጀርመን ባህል ማዕከል | 10-14/5/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የትርጉም አውደ ጥናት | | |
| ከ19ኛው እስከ 20ኛው ክ/ዘመን የዝነኛ የጀርመን ገጣሚዎችን የትርጉም ስራ አውደ ጥናት | ዘሪሁን አስፋው<br>ከሚሃኤል ሂውልስ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ | ዘሪሁን አስፋው፣ ብርሃኑ ገበየሁ፣አስፋ ወርቁ፣ ፋንታሁን እንግዳ፣ፍ/ማርቆስ ደስታ፤ተስፋዬ ገሰሰ፤ወ/ሮ ሙሉ እመቤት ዘነበ፣ ማንያዘዋል እንደሻው እና ነብዩ መኮንን | ጀርመን ባህል ማዕከል | 10-12/5/2000 |
| የጀርመን ግጥሞች ምንባብ | የጆሴፍ ቮን ኢችንዶርፍ፤ሄነሪ ክ ሄን፤ሬይነር ማርያ ሪሌክ፤ገንተር ግራስ እና ሃንስ ማግነስ እንዘስንበርግር | በነብዩ መኮንን | ጀርመን ባህል ማዕከል | 25/5/2000 |
| የግጥም ንባብ | እሌኒ መኩሪያ | ፊርማዬ አለሙ በአማርኛና ሳራ ክሪሽ በእንግሊዘኛ ተርጉማ አቅርባለች | ጀርመን ባህል ማዕከል | 26/7/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የህጻናት መጻህፍት በኢትዮጵያ (እንዴት የህጻናት መጻህፍት እንደሚጻፉ፤የገጸ ባህርያት አሳሳል፤ የድራማ አወቃቀር፤ትረካዊ፤ድ ምጾት የመሳሰሉት ላይ ስልጠና አዘጋጅተዋል) | | ሪናተ አህረንስ ክራመር | ጀርመን ባህል ማዕከል | 7/12/2000 |
| ግጥም | | የብሩክ ገ/መድህንና ደርስ ገሬንቢን የተባለ ወጣት ጀርመናዊ ዘመናዊ ግጥሞች | ጀርመን ባህል ማዕከል | 21/12/01 |
| የጀርመን አጭር ልቦለድ አጻጻፍ | | በጀርመናዊ ደራሲና ኤዲተር ሚካኤል ሃልስ | ጀርመን ባህል ማዕከል | 9/5/01 |
| በታወቂው ጀርመናዊ የአጭር ልቦለድ ደራሲ የፍራንዝ ካፍካ አጻጻፍ ላይ ያተኮረ የትርጉም ስልጠና | ሚካኤል ሂውልስ | ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ጋር በመተባበር | ጀርመን ባህል ማዕከል | 28/5/01-1/6/01 |
| የኩኩሉ መጻህፍ | የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር | የኢትዮጵያን ህጻናት ደራሲዎች | ጀርመን ባህል | 23/4/02 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ምረቃ | | | ማዕከል | |
| 2 | የልቦለድ ስነጽሁፍ ከጀርመን ስልጠና | ሚሃኤል ሂውልስ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 21-24/5/02 |
| 3 | የጀርመን ልቦለድ ንባብ | ሚሃኤል ሂውልስ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 22/5/02 |
| 4 | የግጥም ንባብ ጊዜ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | ዶ/ር ዮናስ አድማሱ የራሳቸውን ግጥም አቅርበዋል | ጀርመን ባህል ማዕከል | 28/1/2003 |
| 5 | የተመረጡ የገጣሚና ጸሐፊ ተውኔት ደበበ ሰይፉ ግጥሞችና የህይወት ታሪኩ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 20/3/2003 |
| 6 | የተመረጡ የሰይፉ መታፈሪያ ግጥሞችና ሥራዎቹ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 15/10/03 |
| 7 | የተመረጡ የ ገ/ክርስቶስ ደስታ ግጥሞቹና ሥራዎቹ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 23/12/03 |
| 8 | የገ/ክርስቶስ ደስታ ግጥሞች በልዩ የህዝብ ጥያቄ የተዘጋጀ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 23/12/03 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መድረክ | | | | |
| 9 | የወጣቶች ድምጽ ክፍል አንድ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | ሶስት ወጣት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ያልታተሙ ግጥሞች | ጀርመን ባህል ማዕከል | 26/2/04 |
| 0 | የወጣቶች ድምጽ ክፍል ሁለት የግጥም ንባብ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | ሶስት ወጣት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ያልታተሙ ግጥሞች | ጀርመን ባህል ማዕከል | 27/3/04 |
| 1 | ወጣት ተራኪዎች ክፍል አንድ በአጭር ልቦለድ ንባብ ጊዜ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | ዶ/ር ዮናስ አድማሱ በፈጠራ አጻጻፍ ዙሪያ አውደ ጥናት ካቀረቡ በኋላ የአራት ደራሲዎችን ስራ አቅርበዋል | ጀርመን ባህል ማዕከል | 29/5/04 |
| 22 | ወጣት ተራኪዎች ክፍል ሁለት በአጭር ልቦለድ ንባብ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | ዶ/ር ዮናስ አድማሱ በፈጠራ አጻጻፍ ዙሪያ አውደ ጥናት የአራት ደራሲዎችን ስራ በማቀረብ ውይይት | ጀርመን ባህል ማዕከል | 30/9/04 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ተደርጓል | | |
| 3 | የሁለት ዘመን ትውልድ ግጥምና ገጣሚ በቤተሰብ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | አቶ ባዬ ንጋቱና ልጃቸው ነብዬ ባዬ | ጀርመን ባህል ማዕከል | 23/12/04 |
| 4 | የአማርኛና አረብኛ ጽሑፍ ተውውቅ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | በሞሀመድ ሰይድ፣ዶ/ር አወል እድሪስ እና ሞሀመድ አወል | ጀርመን ባህል ማዕከል | 22/3/2005 |
| 5 | የራስን ዘመን በግጥም መድለጽ | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ | ጌትነት እንየው፣በእውቀቱ ስዩም ፣እንዳለ ጌታ ከበደ የተመረጡ ግጥሞቻቸው | ጀርመን ባህል ማዕከል | 26/5/2005 |
| 26 | የጀርመን አጭር ልቦለድ በአማርኛ | | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 10/11/07 |
| 27 | የአስተዋዪ ባልና ሚስት ንባብ | | በአርተር ሽንት ዝለር | ጀርመን ባህል ማዕከል | 11/11/07 |
| 28 | ከህግ በፊትና ሌሎች | | በፍራንዛ ካፍካ | ጀርመን ባህል ማዕከል | 7/7/2007 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | ያለፌት ዘመናት ዳቦዎች | | በሄነሪክ ቦል | ጀርመን ባህል ማዕከል | 6/12/08 |
| 0 | ቀይዋ ድመት | | በሊስ ሬንሰር | ጀርመን ባህል ማዕከል | 20/9/08 |
| 1 | የራሺያን ዲስኮ ንባብና ውይይት | | ውላድ ከሚነር | ጀርመን ባህል ማዕከል | 19/12/09 |
| 2 | የአንድ ቀን ሰው ንባብና ውይይት | | ሜሪሊዮስ ካቼንቲዝ | ጀርመን ባህል ማዕከል | 28/11/09 |
| 3 | መርሳት ንባብ | | ማርጋሬት ሃን | ጀርመን ባህል ማዕከል | 26/9/09 |
| 4 | ጠረጴዛ ጠረጴዛ ነው ንባብ | | ፒተር ቢሼል | ጀርመን ባህል ማዕከል | 8/8/09 |
| 5 | የአንዶራው አይሁድ ንባብ | | ጉንተር ግራስ | ጀርመን ባህል ማዕከል | 27/5/09 |
| 6 | የሮሜ ንባብ | | ማክስ ቮን ደርግሩን | ጀርመን ባህል ማዕከል | 7/2/09 |
| 7 | አዲስ አበባ ታንብብ | ዳንኤል ወርቁና ዮናስ ታረቀኝ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 2-6/1/09 |
| 8 | የጀርመን ተረት | | ወደ ት/ቤት ሄደ ክፍል አንድ | ጀርመን ባህል ማዕከል | 4/11/2010 |
| 9 | አዲስ አበባ ታንብብ አዳማ፤አዋሳ፤ድሬድዋና | ዳንኤል ወርቁና ዮናስ ታረቀኝ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 25-29/2/2010 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቀሌ | | | | |
| | የጀርመን ተረት ወደ ት/ቤት ሄደ ክፍል ሁለት | | የተመረጡ የአዲስ አበባ ት/ቤቶች | ጀርመን ባህል ማዕከል | 15-19/2/2010 |
| 1 | የጀርመን ስነጽሁፍ በአማርኛ | ጎተ ኢንስቲትዩትና ሚዩዚክ ሜይዴይ | | ብሄራዊ ቲያትር | 19/4/10 |
| 2 | ጸሐይ መማር ትወዳለች | ዶ/ር ልጅ አስፋ ወሰን አስራት | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 4/12/09 |
| 3 | ሄነሪክ በሥነ ጽሁፍ ስራዎቹ | | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 7/5/02 |
| 4 | የጀርመን ቴያትርና ስነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ቲያትርና ስነ ጽሑፍ ላይ ያመጣው ለውጥ | ተስፋዬ ገሰሰ እና ዘሪሁን አስፋው | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 15/6/02 |

ሙዚቃ

| ተ.ቁ | የቀረበው የኪነጥበብ ዝግጅት | አዘጋጅ | አቅራቢ | የቀረበበት ቦታ | የቀረበበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሙዚቃ ኮንሰርት | ሃይሉና ጓደኞቹ | ሃይሉና ጓደኞቹ | ጀርመን ባህል ማዕከል | 28/3/06 |
| 2 | የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መዝሙር(ሙዚቃ) | ፕሮፌሰር ወልፍጋንግ ቤንደር ኮሜንዝ ዩኒቨርስቲ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 9/3/06 |
| 3 | ክላሲካል ጊታር | ሚካኤል ላወር | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 9/3/06 |
| 4 | የሙዚቃ ኮንሰርት | ኩውንትት ቻንትሊያ | ከጀርመን የመጣ የሙዚቃ ቡድን | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የባህል አዳራሽ | 14/09/07 |
| 5 | ሙዚቃ በአውሮፓ ቀን | ሚካኤል ላውርና ሊቼ | | ጀርመን ባህል ማዕከል | 9/5/07 |
| 6 | የሙዚቃ ኮንሰርት | ሲሲሊ ቨርኒይ ኳርትት | | ሲራናዶ | 3/12/09 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ሬስቶራንት | |
| 7 | በጀርመን-ቱርክ ሙዚቃ ዙሪያ አውደ ጥናት | | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 12/12/09 |
| 8 | የሙዚቃ ኮንሰርት | | የጀርመን ባህል ማእከል | የጅቡቲ ኢንስቲትዩት | 1/12/09 |
| 9 | የሙዚቃ ኮንሰርት | አካሌ ውቤ ባንድ ከፈረንሳይ | | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ድሬደዋ | 29/11/2010 |
| 10 | ጃዝ ትሪዮሎጂ | | | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ድሬደዋ | 27/11/2010 |
| 11 | ኢትዮጵያን ሬጌ | | | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ድሬደዋ | 26/11/2010 |
| 12 | የሙዚቃ ኮንሰርት | አካሌ ውቤ ከፈረንሳይ | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 26/11/2010 |
| 13 | ባግዳድ ፋንታሲ | ከፈረንሳይ የመጣ | | አሊያንስ ኢትዮ | 25/11/2010 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሾው | ባንድ | | ፍራንሲስ | |
| 14 | የሙዚቃ ኮንሰርት | | | ዞማ ኮንቲምፖራሪ አርት ማእከል | 25/11/2010 |
| 15 | ሑዋትስ አውት ሙዚቃ 2010 | | | አዲስ አበባና ድሬደዋ አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 23-29/11/10 |
| 16 | የሙዚቃ ሲዲ ምረቃ(የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅጂ) | አዝማሪ ተሰማ እሸቴ | | በጀርመን ባህል ማዕከል | 20/9/10 |
| 17 | የሙዚቃ ኪንሰርት | ቲክ፧ሲዛቦና ጃዝማሪስ | | የጀርመን ባህል ማእከል | 15/4/10 |
| 18 | የሙዚቃ ኮንሰርት | ጃዝማሪስ | | የጀርመን ባህል ማእከል | 22/1/2010 |
| 19 | የሙዚቃ ዝግጅት | ዴር ሮት በርጅች | | የጀርመን ባህል ማእከል | 29/3/11 |
| 20 | የሙዚቃ ዝግጅት | ዴር ሮት | | ትሮፒካል | 27/3/11 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በርጆች | | ጋርደን | |
| 21 | የሙዚቃ ዝግጅት | ቱ ኤንድ ቲወልቭ ሳውንድ | | አሊያንስ ጀርመን ባህል ማዕከል | 24/3/11 |
| 22 | የሙዚቃ ዝግጅት | ቮሊቫያ ሴሽን | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 18/3/11 |

## የጣሊያን ባህል ማዕከል

ስዕል

| ተ.ቁ | የቀረበው የኪነጥበብ ዝግጅት | አዘጋጅ | አቅራቢ | የቀረበበት ቦታ | የቀረበበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የስዕል ኤግዚቢሽን | አበበ ዘለለው | | የጣሊያን ባህል ማዕከል | 20-28/2/06 |
| 2 | የስዕል ኤግዚቢሽን | | | የጣሊያን ባህል ማዕከል | 21-30/3/06 |
| 3 | የስዕል ኤግዚቢሽን ዘመናዊው የኢጣሊያ ስዕል ውይይት | ፕሮፌሰር አልቤርቶ ቴሴሮ | | የጣሊያን ባህል ማዕከል | 3/10/17/20/24/27/2/11-3/8/3/2011 |
| 4 | የስዕል ኤግዚቢሽን | ሰይፉ አበበ | | የጣሊያን ባህል ማዕከል | 25-5/5/06 |

ስነ ጽሑፍ

| ተ.ቁ | የቀረበው የኪነጥበብ ዝግጅት | አዘጋጅ | አቅራቢ | የቀረበበት ቦታ | የቀረበበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፊሎሚና ማርቱራና መጽሐፍ ወደ አማርኛ የተተረጎመ | | | ጣሊያን ባህል ማዕከል | 13/3/10 |

## ሙዚቃ

| ተ.ቁ | የኪነጥበብ ዝግጅቱ | አቅራቢ | አዘጋጁ | ዝግጅቱ የተካሄደበት ቦታ | ዝግጅቱ የተካሄደበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ክላሲካል ሙዚቃ | አይ ሶልቲሽ ቬንቲ ክላውዲ ሲሞኒ ከ15 ሙዚቀኞች ጋር | | አዲስ አበባ ሂልተን | 10/12/2004 |
| 2 | ፒያኖና ጃዝ ኮንሰርት | የጀርመን ሙዚቀኞች | | አዲስ አበባ ሂልተን | 13/12/04 |
| 3 | የፒያኖ ሙዚቃ ኮንሰርት | ማርኮ ሶሊኒ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ጣሊያን ባህል ማዕከል | 16/2/06-17/2/06 |
| 4 | የፒያኖ ሙዚቃ | ጆቫኒ | | ጣሊያን ባህል | 24/3/06 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቬሉቴ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ማዕከል | |
| የቫዩሊን ሙዚቃ | ሩዶልፎ ቦንቼ ከራዶ ግሪኮ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ጣሊያን ባህል ማዕከል | 26/3/06 |
| መስኮቶችን መቋቋም ሙዚቃ ኮንሰርት | ፍሪዛን ኦዜፐ ቴክ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ጣሊያን ባህል ማዕከል | 16/3/06 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት | ፍላውቶ ፓውሎ ዳልሞሮ እና ፒያኖ ማውሪዞ ፍርኔሮ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ጣሊያን ባህል ማዕከል | 18/4/2007 |
| መስኮቶችን መቋቋም ሙዚቃ ኮንሰርት | ፍሪዛን ኦዜፐ ቴክ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ጣሊያን ባህል ማዕከል | 16/3/06 |
| መስኮቶችን መቋቋም ሙዚቃ ኮንሰርት | ፍሪዛን ኦዜፐ ቴክ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ጣሊያን ባህል ማዕከል | 16/3/06 |
| መስኮቶችን መቋቋም ሙዚቃ ኮንሰርት | ፍሪዛን ኦዜፐ ቴክ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ጣሊያን ባህል ማዕከል | 16/3/06 |
| የሙዚቃ ኮንሰርት የጣሊያንን ብሄራዊ ቀን ምክንያት በማድረግ | ኢንሪካ ማሪ እና ቻይራ ሚግላሪ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ብሔራዊ ቲያትር | 3/6/09 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሙዚቃ የጣሊያንን ብሄራዊ ቀን ምክንያት በማድረግ | ሙሼ አንቶኒዮ ቪቫልዲ እና ቶማሶ አልቢኖኒ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | ጣሊያን ባህል ማዕከል | 7/9/10 |
| የቤት ሆቨን 250 ኛ ዓመት ልደት የሙዚቃ ኮንሰርት | ጀርመናዊ ው ኢጎር ሌቪት | የጣሊያን ባህል ማዕከል፤አሊያንስ እና ጀርመን ባህል ማዕከል ከ8 የአውሮፓ አገሮች ጋር በመተባበር | ያሬድ ሙዚቃ | 4/10/10 |
| የቤት ሆቨን 250 ኛ ዓመት ልደት የሙዚቃ ኮንሰርት | ግርማ ይፍራ ሸዋ | የጣሊያን ባህል ማዕከል፤አሊያንስ እና ጀርመን ባህል ማዕከል ከ8 የአውሮፓ አገሮች ጋር በመተባበር | ራሺያ ኢምባሲ | 11/10/10 |
| የቤት ሆቨን 250 ኛ ዓመት ልደት የሙዚቃ ኮንሰርት | ፖላንዳዊ ፒዮተር ፓንሲክ | የጣሊያን ባህል ማዕከል፤አሊያንስ እና ጀርመን ባህል ማዕከል ከ8 የአውሮፓ አገሮች ጋር በመተባበር | ያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት | 18/10/10 |
| | ዋይ ኤስ ኤም የክር ሙዚቃ | የጣሊያን ባህል ማዕከል፤አሊያንስ እና ጀርመን ባህል | ያሬድ ሙዚቃ | 15/11/10 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ...ቤት ሆሸን 250 ኛ ...መት ልደት የሙዚቃ ...ንሰርት | ተጫዋቾች እና እዝራ አባተ | ማዕከል ከ8 የአውሮፓ አገሮች ጋር በመተባበር | ት/ቤት | |
| ...ቤት ሆሸን 250 ኛ ...መት ልደት ...ሙዚቃ ኮንሰርት | የአማተሮ ች ምሽት | የጣሊያን ባህል ማዕከል፣አሊያንስ እና ጀርመን ባህል ማዕከል ከ8 የአውሮፓ አገሮች ጋር በመተባበር | ያሬድ ሙዚቃ ቤት | 22/11/10 |
| ...ቤት ሆሸን 250 ኛ ...መት ልደት ...ሙዚቃ ኮንሰርት | ኢጣሊያዊ ካርሎ ሚቺኒ | የጣሊያን ባህል ማዕከል፣አሊያንስ እና ጀርመን ባህል ማዕከል ከ8 የአውሮፓ አገሮች ጋር በመተባበር | የጣሊያን ባህል ማዕከል | 23/11/10 |
| ...ቤት ሆሸን 250 ኛ ...መት ልደት ...ሙዚቃ ኮንሰርት | ፈረንሳዊት ክርስቲን ቻርይሮን | የጣሊያን ባህል ማዕከል፣አሊያንስ እና ጀርመን ባህል ማዕከል ከ8 የአውሮፓ አገሮች ጋር በመተባበር | ያሬድ ሙዚቃ ቤት | 29/11/10 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዝ ኮንሰርት | ካርሎ አክቲስ ዳቶ ኳርቴት | የጣሊያን ኢምባሲና የጣሊያን ባህል ማዕከል | በጣሊያን ባህል ማዕከል እና በጎንደር ሲኒማ ቤት | 2/12/10 እና 4/12/10 |
| ት ሆቨን 250 ኛ ዐት ልደት ዚቃ ኮንሰርት | የስፔን ሙዚቃ | የጣሊያን ባህል ማዕከል፣አሊያንስ እና ጀርመን ባህል ማዕከል ከ8 የአውሮፓ አገሮች ጋር በመተባበር | በያሬድ ሙዚቃ ቤት | 6/12/10 |
| ት ሆቨን 250 ኛ ዐት ልደት ዚቃ ኮንሰርት | ኢስትሪያዊ ጎትሊብ ዋልሽች | የጣሊያን ባህል ማዕከል፣አሊያንስ እና ጀርመን ባህል ማዕከል ከ8 የአውሮፓ አገሮች ጋር በመተባበር | በያሬድ ሙዚቃ ቤት | 13/12/10 |
| ዚቃ ኮንሰርት | ካርሎ ሜየር ፣ጊያንካር ሎ ፣ቢንቼቲ | የጣሊያን ባህል ማዕከል | በጣሊያን ባህል ማዕከል | 9/5/11 |

ሰንጠረዥ 2

በአዲስ አበባ መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ የቴሌቪዥን ፕሮግራም የቀረቡ የባህል ማዕከላት የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች

| የቀረበው የኪነ ጥበብ ዝግጅት | ዝግጅታቸውን ያቀረቡት የኪነጥበብ ባለሙያዎች | የፕሮግራሙ አዘጋጅ | ዝግጅቱ የቀረበበት መድረክ/ቦታ | ፕሮግራሙ የተላለፈበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| ...ኛው የኢትዮጵያ ሙዚቃ ፌስቲቫል | ቻርለስ ባታብ ከአሜሪካ ጌታመሳይ አበበ፤ዮሐንስ አፈውርቅ፤ ጌታቸው መኩሪያ፤ሙኒት መስፍን፤ዘ ኤክስ ባንድ ከሆላንድ እናሌሎችም | ፋንታሁን ኤሬቦ የ20 ደቂቃ ዝግጅት | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 22/09/2000 |
| ...ፕንታዊ ጥበብ አሻራ ...ቤተክርስቲያን ስዕሎች | መዘምር ልሳነ ወርቅ | ፋንታሁን ኤሬቦ የ20 ደቂቃ ዝግጅት | ባሊያን ባህል ማዕከል | 8/9/2000 |
| ...ጻ ጥበብ(ፍሊጋ) ...ተለመደው የአሳሳል ...ጥበብ በማፈንገጥ | የእናት ፋንታ አባተ | | የጀርመን ባህል ማዕከል | 18/11/2001 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተለየ መንገድ በስዕልና ርጻቅርፅ መጠበብ ተማሪዎች አውደ ናትና ስራዎች | | | | |
| ት ነበርን 1950ዎቹና 1960ዎቹ የኢትዮጵያ መናዊ ሙዚቃዎች ይ የተዘጋጀ አውደ ናት | ጥናት አቅራቢ፡ ዳዊት ይፍሩ፤ሰርጸ ፍሬ ስብሃት እና ማህተመ ሐይሌ አወያይ ፡ሰላም ሙሉጌታ | | ጎተ ኢንስቲትዩት | 19/01/01 |
| ብረ ጥበባት የሙዚቃ ዕራፍ ጥበብ | አዱኛ የዳንስና ሙዚቃ ክበብ አባላት | | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 30/08/01 |
| ጥምና ጃዝ በጋራ ነደ ሙዚቃ(ዘፈን) ናበው የቀረበበት | ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ፤አበባው መላኩ፤ምስራቅ ተረፈ፤ምህረት ከበደ | ፋንታሁን ኬሪቦ የ20 ደቂቃ ዝግጅት | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 17/4/01 |
| ነቆቅልሽ | በቀለ መኮንን | ፋንታሁን ኬሪቦ የ20 ደቂቃ ዝግጅት | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 2/7/97 |
| ት ተረት ተረት | ኤሊያስ ስሜ | ፋንታሁን ኬሪቦ | አሊያንስ ኢትዮ | 26/12/98 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የ20 ደቂቃ ዝግጅት | ፍራንሲስ | |
| ክላ ጥበብ | የቀጨኔ ሸክላ ሰሪዎች | ፋንታሁን ኬሬቦ<br>የ20 ደቂቃ ዝግጅት | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 5/2/97 |
| ው የኢትጵያ<br>ዚቃ ፌስቲቫል | ሙዚቃ | ፋንታሁን ኬሬቦ<br>የ20 ደቂቃ ዝግጅት | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 1/7/97 |
| ታዊ ሕይወት | ማርታ መንግስቱ | ፋንታሁን ኬሬቦ<br>የ20 ደቂቃ ዝግጅት | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 28/8/97 |
| 0 ሰዓሊያውያን ስራ<br>ንጋፋና ወጣት<br>ድብል ስዕል | 30 | ፋንታሁን ኬሬቦ<br>የ20 ደቂቃ ዝግጅት | አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ | 17/6/98 |

ገሪ 3

## የተመረጡ ዋና ዋና ቃለ መጠይቆች

ከአቶ እዝራ አባተ ጋር የተካሄደ ቃለ መጠይቅ

ያቂ - በቅድሚያ ስምዎትን፤የትውልድ ዘመንዎንና የት እንደተወለዱ ቢገልጹልኝ ?

ልስ - እዝራ አባተ እባላለሁ።በ1953 ዓ.ም. በጂማ ከተማ ተወለድኩ እድገቴ ግን ዲስ አበባ ነው።

ያቂ - ስለ ባህል ማዕከላቱ(ፈረንሳይ፤ጀርመንና ጣሊያን) ኪነጥበባዊ እንቅስቃሴ መቼ ጀምሮ ነው የሚያውቁት ?

ልስ - በ1972/3 ዓ.ም. አካባቢ ጀምሮ ከተማሪነቴ ጊዜ አንስቶ ይካሄዱ የነበሩ ሙዚቃ ዝግጅቶችን እከታተል ነበር።

ያቂ - በዚያን ወቅት የነበረው የሙዚቃ ዝግጅት ምን ይመስል ነበር ?

ልስ - በወቅቱ አክቲቭ የነበረው የጣሊያን ባህል ማዕከል ነበር። በርካታ የሙዚቃ ግጅቶችን ያቀርብ ነበር።

ያቂ - ከዚያ በኋላስ ያሉት ዝግጅቶች ?

ልስ - ወደ ወጪ አገር ሄጄ ማስተርሴን በሙዚቃ ሰርቼ ስመጣ ሶስቱም የባህል ዕከላት የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ በስፋት ማቅረብ እንደጀመሩ ለማረጋገጥ ቻልኩ።

ያቂ - የሶስቱ የባህል ማዕከላት የሙዚቃ ዝግጅት ምን ይመስል ነበር ?

ልስ - የጣሊያን ባህል ማዕከል ክላሲካል የሆኑ ሙዚቃዎች እና ከአገራቸው ሙዚቀኞችን በማስመጣት የራሳቸውን ሙዚቃ እንድናደምጥ ያደርጉናል።ፈረንሳዮች ግሞ የእነርሱንና የእኛን ሙዚቃ በመቀየጥ ያቀርባሉ። የጀርመኖችን ስትመለከት ግሞ ሙዚቃን አካዳሚያዊ ውይይትና ምርምር ያርጉታል።ሙዚቃና ይንስ፤ሙዚቃና ማህበረሰብ የመሳሰሉ ጉዳዮችን ጥናታዊ ውይይቶችን ያቀርባሉ።

ያቂ - የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ከሶስቱ ማዕከላት ጋር በጋራ ይሰራል ወይ ?

ልስ - በትክክል ! መድረኮችን በሙሉ ተጠቅመንባቸዋል። ወርክሾፕ በሚያዘጋጁበት
ቅት ማዕከላቱ ግቢ ከተዘጋጀ በኋላ ትምህርት ቤታችን ዘንድ መጥተው ወርክሾፕ
ተማሪዎቻችን ይሰጡልናል። ይሄ ደግሞ የእነርሱን የካበተ ልምድ ማካፈላቸው
ጠቅመናል።

ያቁ - አቶ እዝራ ከልብ ጊዜህን ለእኔ ሰጥተህ ለሰጠኸኝ ሙየዠዊ ትንታኔ እጅግ
ው የማመሰግንህ።

ልስ - እኔም በጣም ነው የማመሰግነው ፤መልካም የምረቃ ና የማስተርስ ዲግሪ
ሁፍ ይሁንልህ።

ሮብ 16/10/03 ዓ.ም. ቀን ከጧቱ 5:30 እስከ 6:20 በያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት
ራሱ በዳይሬክተሩ ቢሮ ተካሄደ)

መን ስነ ጽሑፍን ከእኛ ስነ ጽሑፍ ጋር ያለውን ልዩነትና ተቀራራቢነት
በታለህ

ቁ - የባህል ማዕከላት ዘላቂ በሆኑ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ላይ ድጋፍና እገዛ
ፈጉልንም፤የወዲያውና የአሁን ጊዜ እንጂ ዘላቂነት ያለው የምርምር፤የስልጠና
ሳሰሉትን ድጋፎች ከአገራቸው ባለሙያ በማስመጣት ይሁን የእኛኑ ባለሙያዎች
ስልጠን በኩል አልሰሩም የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡በዚህ ላይ በሙዚቃውና በስዕሉ
በ. በተደጋጋሚ ጥያቄዎች ቀርበው መልስ አልተገኘባቸውም፡፡በስነ ጽሑፉም
ሳሳይ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ እዚህ ላይ የአንተ ሃሳብ /አስተያየት/ምንድን
?

ለስ - ያው እንግዲህ የባህል ማዕከላቱ የራሳቸውን ባህል የማስተዋወቅና
ስፋፋት ዓላማና ተግባር ያላቸው ስለሆነ ይሄን መሰል ድጋፍ የሚያደርጉ
መስለኝም፡፡ቢያደርጉ ጥሩ ነበር፡፡ኢምባሲዎች የመሳሰሉት ናቸው ይህንን አያነቱን
ፍ የሚሰጡት፡፡ከዚህ ውጪ እኔ እስከማውቀው ዘላቂ በሆኑ ስራዎች የሚሳተፉ
መስለኝም፡፡ከማዝናናትና ከማስደሰት ባለፈ የባህል ማዕከላቱ አይሰሩም፡፡

ቁ - ውድ ጊዜህን ተሻምቼ ስላስቸገርኩህና ጠቃሚ መረጃዎችን ስለሰጠኸኝ በጣም
የማመሰግነው፡፡

ለስ - ምንም አይደለም ፡፡ ቀደም ብለህም ብትጠይቀኝ ኖሮ ለመስጠት ዝግጁ
ኩ፡፡

ኞ በ20/10/03 ከቀኑ 11፡30 እስከ ምሽቱ 12፡25 በዶ/ር ፈቃደ ቢሮ የተደረገ ቃለ
ልለስ)

ከአቶ በቀለ መኮንን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ቁ - በቅድሚያ ሙሉ ስምዎትን ፤የትና መቼ እንደተወለዱ ቢገልጹልኝ ?

ለስ - በቀለ መኮንን እባላለሁ። ደብረ ዘይት ከተማ በ1956 ዓ.ም.ተወለድኩ። ያው ከተማ ተማርኩ ከዚያም አርት ስኩል ከ1966 እስከ 1971 ዓ.ም በቅርጽ ረኩ። ከዚያም ወደ ሶብየት ሕብረት ሄጄ የማስተርስ ዲግሪዮን በስዕል ሰርቼ ባሁ።

ቁ - በአሁኑ ወቅት በምን ስራና ሃላፊነት ላይ ይገኛሉ ?

ለስ - በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአለ የስነ ጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት ሬክተር ነኝ ።በሙያዬ ሰዓሊና ቀራጺ፤አስተማሪ ነኝ።

ቁ - ገጣሚስ ?

ለስ - መባል ካለበት ያው ስሜቴን እጽፋለሁ።

ቁ - የጀርመን፤ የጣሊያንና ፈረንሳይ ባህል ማዕከላትን ከመቼ ጀምሮ ነው ያውቋቸው ?

ለስ - ከተማሪነቴ ጊዜ አንስቶ ማለትም ከ1970 ጀምሮ እከታተላለሁ። ከውጪ ምሬ ከመጣሁ በኋላ ደግሞ እ.ኤ.አ. ከ1994 ጀምሮ ፈረንሳይና ጀርመን ባህል ዕከላት በቡድንም ሆነ በግልም ዝግጅቶቼን/የስዕል ኤግዚቢሽኖችን/አቀርባለሁ።

ቁ -በተለይ በጀርመን ባህል ማዕከልስ ?

ለስ - ከጀርመኖች ጋር ከስዕል ፕሮግራም ጋር በተያያዘ ፕሮግራም መርቼም ላትፌም አውቃለሁ።በተለይ በገ/ክርስቶስ ደስታ ዙሪያ የስዕሉንና ስነ ጽሑፍ ስራዎች ቀርቡ ነበር።

ቁ - የአሊያንስ ጋለሪስ አካባቢ?

ለስ - በአሊያንስ እንደጀርመን ባይሆንም አልፎ አልፎ ዝግጅቶችን አቀርባለሁ።

ቁ - የጀርመን ባህል ማዕከል የስዕል ባለሙያዎችን በምን መልኩ ነው
መርጠውና የሚያቀርቡት ?

ስ - ባህል ማዕከሉ የባለሙያዎችንና የሙያውን ደረጃ ለመጠበቅ
ክራሉ።በታዋቂ ባለሙያዎች ስራዎች ከተገመገሙና ማረጋገጫ ከሰጡህ በኋላ
፤ የሚቀርበው።ይሄ አሰራር ለሙያው ደረጃ ጥሩ ቢሆንም ለባለሙያው እንደችግር
ሉ ችግሮች ግን ነበሩበት።መራጮች ከአንተ ጋር አለመግባባቱ ካለ ሙያውን
ት ይችላሉ። ማስመስከርም ሆነ ማስረጋገጥ አትችልም።ኤግዚቢሽንህንም
ቀርብ ትችላለህ።ደረጃ ማውጣቱ አንድ ነገር ሆኖ፤ለሙያው እድገት ከሚኖረው
ሜታ አንጻር ማለቴ ነው።ሌላው ችግር ግን ችግር ነው።

ቁ - አሁን የምታነሳልኝ ችግር ቀደም ሲል የነበረ ነው ወይስ አሁንም ችግሩ
ኋል ?

ስ - አሁን እንደ ድሮው ችግሩ የለም ።መስራትና ማሳየት ከቻልክ መድረኩ
ት ነው ። ብዙ ወርክሾፖች፤ኤግዚቢሽኖች ይካሄዳሉ።ወደ ጀርመንም በመላክ
ምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ወጣቶችን ይልካሉ።

ቁ - እንዴት ነው የጀርመንም ሆነ የፈረንሳይ ባህል ማዕከል ወደ ስዕሉ ያዘነብላሉ
ል?

ስ - እርሱ እንደ ዳይሬክተሩ ሁኔታ ይለያያል። ዳይሬክተሩ የስዕል አፍቃሪ ከሆነ
ጋጋሚ የምታየው ስዕሉን ነው። የሙዚቃም ከሆኑ እንደዚያው ።

ቁ - ስዕልን የሚያቀርቡ ባለሙያዎች የተለዬ ክፍያ ያገኛሉ ?

ስ - እኔ እስከ ማውቀው ኤክስፖዠሩን፤መድረኩን ነው የሚፈጥሩልህ።የትስ
ሽው ትሄዳለህ ።መድረኩን ማግኘት ቀላል ነገር አይደለም ። አነስተኛ ቢሆንም
ውም የነጻ ያህል ክፍያ ይከፍሉሃል።

ቁ - የባህል ማዕከላት በትክክል የእኛን ኪነ ጥበብ አሳድገዋል ወይም
ተዋውቀዋል ለማለት እንችላለን ?

ጀርመን ባህል ማዕከል ስራ ጠንከር ያለ ነው። አሁን ደግሞ ወደ
ሲገቡ የባሰ የኪነ ጥበብ ስራዎችን አካዳሚያዊ በማድሩ በኩል ስኬታማ

መሼ አስቸግሬ ቃለ መጠይቅ እንድትሰጠኝ ለጠየኩህ ለጊዜህ ሳትሰስታና
ለበት ያልከውን ሁሉ በሙሉ ስሜትህ ስለሰጠኸኝ በእውነት ከልብ ነው
ው

ግር የለም። የባህል ማዕከላቱ መድረኩን በማመቻቸት አስተዋጽኦ አላደሩም
ዓልሆነ በደንብ ያዝልኛ ።

ኔ 9 ከቀኑ 11:45 እስከ ምሽቱ1:30 በጎተ ኢንስቲትዩት ግቢ ቃለ ምልልሱ

ከአቶ ዳንኤል ወርቁ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ዊቁ - በቅድሚያ ሙሉ ስምዎትን፤የትና መቼ እንደተወለዱ ቢገልጹልኝ ?

ኤልስ - ስሜ ዳንኤል ወርቁ እባላለሁ። በ1956 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለድኩ። እድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ተምሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሊትሬቸር ተመርቄአለሁ።

ዊቁ - ስራዎትን ቢገልጹልኝ ?

ኤልስ - ደራሲ፤ጋዜጠኛ፤የፊልም ባለሙያ ነኝ

ያቁ - ስለባህል ማዕከላቱ የሚያውቁትን ቢገልጹልኝ

ኤልስ - ከ1980ዎቹ ጀምሬ በባህል ማዕከላቱ አካባቢ የሚካሄዱ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን በመከታተልና በመሳተፍ በቅርበት አውቃቸዋለሁ ። አብሬአቸውም በመስራት ላይ እገኛለሁ።

ያቁ - በጀርመን ባህል ማዕከላትም ሆነ በፈረንሳይ በተለይም የስዕል ዝግጅቶችን ለማቅረብ ችግር እንደነበረ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ይህንን ችግር በቅርበት የማወቁ አጋጣሚ ይኖርህ ይሆን?

ኤልስ - አዎ ! አስታውሳለሁ። በተለይ ጀርመን ባህል ማዕከል አካባቢ በተለይም በስዕሉ ዙሪያ ስለሙያህ እነ እከሌ ይመስክሩልህ የሚለው አሰራር አስቸጋሪና በርካታ ሰዓሊያንን የማይመች ጉዳይ ነበር። ብዙዎችም እነዚያ ሰዎች ስላልመሰከሩላቸው ስራቸውን ለማቅረብ ሲቸገሩ ተመልክቼ የመጀመሪያውን የስዕል ማሳያ የግል ጋለሪ መክፈት ችያለሁ።

ያቁ - በጀርመን ባህል ማዕከል በተለይም በስዕሉ ዘርፍ በአሁኑ ወቅት መድረኩ ለተመቻቸ ከመሆኑም ባሻገር ውጪ አገር ድረስ ስራቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ ወጣቶች ደግሞ እዚያው ጀርመን አገር የአጭር ጊዜም ቢሆን ስልጠናና የልምድ ውውጥ እንዲያደርጉ እየተደረገ መሆኑን ይናገራሉ ይሄንን እንዴት ትመለከተዋለህ?

ግ አንስቶ በርካታ የኪነ ጥበብ ስራዎችን ለማቅረብ እንዲችሉ ማድረግ ይቻላል
ምነት አለኝ።

ለ ሰጠሽኝ ቃለ ምልልስ ከልብ አመሰግናለሁ።

ችግር የለም ። የማውቀውን ነው እኮ የነገርኩ።

ሰኔ 9 ከቀኑ 11፡45 እስከ ምሽቱ1፡30 በጎተ ኢንስቲትዩት ግቢ ቃለ ምልልሱ

፡ 4

# ጥያቄዎች

ለፈረንሳይ፤ጣሊያንና ጀርመን የባህል ማዕከላት ሃላፊዎች የቀረበ ጥያቄ

ኢትዮጵያና የአገራቱ የፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መቼ እንደተጀመረ
ን ሊነግሩኝ ይችላሉ? የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱስ መቼ ተጀመረ ተብሎ
ናል ? የግንኙነቱ መሰረትስ ምንድን ነበር ?

ህል ተቋሙ መቼና እንዴት እንደተቋቋመስ ሊያስረዱኝ ይችላሉ ? ዓላማውንስ
ሉልኝ ?

ባህል ተቋሙ በዋናነት የሚከወነው የኪነ ጥበብና የባህል እንቅስቃሴ ምንድን
በዋናነት ባይሆንም ምን ምን አይነት እንቅስቃሴዎችስ ይካሄዳሉ ?

ል ማዕከላቱ የሚቀርቡ ዝግጅቶችን ለታዳሚዎች ለመጋበዝ የምትጠቀሙባቸው
ተዋወቂያ ወይም የጥሪ መንገዶች ምን አይነት ናቸው ?

ል ማዕከላቱ የሚያቀርቡ ባለሙያዎችን በምን መስፈርት ነው
መርጧቸው? ምንስ አይነት ድጋፍ ታደርጉላቸዋላችሁ?

ፉት ዓመታት በሁለቱ አገሮች መካከል የኪነ ጥበብና ባህል ትውውቅ በማድረግ
ማዕከሉ የተጫወተው ተግባር ምንድን ነው ይላሉ?

ትዮጵውያን የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የባህል ማዕከሉ ያበረከተውን አስተዋጽኦ
ጹልኝ ይችላሉ ? ለከፍተኛ እውቅና ያበቃችኋቸው ባለሙዎችስ ይኖሩ ይሆን?
ሊጠቅሱልኝ ?

ሌሎች የባህል ማዕከላት ጋር በመቀናጀትም ይሁን ከኢትዮጵያውያን የኪነ ጥበብ
ማት ጋር በጋራ ያከናወናችኋቸው ተግባራትን ሊገልጹልኝ ይችላሉ ?

ኪነጥበብ ማበብና ማደግ የባህል ማዕከሉ ሚና እንደምን ይገለጻል ?

ሉ የተቋቋመበትን ዓላማ ከማስፈጸም አንጻር የአገራችሁን ባህል፤ቋንቋ እና
ብ ስራዎች ከማስተዋወቅና ከማስፋፋት አንጻር ምን ያህል ውጤታማ
ል ?

ብዛኛው በባህል ማዕከላቱ የሚቀርቡ ክንውኖች እዚያው መድረኩ ላይ አብረው
ቱ እንጅ በአግባቡ ዶክመንት ተደርገው ያለመቀመጥ ችግር እንዳለባቸው
ከት ችያለሁ፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ ?

ል ማዕከላቱ በስፋት ኪነ ጥበብን ከማስተዋወቅና ከማስፋፋት አንጻር አሁን
ው በላቀ ደረጃ እንዳይሰራ የሚያደርገው እና እንደችግር የሚያነሳው ካለ
ላኝ? የገንዘብ፤የባለሙያ፤የመንግስት ድጋፍ እጦት አሊያም ሌሎች ምክንያቶች

## ጥያቄ 2.

...ታዊ ተቋማት ፤ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፤ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና ...በባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቀረቡ ጥያቄዎች

...ዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት ኢምባሲዎች የባህል ማዕከላት መቋቋም ...ንም ሆነ ለሁለቱ አገሮች የሚኖራቸው ጠቀሜታ ምንድነው ?

...ም የፈረንሳይ፤የጣሊያንና የጀርመን ባህል ማዕከላት የሚያከናውኗቸውን ...በ ስራዎች በምን መልኩ ክትትልና አስፈላጊ ሆኖም ሲገኝ ድጋፍ ...ቸዋላችሁ ?

...ገራችን የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ማደግና መታወቅ የባህል ማዕከላቱ ምን ...ሚና እየተጫወቱ ነው ይላሉ?

...ዕከላቱ እምብዛም የራሳችን ያልሆነ ባህልን ወይም የኪነ ጥበብ ውጤቶችን ...ዋወቅ ረገድ ለህብረተሰቡ ያስተላልፋሉ የሚል አመለካከት ቢኖር ምን አይነት ... ነው የሚደረገው?

...ዲስ አበባ ወጣ ብለውም ወደ ክልሎች በመሄድ የባህል ትውውቅና የኪነጥበብ ...ችን የሚያስተላልፉበት ወይም የሚያሰራጩበት አጋጣሚዎች ይኖራሉና ...ችሁ በክትትልም ሆነ በድጋፍ እያከናወነ ያለውን ቢገልጹልኝ?

...ገርን መልካም ገጽታም ሆነ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ከማጠናከር አንጻር ... ማዕከላት በአግባቡ አስተዋውቀንባቸዋል ለማለት ይቻል ይሆን ? ... በምን መልኩ?

...ጣይ በባህል ማዕከላቱ የሚቀርቡ የኪነ ጥበብ ስራዎችን ለአገር በሚጠቅም ... ለማስተዋወቅ ምን ማድረግ ይኖርብናል ትላላችሁ?

...ኪነጥበብና ባህል ትስስሩን በመጠቀም ከየሃገራቱ ጋር ያለውን ዲፕሎማሲያዊ ...ነት ለማሳደግ ታስቧል?

ጥያቄ 3

ማዕከላቱ የኪነጥበብ ስራዎቻቸውን ላዘጋጁና ላቀረቡ ባለሙያዎች የቀረቡ
ዎች?

ስምዎትንና ዕድሜዎትን ቢገልጹልኝ?

ወቅት በምን ሙያ ላይ ይገኛሉ?

ማዕከላቱ የኪነጥበብ ስራዎች ከመቼ እስከ መቼ ነው ያቀረቡት?

ማዕከሉ የኪነጥበብ ስራዎችን ለማቅረብ እንዴት ተመረጡ?

ማዕከል ምን አይነት የኪነጥበብ ስራዎችን ይዘው ቀርበዋል?

ሉ የኪነጥበብ ስራዎችነ ለማቅረብ ምን አይነት ድጋፍ አገኙ? በገንዘብ፤
ክ ፤ ወዘተ ካለ ቢገልጹት

ማዕከሉ ለሙያዎ ማደግ አልያም ለእውቅና እንድበቃ እገዛ አድርጎልኛል
?

ማዕከላቱ ለአገራችን ጀማሪ የኪነጥበብ ባለሙያዎችም ሆነ ለአንጋፋ
ያዎች እያደረገ ያለውን እገዛ እንደምን ይገልጹታል ?

ላቱ ለአገራችን የኪነ ጥበብ እድገት እየሰጡ ያሉትን አበርክቶ እንዴት
ጹታል?

ከላቱ ዙሪያ ሊነሱ የሚገቡ ድክመቶችና ይሄ ቢስተካከል የበለጠ የባህል ማዕከሉን
ከግብ ያደርሳሉ የሚሉት አስተያት ካለዎት ?

## ጥያቄ 4

ል ማዕከላቱ የኪነጥበብ ስራዎችን በመከታተል ለዘገቡ ጋዜጠኞች የቀረበ ጥያቄ

-ሉ ስምዎት ፤ እድሜዎት ና ከየትኛው ሚዲያ እንደመጡ ይግለጹልኝ ?

ባህል ማዕከላቱ የኪነጥበብ ስራዎችን በመከታተልና በመዘገብ ለምን ያህል ጊዜያት ም ዓመታት ሰርተዋል ?

ሊያንስ፤ በጎተ እና በጣሊያን የባህል ማዕከላት ምን አይነት የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ርባሉ ?

እስካሁኑ ክትትልዎ ምን አይነት ዝግጅቶች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ?

ዝግጅቶቹ ምን ያህል አስተማሪ፤አዝናኝና ኪነ ጥበብን የሚያስተዋውቁና የሚያስፋፉ ው?

ባህል ማዕከላቱ ኢትዮጵያውያን የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች መድረኩን ከማግኘት ነተው በአግባቡ ስራዎቻቸውን አቅርበውበታል ትላላችሁ ?

ባህል ማዕከላቱ የየአገራቸውን ባህልና የኪነ ጥበብ ስራዎችንስ ለኢትዮጵውያን ተዋውቀዋል ወይም አስፋፍተዋል ?

ማዕከላቱ የሚቀርቡትን ዝግጅቶች በምታቀርበው የኪነ ጥበብ ፕሮግራም ላይ ምን ል አቅርበሃቸዋል? ከቀረቡስ በኋላ ያገኘሄው ግብረ መልስ ምን ይመስላል ? ግጅቶቹ መልዕክት አድማጮች እንደወደዷቸውስ ገልጸውልህ ይሆን ?

ጥያቄ 5

ል ማዕከላቱ የኪነጥበብ ዝግጅቶችን የተከታተሉ አድማጭ ተመልካቾች የቀረበ

ሉ ስምዎትን፤እድሜዎትንና ስራዎትን ቢገልጹልኝ ?

ህል ማዕከላቱ የኪነ ጥበብ ስራዎችን ከመቼ ጀምሮ ነው የሚከታተሉት ?

ኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን የሚከታተሉት የሙያው ፍቅር ወይስ የሚቀርቡት
ቶች ስለሚስብዎት ነው ? በምንስ መልኩ ነው ዝግጅቶችን አውቀው
ታተሉት ?

ስዎ በተከታተሏቸው ዝግጅቶች በአመዛኙ ምን አይነት ዝግጅቶች ናቸው በባህል
ላቱ የሚቀርቡት ?

ትዮጵያውያን የኪነጥበብ ባለሙያዎች በማዕከላቱ ምን ዝግጅቶች ላይ በስፋት
ባሉ ?

ውጪ አገርስ ከሚመጡ ዝግጅቶች መካከል በይበልጥ የሚስብዎትና በተደጋጋሚ
ቡ የሚመርጧቸው ዝግጅቶች የትኞችን ነው ?

ገራቸውን ኪነጥበብ በተደጋጋሚና ለበርካታ ጊዜ በማቅረባቸው ምክንያት
ቸውን ያወቁ ያህል ይሰማዎታል ? ለምሳሌ የፈረንሳይ፤የጣሊያን እና የጀርመን
ዚቃ ዝግጅታቸውና ቋንቋቸውን በቀላሉ የመለየት ሁኔታ አለ ?

ህል ማዕከላቱ መኖር ለአገራችን የኪነጥበብ ባለሙያዎች ሙያቸውን ከማሳደግ
ር፤የውጪውን የኪነጥበብ ውጤት ለአገራችን ከማስተዋወቅ አንጻር እና
ዓሚዎች ደግሞ የመዝናኛና የባህል ትውውቅ እና ልውውጥ ከማድረግ አንጻር ምን
ድልድይ ሆነው አገልግለዋል ታላላችሁ?